
# ሐመር

ዘ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፯ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ኅዳር/ታኅሣሥ ፳፻፩ ዓ.ም




## እንኳን ለጾመ ነቢያት አደረሳችሁ

በጠበሉ ፈዋሽነት የሚታወቀው
ጥንታዊው የአቡነ ሃራ ገዳም
(ባሕርዳር ዙሪያ)
ታሪኩን በሚቀጥሉት ኅትመቶች ይጠብቁ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን

## ነፃ አውጪው ማነው?



ካሰቡትና ከጠበቁት በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ከታላላቅ ገዳማትና አድባራት ተገኝተው የተመለከቱ ደጋግ ምእመናን ለአግራሞታቸው ስንኝ ቋጥረው «ዓይኔ ዓለም አየ እግሬ ደርሶ /፪/» እያሉ እያዜሙ እግዚአብሔርን ያመስግናሉ:: የዛሬውን ትዝብቴን ግን ምን እንደምለው አላውቅም::

በወርሃዊ ወይም በዓመታዊ በዓላት በሚከበሩበት አብያተክርስቲያን ጠዋት አልያም ማታ እየሔድኩ ከቅዳሴውና ከስብከቱ እየተሳተፍኩ ለነፍሴ እቃርማለሁ:: ታዲያ ሁሌም የሚጨንቀኝ አንድ ነገር አለ:: እንደ እኔ አትኩሮታችሁን ስቦ እንደሆን፤ መንግሥት የጎዳና ላይ ንግድን እየተቆጣጠርኩ ነው በሚልባት በመዲናችን በአዲስ አበባ፤ የወርና የዓመት በዓላት በሚታሰቡብትና በሚከበሩበት አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ አንዳንዴም ውስጥ የጐዳና ላይ ንግድ ተጧጡፎ ማየት የተለመደ ትዕይንት ነው:: ከኢየሩሳሌም የመጣና የሚያበራ መስቀል ከሚለው ጀምሮ የዝነኛው ሰባኪና ዘማሪ አዲስ የወጣ መዝሙር እስከሚለው ባለሞንታርቦ፣ የቤተ ክርስቲያኑን መውጫና መግቢያ በር አንቀው የቅዳሴና የስብከቶቹን መልእክት እንዳንሰማና በተረጋጋ ኅሊና ከፈጣሪ ጋር እንዳንቆይ የሚረብሹን የትየለሌ ሆነዋል:: ለአንድ ሰው አንድ ድምፅ ማጉያ የተባለ ይመስል፤ በነፍስ ወከፍ ድምፅ ማጉያ ይዘው የሚለምኑና የሚነግዱ ወራሪዎች በዝተዋል:: የሚገርመው ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር የማይጣጣሙ ሸንኩርት፣ ቅቤና ሹካ ማንኪያ ወዘተ... ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ተደርድሮ በጨኸት ታጅበው ይሸጣሉ::

የቀድሞዎቹ እናቶቻችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲጓዙ የኔ ቢጤዎችን በማሰብ፤ ከቻሉ በመቀነታቸው ካልቻሉ በዳንቴላቸው ቋጥረው በጥሬና በዓይነት ይመጸውቱ ነበር:: የዛሬዎቹ ግን በያዙት ሳንቲም ከቤተ ክርስቲያን ደጅ የወደቁትን ምንዱባንና የቤተ ክርስቲያኑን ሙዳየ ምጽዋት ከመጐብኘት ይልቅ፤ ከቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ቄጤማና ጭሳጭስ ያለዞም ጫማና ውስጥ ልብስ ሸምተው ይገባሉ:: ለመሆኑ ከነፍስ ገበያ ይልቅ፤ ለሥጋ ገበያ ስናደላ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በመናቅ ስንነግድበትና ስናስነግድበት እግዚአብሔር ዝም የሚለን ይመስለናል? ጅራፍ ገምዶ የማይገርፈን ገበታችንን የማይገለብጠው ይመስለናልን? «ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፤ የገንዘብ ለዋጮችንም፣ ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም መንበሮች ገለበጠና ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች፤ ተብሎ ተጽፎአል እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው» ተብሎ መጻፋንስ ዘንግተነው ይሆን? ማቴ.፳፩÷፲፪:: እኔን የጨነቀኝ ይኸው ነው፤ የነፍስ ገበያ በሥጋ ገበያ ሲወረር ነፃ አውጪው ማነው? ሰበካ ጉባዔው፣ ሰንበት ትምህርት ቤቱ? ስበከተ ወንጌሉ? ጠቅላይ ቤተ ክህነት? ምእመናን ወይስ መንግሥት? አበቃሁ::✥

*አንተነህ ነኝ*
*ከፊት በር*

## በልምድ መመላለሱ ይብቃን

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምታዘክራቸው የቅዱሳን አበውና እማት፤ የፈጸሙት ገድልና ትሩፋት ቅዱሳት መጻሕፍትን እየመረመሩ፤ አጠገባቸው ያሉትን ሊቃውንት እየጠየቁና እየተረዱ በዕምነትና በእውቀት እንጂ እንዲሁ በልማድ በመመላለስ አይደለም:: በልማድ የሚደረግ ነገር ሁሉ ፍጹም አይደለም:: ይልቁንም ያደክማል፣ ያሰለቻል፣ አያከብርም፣ አያጸናም:: እስኪ አንድ ማሳያ ልጥቀስ::

ሥርዓተ ቅዳሴውን ለመከታተል ወደ ቤተ ክርስቲያን ከማቅናታችን በፊት ልናደርጋቸው የሚገቡ ዝግጅቶች አሉ:: ንጽሕናችንንና አለባበሳችንን ጨምሮ ሥርዓተ ቅዳሴው ላይ ደግሞ ማድረግ የሚገባን በርካታ ቁም ነገሮች አሉ:: ይኸውም ጸሎተ ንስሐ ሲነበብ፣ አሐዱ ሲባል፣ በየጊዜ በሚሰማው የዲያቆኑ ዐዋጅ ጊዜ፣ በእንተ ቅድሳት ሲነበብ፣ ወንጌል ሲነበብ በሥርዓተ ቁርባን ጊዜ ወዘተ... ምን እንደሚባልና ምን እንደሚደረግ አውቀን፤ ካላወቅንም ጠይቀን ሥርዓቱን መከታተል ይኖርብናል:: አለበለዚያ ግን ቅዳሴው ላይ የምንገኘው በግድ ይሆንና ሙሉ ቅዳሴውን በድካም፣ በማዛጋት በእንቅልፍ ያለዛም በወሬ እንጨርሰዋለን:: የቀድሞዎቹ እናቶቻችንና አባቶቻችን ግን በእምነትና በዕውቀት ስለሚቆሙ ቅዳሴውን በፍቅር ጀምረውት ያውም ፊታቸውን በእንባ እያጠቡ ውስጣቸው ሀሴትን ተላብሶ በፍቅር ይጨርሱታል::

በነገራችን ላይ ይህን እንደ ምሳሌ አነሣሁት እንጂ፤ ብዙ አለ:: በእርግጥ የእግዚአብሔር የማዳኑ ጥበበ ከኀሊና በላይ ነው:: ነገር ግን እርሱም ቢሆን ያስተማረን ለመዳን ማወቅና ማመን እንዳለብን ስለሆነ በተለይ በዘመናችን ያሉ አሕዛብ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያነሡትን ያለ አዋቂነት ተቃውሞና ትችች ለማምከን ሁላችንም በተለይም ወጣቶች ዐውቀንና አምነን ክርስቶስ በአስተማረን መንገድ ልንጓዝ ይገባናል:: በልምድ መመላለሱ በራሳችንም ሆነ በሌላው ዘንድ ትርፍ የለውም::✥

*ጽጌ ማርያም*
*አዲስ አበባ*

©ማኅበረ ቅዱሳን

# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፬ — ኅዳር /ታኅሣሥ ፳፻፩ ዓ.ም.

## ይዘት

**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**

* የመዝሙራችንን ችግሮች ለመፍታት ሁላችንም እንነሣ ______ ፪

**መልእክቶቻችሁ** ______ ፬

**በረከተ ወንጌል**

* ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም ______ ፮

**ወቅታዊ ጉዳዮች**

* መዝሙራችን ወዴት እያመራ ነው? ______ ፰

* ቃለ በረከት ዘቅዱስ አትናቴዎስ ______ ፲፪

**ትምህርተ ሃይማኖት**

* ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት ______ ፲፯

**ጥያቄዎቻችሁ**

* ጫትን በመጠኑ ብንጠቀምበት ምን ይጐዳል? ______ ፲፱

**ምዕራፍ** ______ ፳፪

**ኪነ ጥበብ**

* «ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ» ______ ፳፫

**እናስተዋውቃችሁ**

* ተአምረ ማርያም በግብጽ ______ ፴፩

* በጆሮአችን የሰማነውን በዓይናችን አየነው ______ ፴፫

**ሐመረ ሕይወት**

* ዘጠኝ ቀንጮ በአንዲት ጎጆ ______ ፴፮

**ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**

* ጥቂት ስለ ግእዝ ቋንቋ ተመራማሪዎች ______ ፴፱

* የዐቢይ አንቀጽ እርባታ ______ ፵

ዋና አዘጋጅ
ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

ም/ ዋና አዘጋጅ
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

አዘጋጅ
ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

ሪፖርተሮች
ጌታቸው በቀለ
ዲ/ን ምትኩ አበራ

የገጽ መልክአ /ሌይ አውት/ ዲዛይነር
ርብቃ ኃይለማርያም

ረ/ የገጽ መልክአ /ሌይ አውት/ ዲዛይነር
ወይንሸት ወልደጻድቅ

ጸሐፊዎች
ጸዳሉ ሁንዴሳ
ልደት አስፋው
ደብረወርቅ ተክለጽዮን

የዝግጅት ክፍሉ
☎ 011 1 553442

የዝግጅት ክፍሉ፡
Email:- hamermk08@gmail.com

የማኅበሩ ጽ/ቤት
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org

በማኅበረ ቅዱሳን የሰሜን አሜሪካ መካነ ድር
www.mahiberekidusan.org

መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ

**«ማኅበረ ቅዱሳን»**

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣
የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣
ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት
በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል።

*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።*

መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።*

# የመዝሙራችንን ችግሮች ለመፍታት ሁላችንም እንነሣ።

መዝሙር «ዘመረ - አመሰገነ» ከሚለው ግሳዊ ስም ወጥቶ ለታወቀ ድርሰት መጠሪያ ከሆነ ሰነባብቷል። በየሰን በቱና በየክብረ በዓላቱ በየማኅሌቱ የሚቆመው የማኅሌታችን ምስጋና መዝሙር ይባላል። አሁን ግን ይህን ስያሜ ወስዶ ለራሱ የሚጠቀምበትና ምእመናን በሰፊው የሚያውቁት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በግጥምና በዜማ ድርሰት ተዘጋጅቶ ለምእመናን የሚቀርበውን አዲስ የካሴት ሥራ ነው። ታዲያ ይህ መዝሙር ምእመናን በተለይም ወጣቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማቅረብ ስብከተ ወንጌሉንም ለማስፋፋት ታላቅ እገዛ ሲያደረግ ቆይቷል። በተለይ ቀደም ያሉት መዝሙሮች በግጥም ጥንካሬያቸው፣ በመንፈሳዊ ይዘታቸውና በኦርቶዶክሳዊ ላህያቸው ምእመኑን ሲያጽናኑት፣ ለንስሐ ሲያስለቅሱት በደስታና በተመስጦም ሲያዘምሩት ቆይተዋል። ትምህርቱን ተምሮ እነዚህን መዝሙራት ሲዘምር አስቀድሶ እንደቆረበ ሰውነቱ በሐሴት፣ አእምሮውም በውሳጣዊ ሰላም ይሞላ ነበር።

ይህን ታላቁን ሀብታችን ግን አጀማመሩን እንጂ አካሔዱን ያሰበበት አልነበረም። ጥሩነቱን እንጂ የጥሩነቱን ምንጭ አጥንቶ በዚያው እንዲቀጥል ያሰበለት፣ ሥርዓትም የዘረጋለት አልተገኘም። ስለዚህም እንደሌላው ሁሉ እያደር እየላላ፣ ጣዕሙ እየቀነሰ፣ ወዙ እየጠፋ፣ ላህዩም እየደፈረሰ መጥቷል። በዚህም «ታመመ» ሊባል የሚችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ።

መዝሙሩ ታመመ እንጂ አልሞተም፤ ይሁን እንጂ ሊያክመው ወይም ሊያሳክመው የተነሣ ግን አልተገኘም። ከራሱ ከኢትዮጵያዊው ከቅዱስ ያሬድ ዜማ፣ ከወቅቱም ከማኅሌተ ጽጌ ወረቦች የሚሰማውን አዋጅ ካደመጥነው መዝሙሩ ራሱ ስለመዝሙራችን ይጮኻል። «እለ ትነብሩ ተንሥኡ ወእለ ታረምሙ አውሥኡ፣ ...» የተቀመጣችሁ ተነሡ፤ ዝም ያላችሁም ዘምሩ /መልሱ/ እያለ።

ችግር እንደሌለበት አይተን፣ በይሉኝታ ገመድም ታሥረን ለተቀመጥነውሁሉ ጩኸቱን ያሰማናል። በ«አያገባኝም» ዙፋን የተቀመጣችሁ፣ በይሉኝታ መሐረብ አፋችሁን ይዛችሁ ዝም ያላችሁ አሁን የምትነሡበትና ስለመፍትሔው የምትናገሩበት ዘመን ነው ይለናል።

በርግጥም አሁን መዝሙር ላይ ያለውን ችግር እንደሌለ አድርገን የምናልፍበት ጊዜ አይደለም። ሕዝቡን አንድ አድርጎ በተመስጦ ጉዳና ይመራ የነበረው መዝሙራችን ዛሬ ግማሹን በዝላይና በጩኸት የሚያሳብድ ሆኖአል። ኀሊናን የሚመረምሩ፣ ራስን በመግዛት መንፈስ ነፍስን መስጠው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኙ መዝሙራት የተወገዙ ያህል ከቤተ ክርስቲያን መድረክ ተባርረዋል። በሌሎችም ዘንድ እንደ ጉባኤ «ፍሪጅ» /ማቀዝቀዣ/ ተቆጥረዋል። ስለዚህም ምክንያት ሊቃውንቱ አዝነዋል፤ ምእመናንም ግራ ተጋብተዋል። ስለዚህ የመዝሙራችንን ችግር ለመፍታት፣ ሓላፊነት ያለባቸው አካላት ሁሉ ለመፍትሔ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህም ከሚከተሉት አካላት ተጨባጭ መፍትሔ ይጠበቃል።

*፩ኛ/ ቅዱስ ሲኖዶስ፡-* ቅዱስ ሲኖዶስ በመዝሙርና በአዘማመሩ በኩል ያሉትን ችግሮች በውል መረዳት እንዲቻለው ማስጠናት ይኖርበታል። የጥናቱን ውጤት መሠረት አድርጎም ፖሊሲ አስቀርጾና አጽድቆ ማውጣት ይጠበቅበታል። ፖሊሲውን የሚያስፈጽም፣ የሚያግዝ፣ የሚቆጣጠርና ፈቃድ የሚሰጥ ተቋምም ከተግባርና ሓላፊነቱ ጋር ማቋቋም ለነገ የማይባለው ተግባሩ መሆን አለበት። በዚህም የመዝሙርን ጉዳይ እንደተራ ነገር ሳይቆጥረው ቤተ ክርስቲያኒቱን በሁለንተናዋ የመምራት ሓላፊነቱን በተግባር በማሳየት እንዲገለጥ ያደርገዋል።

*፪ኛ/ ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፡-* እስካሁን ባለው የቤተ ክርስቲያናችን አደረጃጀት የወጣቶች ጉዳይን የሚመለከተው ይኸ መምሪያ ነው። ይሁን እንጂ የሚጨበጥ፣ መሠረት ያለው፣ ችግር ፈች የሆነና ሊጠቀስ የሚችል ሥራ እስካሁን አላሳየንም። ለዚህ ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም ከእነዚህ ጥቂቶቹን እንኳ በአግባቡ ሲፈታቸው መታየት ነበረበት። ነገር ግን ይህ ሲሆን አልታየም። መዝሙር ትልቁ የወጣቶች ጉዳይ ከመሆን አልፎ አሁን አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን መምሪያው ቅድሚያ ተነሣሽነቱን መውሰድ ነበረበት። ስለዚህም የመዝሙርንም ሁኔታ በአግባቡ በማጤን ዘማርያንን፣ ሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን፣ አሳታሚዎችንና ሌሎች ባለድረሻዎችን /Stake holders/ በማሰባሰብ በጥናት ማወያየት፣ ጊዜያዊ መፍትሔም ቢሆን መስጠትና አዎንታዊ ዕርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል።

*፫ኛ/ መንፈሳዊ ኮሌጆች፡-* እነዚህ ተቋማት የመዝሙርን ጉዳይ በብዙ መንገድ ማስጠናት ይጠበቅባቸዋል። ችግሮቹንና መፍትሔዎቹን፣ ታሪኩንና ትውፊቱን ... በጥናት ማሳየት ከእነርሱ የሚገኝ መሆን አለበት። ከዚህም አልፎ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት፣ ልክ እንደ ሌላው ትምህርት ዐቢይ /Major/ እና ንዑስ /Minor/ ሆኖ በኮሌጅ የሚሰጥበትን የትምህርት መስክ /faculty or Department/ ሆኖ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ከኮሌጆቹ የሚጠበቅ ነው። በዚህ መሠረት ቢታነጽ፣ ሊያመጣ የሚችለው ለውጥና ጠቀሜታ በእጅጉ ታላቅ ይሆን ነበር። በዚህ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አቅጣጫ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችና ዜማዎች የሚተላለፉበትን መንገድ፤ ያሬዳዊ ዜማዎች ለሌላ ቋንቋ መዝሙሮች ሊኖራቸው የሚችለውን ጠቀሜታ በማጥናትና በሚመለከተው የቤተ ክርስቲያኒቱ አካላት እያስወሰኑ ለትግበራ ማነሣሣት አሁንም ከእነዚሁ ተቋማት ካልሆነ ከማን ይጠበቃል:: አሁንም አልመሸም፤ ከትናንት ብንዘገይም ከነገ መድረስ እንችላለንና:: በተለይ በየኮሌጆቹ ያሉ የጥናትና ምርምር ዘርፎች /Centers/ ፕሮጀክት ቀርጸው ባለሙያ መድበው በቀላሉ ሥራውን መሥራት ይችላሉ:: ከዚህም በላይ ራሳቸው ተነሥተው ሌላውንም በዕውቀት ደወል በሥርዓትም ነጋሪት ማስነሣት ይኖርባቸዋል::

*፪ኛ/ ሰንበት ት/ቤቶች፡-* የመዝሙርን ችግር ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ከሚችሉትና ቅድሚያውን ከሚወስዱት ከመዘምራን በኋላ ሰንበት ት/ቤቶች ሁለተኛውን ቦታ ሊይዙ ይችላሉ:: ይህን የሚያስብሉ ብዙ ምክንያቶች አሉና:: በመጀመሪያ ደረጃ ከአሁን በፊት ከተነሡት መዘምራን አብዛኛዎቹ የወጡት ከሰንበት ት/ቤት ነው:: ወደፊትም ይህ ሁኔታ የማይቀጥልበት ምክንያት አይኖርም:: መዝሙሮች በቡድን መዘምራን የሚጠኑበት ቦታም ሰንበት ት/ቤቶች ናቸው:: ከዚህም በላይ ወጣቶችን ለመቅረጽ፣ በኮርስ የትምህርተ ሃይማኖት ዕውቀታቸውን ለማሳደግም ከሰንበት ት/ቤቶች የተሻለ መልካም ቦታ ያለ አይመስልም:: ስለዚህ ትልቅ ድርሻ እንደሚኖራቸው የታመነ ነው::

ሰንበት ት/ቤቶች መዝሙርን በተመለከተ ብዙ ሥራዎችን ሊሠሩ ይችላሉ:: በችግሮቹ ዙሪያ በማወያየትና መነቃቃት በመፍጠር፣ ለሰንበት ት/ቤት መዘምራን ሥልጠና በመስጠትና ኦርቶዶክሳዊ ላህይ ያላቸውን መዝሙሮች አስጠንቶ ጉባኤያቱን በማገልገልና በመሳሰለው ሁሉ ላቅ ያለ ድርሻ ሊወጡ ይገባቸዋል:: ከዚህም አልፎ በስሜትና በአጓጉል የወጣትነት መሻት ላይ ተመሥርተው ያፈነገጡ መዝሙሮችን ባለመዘመርና እንዲያም ሲሉ በጉባኤያቸው እንዳይዘመሩ በመከልከል በምእመኑና በሌሎች አካላትም ላይ ትንሣኤ መፍጠር ይችላሉ፤ የሚጠበቅባቸውም ይኸው ነው::

*፫ኛ/ መዘምራኑ፡-* መዘምራኑ በተለይ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበሩት በቅን ኅሊናና በትሑት ሰብእና ብዙ አገልግሎት ፈጽመዋል:: በቅርብ ጊዜያት የተነሡት ወጣት መዘምራንም ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል:: ይህ ሁሉ ግን በመዝሙሮቻቸው ላይ የተፈጠሩትን ችግሮች አይሰውርባቸውም ብለን እናምናለን:: ስለዚህ ስለአገልግሎቱ የደከሙትን ያህል ስለመዝሙሩም ንጽሕናና ቅድስና ሊጋደሉለትና ከማንኛውም ጥበብ በላይ የሚከበር፣ የሚወዳደር በሥርዓቱ ብቻ ሊጓዝ የሚገባው ዕንቍ ሀብታችን ሊያደርጉት ይችላሉ:: እንኳን ለአምላክ የሚቀርብ መዝሙርን ሀገራዊ ሙዚቃን እንኳ እንደ ክት ልብስ ለልዩ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ብቻ በማስከበር የሚሠሩትን ምዕራባውያንን ለሚያዩ ወጣቶች ይህ ከባድ አይመስለንም:: ከመዘምራኑ ቀድሞ ለመዝሙሩ የሚያስብ መኖርም አልነበረበትም:: ከገበሬው የበለጠ ዘሩን /አዝመራውን/ የሚጐበኝ፣ የሚከታተልና አረሙን የሚያርም እንደሌለው ሁሉ ለመዝሙርም ራሳቸው ቀድመው ሊደርሱለት ይገባል:: ስለዚህ ራስን በትምህርት ከማነጽ፣ ችግሮቹን ከመለየት፤ መፍትሔ ከማቅረብና ከመተግበር ጀምሮ በውይይትና በምክክር፤ የጋራ መድረኮችንም በመፍጠር የመዝሙርን ቅድስና ማጉላት ይጠበቃል:: በጋራ እንደሚዘምሩትም ሁሉም በጋራ የሚደሰቱበትን መፍትሔ ማቅረብ ይገባቸዋል:: «ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት ወቅኔያትን ...»ን ብዙ ጊዜ እንዘምረዋለን:: እውነት ነው ቅዱስ ያሬድ ከድምፁና ከዜማው ባሻገር የቅኔያትና የምስጢራት ፈጣሪ፤ የመንፈሳዊ ፍልስፍና ፋና ወጊ ነው:: ያሬዳውያኑ ኢትዮጵያውያን መዘምራንም በያሬዳዊ መንፈስ የስብሐተ መላእክት፣ የቅኔያት ፈጣሪ መሆንን ለራስ ገንዘብ በማድረግ ሕዝቡንም ከረሀቡ ቀን ምግብ ከ«ሞት እንጀራ» መታደግና የቀረበውንም እንደ ኤልሳዕ በመፈወስ የሞት ሊሆን የነበረውን ማንንም ከመጉዳቱ በፊት የሕይወት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: በሌላ ቋንቋ የመዝሙርን ችግር ለመፍታት ከማንም በፊት ዘማርያኑ ቅድሚያውን ሊወስዱ ይገባቸዋል::

*፬ኛ/ ምእመናን፡-* የምእመናን ድርሻ ግለሰባዊ ቢሆንም አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፤ ተቋማዊ የመሆን ዕድሉም ሰፊ ነው:: /ለምሳሌ የማኅበራት ድርሻ/:: ስለዚህ ምእመናንም የሚወዷትን ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚደሰቱባት ብቻ ሳይሆን ለንስሐና ለጽድቅ የሚዘጋጁባት ማድረግ ይችላሉ:: ሁሉንም ከማግበስበስም እንደ አቤል ካለው አንጠርጥሮ መርጦ ንጹሑን መሥዋዕት ለአምላክ ማቅረብ ይገባልና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል::

ከዚህም በላይ ብዙ ሐሳፊነቶችን ልንወስድና የድርሻችንን ሁሉ ልንወጣም ይገባናል:: ቀደም ብለን እንደገለጽነው ስለመዝሙሩ እንድንነሣ የጠራን የነገረንም ራሱ መዝሙሩ ነው:: በእውነት እግዚአብሔር «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትን አይደለም፤ ... የፍሪዳችሁ መስባት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? ...» እንዳለው ውሳጣዊነት ርቱዕነትን ትቶ በአፍአዊ ሁናቴ የከበረው ሁሉ ደስ የሚያሰኘው አይደለም:: እንደ ቃየን መሥዋዕት እንክርዳድ የተቀላቀለበት ነገር ብናቀርብ የእግዚአብሔር ፊት ከእኛ ተነሥቶ ወደ ቅዱሳኑ /ምርጥ መሥዋዕት አቅራቢዎች/ ብቻ እንደሚሆን የማንጠራጠረው ሐቅ ነው:: ስለዚህም ለመፍትሔው በጋራ፣ በፍቅር፣ በአንድነትና በእውነት እንነሣ:: በራሱ በመዝሙሩ «እለ ትነብሩ ተንሥኡ፤ ወእለታረምሙ አውሥኡ» ተብለናልና::✦

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## እንደ ሙስሊሙ የፕሮቴስታንቱም አክራሪ አሳስቦኛል

ከዚህ በፊት በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ መናፍቃን በመቃብር ቦታ ሰበብ ሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ መከራ እያደረሱ መሆኑን አንብቤያለሁ። በእርሱ ተገርሜ ሳይበርድልኝ አዲስ አበባ አንድ የፕሮቴስታንት ዘመዴ ሰርግ ላይ ተገኝቼ የሰማሁት የበለጠ አስደንግጦኛል። ምን መሰላችሁ መናፍቃኑ ሰርጉን በማሰብና በመዘመር ስም ይጮኻሉ። ያ ባልከፋ ለእኔ እንግዳ የሆነው ነገር ግን «ኦርቶዶክስ ዋ…፣ ዋ…፣ ኦርቶዶክስ ዋ… ዋ…» በማለት ያሰሙት የዛቻና ማስፈራሪያ ድምፅ ነው። እናም ወገኖቼ እነዚህ ሰዎች ዕድል አላገኙም እንጂ ዕድል ቢያገኙ ከሙስሊሙ አክራሪዎች ባላነሰ በነፍስም በሥጋም ገዳዮቻችን እንዳይሆኑ ሰግቻለሁ። እባካችሁ ይሄ አዝማሚያ ይጠናና መንፈሳዊ መፍትሔ ይሰጠው።፨

*ኤርምያስ አባተ*
*ከአዲስ አበባ*

## ሊበረታቱ ይገባል

ውድ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? የሐመርና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ የረጅም ጊዜ ደንበኛ ነኝ። መጽሔቱና ጋዜጣው መንፈሳዊ እውቀቴ እንዲዳብርና የቤተ ክርስቲያንን ወቅታዊ ሁኔታ እንዳውቅ ረድተውኛል። በተለይም በአቡጊዳ የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ዓምድ ላይ የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር የሚያቀርበው የግእዝ ትምህርት ብዙዎቻችንን የግእዝ ቋንቋ እንድንሰማ፣ እንድንናገርና እንድናነብ አስችሎናል።

የዓምዱ ጸሐፊ መምህር ደሴ ቀለብ በማኅበረ ቅዱሳን አዲስ አበባ ማዕከልና በአንዳንድ የአዲስ አበባ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የግእዝ ቋንቋን ለወጣቶች ያስተምራሉ። ይህንን መልካም ጅምር ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ በሰንበት ት/ቤት ወጣቶችም ዘንድ ልታስፋፋውና የግእዝ ት/ቤትም ሊኖራት ይገባል። መምህር ደሴና መሰሎቻቸው ሁሉ ሊበረታቱ ይገባል።፨

*ታከለ አሳየ*
*ከአፋር ሎጊያ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን*

## መግቢያ ቀዳዳ …

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች «መዝሙራችን ወዴት እያመራ ነው?» በሚለው ርእስ የወጡትን ተከታታይ ጽሑፎች ሳነብ እንባዬ ይመጣል። ምክንያቱም በግቢ ጉባኤም ሆነ በሰንበት ት/ቤት በመዝሙር የተነሣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲከፋፈሉ በማየቴ ነው። ይሔ ደግሞ ከእኛ በኋላ ለተነሡ ሌሎች የኑፋቄ ድርጅቶች የመግቢያ ቀዳዳ እየሆናቸው ያለ ጉዳይ ነው።

ይህንን ደብዳቤ እንድጽፍም ያነሣሣኝ በሐመር መጽሔት ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ሐምሌ /ነሐሴ ፳፻ ዓ.ም ከላይ በጠቀስኩት ርእስ ሦስቱ የቃለ መጠይቅ ተጋባዦች የሰጡት አስተያየት ነው። እያንዳንዳችን ስለመዝሙሮቻችን መስተካከል ድርሻ ሊኖረን ይገባል። በተለይ መምህር በየነ ድንቁና መምህር ሐዲስ ትኩነህ እንዳሉት መዝሙሮችን የሚገመግም አካል አልተቋቋመም እያልን ገደል ውስጥ እየገባን መሆናችንን ልናውቅ ያስፈልጋል።

ለዚህ ደግሞ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን ልጆች በማስተባበርና ከላይ እስከታች /ሰንበት ት/ቤት/ ድረስ ያለውን መዋቅር በማጠናከር መሥራት የቤተ ክህነቱ ሓላፊነት ነው። ምክንያቱም ዘማርያኑም ሆኑ ሌሎች ከዚህ ውጭ አይደሉምና ነው። እግዚአብሔር ዓይነ ልቡናችንን አብርቶ በአንድ አሳብ ተጉዘን ለሰማያዊት ኢየሩሳሌም ያብቃን።፨

*አሳየ ዓለማየሁ /ከከፋ ዞን ጊምቢ ወረዳ /*
*ዲ/ን ዳንኤል ሐጐስ /ከአርባ ምንጭ ግቢ ጉባኤ/*
*አቡቀለምሲስ /ዘደብረ ዘይት/*
*ስንታየሁ ስሜ /አ.አ./*

## የበኩላችንን እንወጣ

ሐመሮች እንዴት ናችሁ? ከሁሉ አስቀድሜ እግዚአብሔር በሥራችሁ ብርታትን ይስጣችሁ እላለሁ። ዛሬ መጀመሪያ የሆነችኝን ደብዳቤዬን እንድጽፍ ያስገደደኝ ጉዳይ ምን መሰላችሁ፤ ነገሩ እንዲህ ነው።

አንድ ቀን ከአንድ ቪዲዮ ቤት የአማርኛ ፊልም ተከራይተን ቤት ውስጥ ስናይ፤ የፊልሙ አጠቃላይ ይዘት ሃይማኖታዊ ሆኖ አገኘሁት። መሐል ላይም «በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኦርቶዶክስንና የእርሷ የሆነውን ሁሉ ማጣጣል» በሚለው መርሐቸው መሠረት፤ የተደበቀ ዓላማ ያላቸው አካላት ቆብ ጠበል ያላቸውን አመለካከት ሽፋፍነው ለማስቀመጥ ሞክረዋል። ይህ ነገር ለየዋሃን እውነት እንዳይመስል፤ እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚንም በመጠቀም እየተካሄዱ ያሉ ዘመቻዎች መኖራቸውን ለሕዝበ ክርስቲያኑ አሳውቁ እላለሁ። ሁላችንም የበኩላችንን እንወጣ። ዘመን ዘመንን ሲተካ ኦርቶዶክሳዊ ማንነታችንን መጠበቅ ግን የሁላችንም ሓላፊነት ነው።፨

*ከጂ.ዋይ.*
*ከደብረ ብርሃን*

## ለንስሐ ይቅረቡ

በሐመር ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፬ ላይ «የሃይማኖተ አበው ሚጠት /መመለስ/ የእርያ እጥበት» በሚል ርእስ የቀረበውን ጽሑፍ አነበብኩት። ጽሑፉ እጅ አሳጥሮ፣ አፍ አስይዞ በአግራሞት የሚያስደምም ቢሆንም «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር «ከሺሕ ዓመት በፊት የነበሩ የነጠሩ አባቶቻችንን ስም በመታሰቢያነት ይዞ ሲከተል የነበረ ማኅበር መሆኑን ስንረዳ በስም ብቻ የሚጠቀም ያለአንዳች ፍሬ የቆመ በለስ /ሉቃ.፲፫፥፮-፱/ መሆኑን ነው የተገነዘብነው። ይልቁንም በለሷ የራሷ አለማፍራት ሳያንስ በየጊዜው በሚነፍሰው ነፋስ እየተገለባበጠች የፀሐይ ብርሃንን በመጋረድ ሌሎቹን ተክሎች /ምእመናንን/ ያለ ፍሬ በማስቀረቷ በደሏ የከፋ ነው። ተጠቃሹ «ማኅበር» ብዙ በጎችን ወስዶ ወደ ፍየሎች መንጋ ጨምሯል። እኔ ደፍሬ አስተያየት ልሰጥ የምችለው በማኅበሩ የልመለስ ጥያቄ ላይ ሳይሆን የዚህ ማኅበር አባል ሆነው ሳያውቁ በስሕተት፣ አውቀው በድፍረት ዓላማውን ያራምዱ የነበሩ ሁሉ ለንስሐ ይቀርቡ ዘንድ ልባቸው፣ እንዲነሣሣ ነው። በተረፈ ጽሑፉ ከሃይማኖተ አበው ብቻም ሳይሆን በዚህ ዘመን በዘመቻ ከተነሡት «መነኩሴና ባሕታዊ» ነን ከሚሉ አስመሳዮችም ጭምር እንድንጠነቀቅ ያስገነዘበናልና ምስጋናዬ የላቀ ነው።፨

*ጸጋዬ ዘውዴ /ወልድያ/*
*ዲ/ን አበበ መንግሥቴ /ቆቦ/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ከምስጋና ሌላ ምን እንበላችሁ?

የ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ሐመረ ተዋሕዶን እንዳስነበባችሁን የ፳፻ ዓ.ም ሐመረ ተዋሕዶን በእ ግዚአብሔር አጋዥነት ላስነበባችሁን አዘጋጆች በዝግጅቱ ለተሳተፋት፣ በሐሳብና በጸሎት ለተባበሩት ሁሉ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ርስት አያሳጣቸውና ስለኀት መቷ ከምስጋና ሌላ ምንም የምለው የለኝም:: በዚህ አገልግ ሎታችሁ በርትታችሁ እንድትቀጥሉ ሁሌም የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አይለያችሁ::

በተረፈ በሐመር ፲፮ኛ ዓመት ላይ ፫ እና ፬ እትም «በጅሮ አችን ...» በሚል ርዕስ ስለጅማ ሀገረ ስብከት ያቀረባችሁት ዘገባ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ይህ እግራችሁ ሌሎች ሀገረ ስብከቶ ችንም ቢደርስ በጣም ጥሩ ነው::✤

*ገ/ሰንበት ወ/ጻድቅ*
*ከወላይታ ሶዶ*

## የእኛ ማንቀላፋት ምን የሚሉት ነው?

ውድ አዘጋጆች ሐመረ ተዋሕዶ ፲፱፻፺፱ እና ፳፻ ዓ.ምን ጓደኞቼ አውሶኝ እያነበብኩ ነው ብዙ ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር በአ ክራሪ ሙስሊሞች በአጋሮ ጅማ ክርስቲያኖች ላይ ስለደረሱት አሰቃቂ ድርጊቶችና ሌሎችንም በዚህ ዙሪያ ያሉትን ጉዳዮች አንሥተን እንነጋገራለን:: ይህንን የአክራሪ እስልምናን እንቅስቃሴ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያወቀው ትላንት ከጅማው ጭፍ ጨፋ በኋላ ነው:: እነሱ ሀገረ እግዚአብሔር የተባለችው ኢትዮ ጵያን ታሪኳን ለመለወጥ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለና በዕቅድ እንደሚንቀሳቀሱ አለ መገመት ሞኝነት ነው:: ስለዚህ የእኛ ማንቀላፋት ምን የሚሉት ነው? ቤተ ክህነትስ ቢሆን ለም ንድነው በየአጥቢያው የደረሰውን የወገ ኖቻችንን ስቃይ በተመለ ከተ ትኩረት ሰጥቶ ያላወያየን? እናንተ ግን እየሠራችሁ ያለው ሥራ የሚያኮራ ነውና ልትበረታቱ ይገባል::

በመጨረሻም ዛሬ ዛሬ አብዛኛው ሰው ከማንበብ ይልቅ ወደ ቪሲዲው እያደላ ስለሆነ ዋና ዋና ነጥቦችን በመምረጥ በዚሁ መልኩ ብታቀርቡልን መልካም ነው እያልኩ በጅማ ሀገረ ስብከት ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም የሀገራችን ክፍሎች በአሕዛብ እንቅ ስቃሴ ጫና የሚበዛባቸውን አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን ለመርዳት በሀገር ቤትና በውጭ ያሉ ባለሀብቶች አንድ ማኅበር ቢያቋቁሙና እኛም እንደአቅማችን አጋርነታችንን ብናሳይ መልካም ነው እላለሁ::✤

*ማንደፍሮ ጫላ*
*ወላይታ ሶዶ*

## እንግዳ ሲሰነብት ባለቤት ይሆናል

በሐመር ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፪ እና ቁ.፫ በእናስተዋወ ቃችሁ ዓምድ በጅማ ሀገረ ስብከት ስለአለው አሳዛኝና አሰቃቂ ሁኔታ ሲታስነብቡን ዘጋቢዎቹ በአካል እኛ ደግሞ ካለንበት ሆነን በመንፈስ እን ጓዝ ነበር:: ጽሑፉ ልብ የሚነካ ነበር:: በእ ውነቱ ይህ ችግር የጅማ ሀገረ ስብከት ብቻ ሳይሆን የማንኛውም ክርስቲያን ችግር ነውና:: ሁላችንም ከጐናቸው ልንቆምና ያን ቦታ ዘወትር በጸሎት ልናስበውም ይገባል:: ጉዳዩ እንግዳ ሲሰነብት ባለቤት ይሆናል ከሚባለውም በላይ ነውና ሁላችንም በአ ጽንኦት ልንከታተለው ግድ ይለናል::✤

*መ/ር ዓለሙ በላይ /ዳንግላ /*
*ዲ/ን ሰሎሞን ጌታቸው /ጉንደ ወይን/*

## ወደ ፍጹም ክህደት እንዳይገቡ

ሐመሮች እንደምን ሰነበታችሁ? አገልግሎታችሁን እግዚ አብሔር ይባረክ:: እንድጽፍላችሁ ያነሣሣኝ «መዝሙራችን ወዴት እያመራ ነው?» በሚለው ዓምድ ያቅረባችሁት ቃለመ ጠ ይቅ ነው:: መዘምራኑ የሚፈጽሟቸው ስሕተቶች ጉልህና የሚያ ሳዝኑ ቢሆንም የትምህርት ማነስና የንዝህላልነት ውጤቶች ብቻ ይመስሉኝ ነበር:: ነገር ግን ዲ/ን አሸናፊ የተባለው ዘማሪ «ድንጋይና ድንጋይ ሲጋጭ እንኳ ከቅዱስ ያሬድ ዜማ አይወ ጣም» ያለው በእጅጉ አስገርሞኛል:: አላወቀውም እንጂ ይህ ፍጹም ክህደት ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ዜማ አንድና የተደባለቀ ነው ከማለቱም በላይ ከቅዱስ ያሬድ በፊት ድንጋዮ ችም ስለተጋጩ፣ ዜማም ስለነበረ ... የተለየ የመላእክት ምስጋና መኖሩን፣ መላእ ክትም ለቅዱስ ያሬድ ማስተማራቸውን ... ሁሉ ክዷል ማለት ነው:: እኔንም ያሳዘነኝ ከሙዝሙሩ መበላሸት ይልቅ ለስሕተታቸው መከራከሪያ እየያዙት ያለው ፍልስፍና ነው:: ከዚህም በፊት አንድ ሰው መጽሐፍ ላይ በተደረገ ሌሎችን የማናናቅ ሒደት ክህደትን አስተውያለሁ:: ስለዚህ እባካችሁ በድፍረትና ባለማወቅ መናገር ለፍጹም ክህደት የሚዳርግ መሆኑን ዐውቀው እንዲጠ በቁ ከእልህም ይልቅ በማስተዋል ወደ ማድ መጥ እንዲመለሱ መልእክቴን አድርሱልኝ::✤

*ዲ/ን ይርጋለም አሻግሬ*
*ከባሕርዳር*

---

ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው የተከበራችሁና የተወደዳችሁ አንባብያንና ተሳታፊዎቻችን አስተያየቶቻችሁ፣ ግጥሞቻችሁ፣ ጥያቄዎቻችሁና ጽሑፎቻችሁ ደርሰውናልና እናመሰግናለን:: ጽሑፎቻችሁን እንደቅደም ተከተላቸውና ወቅታዊነታቸው በተራ ለማስተናገድ እንሞክራለን:: እናንተ ግን በተሳትፎአችሁ ቀጥሉበት:: ኡራኤል ለማ /አ.አ/፣ ዘሪቱ ዋቆ /አዋሳ/፣ ዲ/ን ሣህለ ሚካኤል /ሶያማ/፣ ዲ/ን ጋሻሁን ወ/ሚካኤል /አ.አ/፣ ዲ/ን ኃ/ገብርኤል አየለ /አ.አ./፣ ስንታየሁ ጌታሁን /አክሱም/፣ ክፍለ ሚካኤል እንዲህ ነው /ባሌ/፣ ብንያም አሰፋ /ጎንደር/፣ ዲ/ን ንጉሤ ታደሰ /አሰላ/፣ ወንድምአገኘሁ በኃይሉ /ሱማሌ ክልል/፣ ዘሩባቤል ዐቢ ይ /ጅጅጋ/፣ መ/ርት ድርቤ /ይርጋ ጨፌ/፣ ተማሪ ደስታው አያሌው /ጎንደር መምህራን ኮሌጅ/::


አቡሻኽር

አዲስ መጽሐፍ
በገበያ ላይ

የኢትዮጵያ የዘመን ቀመር
- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ጥበባትና ልዩ ባሕርያት
- የ፲፫ኛ ወራችን የጳጉሜን የዘመን ስሌት
- የአጽዋማትና በዓላት ስሌት /ባሕረ ሐሳብ/
- የቤተ ክርስቲያን ሒሳብና መንፈሳዊው ሳይንስ

በዲ/ን
ኢንጂነር አብርሃም
ጤናው
0910 00 08 38/
0918 77 49 65

በማኅበረ ቅዱሳን፣
በሜጋ
እና
በሌሎችም
ማከፋፈያዎች
ያገኙታል::




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ከጸሎትና ከጾም በቀር አይወጣም»

/ማቴ.፲፯÷፳፩/

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን



ከደብረ ታቦር ተራራ ግርጌ ዘጠኙ የጌታ ደቀመዛሙርት ታላቅ ፈተና ገጠማቸው፡፡ አንድ ሰው ስለ ልጁ ሕመም /ደዌ/ ተማጸናቸው፤ ከሰይጣን እስራት እንዲፈቱለት፣ ነጻነት እንዲሰጡት፣ ሰላሙን እንዲመልሱለት፣ ከሰው እኩል እንዲያደርጉት፡፡ ያንን ለማድረግ ቢሞክሩም ግን ለሐዋርያት እንዳሰቡት አልቀናቸውም፡፡ በብላቴናው ያደረው የሰይጣን አገዛዝ አሁንም ጸንቶበት ነበር፡፡ ይህ መንፈስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ለነበረው ሕዝብና ለጻፎች መከራከሪያ ሆኖ ነበር፡፡

በዚህ ብርቱ ክርክር መሐል ጌታችን ምስጢረ መንግሥቱን ከገለጠላቸው ሦስቱ ሐዋርያት ጋር መጣ፡፡ ስለምን እንደሚከራከሩም ጠየቃቸው፡፡ የዚያም ብላቴና አባት ተናገረ፤ እንዲህ ሲል፡- «መምህር ሆይ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼአለሁ፤ በያዘውም ሥፍራ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋም ይደፍቃል፤ ጥርሱንም ያፋጫል፤ ይደርቃልም፡፡ እንዲያወጡለትም ለደቀመዛሙርትህ ነገርኳቸው፤ አልቻሉምም፡፡» /ማቴ.፲፯÷፲፬-፲፰፤ ማር.፱÷፳/ ጌታችንም እርሱ ከእነርሱ ጋር በአካል ባልነበረበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ለምእመናን መድኃኒትን መስጠት ባለመቻላቸው ወቀሳቸው፡፡ ያ መንፈስ ግን ለጌታ ተገዛ፡፡ ታዞም ወጣ፡፡ ያም ብላቴና ጤናማ ሆነ፡፡

በዚህ አጋጣሚ ሐዋርያት በምስጢር ለጌታ ያነሡት አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ነበር፤ «እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለምን ነው?» ጥያቄው የሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ሐዋርያት የገጠማቸውን ፈተና ያዩ በየዘመኑ የተነሡና የሚነሡ ወገኖችም ነው፡፡ የጌታችን መልስ ግን «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፡፡ እውነት እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፡፡ የሚሳናችሁ ነገር የለም፡፡ ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም» የሚል ነበር፡፡ /ማቴ.፲፯÷፳/

## አብሮ አደግ ጋኔን

ጠላታችን ሰይጣንን ለማሸነፍ በእምነት የሚፈጸም ጾም ጸሎት ሙቼም ቢሆን የምንጠቀምበት ዕቃ ጦራችን ነው፡፡ በተለይ ግን ጌታችን «ይህ ዓይነት» /ማቴ.፲፯÷፳፩፤/ «ይህ ወገን» /ማር.፱÷፳፱/ በማለት የገለጸውን ሊቃውንቱ ደግሞ «አብሮ አደግ ጋኔን» በማለት የተረጐሙትንና ለይተው የነገሩንን የሰይጣን ውጊያ በአሸናፊነት ለመወጣት ጾም ጸሎት አስፈላጊያችን ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሠፀው፤ በዚህ ብላቴና ላይ ያደረው መንፈስ አሠራር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የብላቴናው አባት ሲያስረዳ የሚጥል /ቦታ ሳይመርጥ በእሳት በውኃ ላይ/፣ አረፋ የሚያስደፍቅ፣ ጥርስን የሚያስፋጭ፣ የሞተ አስመስሎ የሚያደርቅ ነው፡፡ /ማር.፱÷፲፰/ ጌታችን ምን ያህል ጊዜ በዚህ መንፈስ እንደተገዛ የብላቴናውን አባት ሲጠይቀው «ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው» በማለት መልሷል፡፡ ይህም መንፈሱ ለረጅም ጊዜ መቆየቱን /አብሮ አደግነቱን/ ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም «በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሰቃያል» በማለት እንደገለጸው ጊዜ እየመረጠ /እየለየ/ እንደሚያሰቃየው ነግሮናል፡፡ /ማቴ.፲፯÷፲፭/ የዚህ አብሮ አደግ ጋኔን ጸባይ ይህ ብቻ ሳይሆን ጌታችንን «ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን» /ማቴ.፰÷፳፱/ እያሉ ሲጮኹ ከነበሩ ርኩሳን መናፍስት በተለየ የማይናገር /ዲዳ/ መንፈስ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እንዲህ ያለው መንፈስ ላደረበት ሰው ብቻ ሳይሆን ለቤተሰብ ሁሉ ፈተና ይሆናል፡፡ የዚህ ብላቴናም አባት ልጁ ከባህር እንዳይወድቅ በእሳት እንዳይቃጠል በመጠበቅ ይንገላታ ነበር፡፡

ዛሬም ድረስ በብዙ ገጠመኞቻችን እንደምናየው በሕፃንነት ወራታቸው ለዕድሜ ባሕርያቸው የማይስማማ ክፉ ሥራን ሕፃናት እንዲፈጽሙ በማድረግ በኃጢአት ለማሳደግ ካልሆነም በስቃይ ለማኖር አጋንንት ይተጋሉ፡፡ እነዚህ ሕፃናት አድገው ራሳቸውን በውቀው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ በውስጣቸው ያለ የሰይጣን መንፈስ የዕጣኑን ሽታ፣ የጧፉን ብርሃን፣ የቤተ ክርስቲያን የደጇን አፈር፣ ጠበሏ፣ እምነቷ፣ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳቷ ሲሸተው፣ ሲያይ ወይም በሰውየው በኩል ሲነካ ይታሰራል፤ ይቃጠላል፤ ይወድቃል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ በመንካቱ ወደ እርሱም ርስት በመግባቱ የሚገጥመው ቅጣት ነው፡፡ የካህናቱ አልባሳትና ጥላ ሁሉ ለእርሱ እሳት ነው፡፡

የዚህ መንፈስ ፍጹም ሽንፈት ግን ይህ አይደለም፡፡ ብዙዎቻችን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ወድቀው በአጋንንት እስራት ሲሰቃዩ ከምናያቸው ሰዎች ሁሉም ፈውስን ሲያገኙ አይታይም፡፡ ከላይ በጠቀስነው ብላቴና ላይ ያደረው መንፈስ በደብረ ታቦር ተራራ ግርጌ ቢወድቅም፤ በሐዋርያቱ ፊት ቢንፈራፈርም፤ ፍጹም ማሸነፍን ግን አላሸነፉትም ነበር፡፡ ለዚህም ነው ሐዋርያት «ለምን አልቻልንም» በማለት የጠየቁት፡፡

እኛም በጠበል ቤቶቻችን ወይም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወድቆ ሲቃጠል የምናየው መንፈስ አንዳንዴ ሲፎክርብን፤ «አሳድጌ አሳድጌ አለቅም» እያለ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሲዝትብን ሁሉ ይስተዋላል:: አንዳንዱንም መንፈስ የማይሸነፍ አድርገን በመውሰድ ተጠቂዎችን ተስፋ እናስቆርጣለን::

ጌታ ግን ቀድሞ እንደተጠቀሰው ለዚህ ዓይነቱ አብሮ አደግ መንፈስ ሽንፈት በግልጽ ከእምነት ጋር የሆነ ጾም ጸሎት እንደሚያስፈልግ ነግሮናል:: እንዲህ ያለውን መንፈስ ከራሳችን ወይም ከወንድሞቻችን ብዙ ጊዜ ለማስወጣት ብንታገልም ታማሚው፣ አዳኞች ሆነን የምንቀርበውም ለማሸነፍ በማሰብ ከእምነት ጋር ጾምና ጸሎትን ስለማንይዝ ቢወጣም ተመልሶ እየገባ ለነፍስም ለሥጋም ደዌ መሆኑን ይቀጥላል:: ከዚያም ያ ሰው በጥንቆላ በማመን ወይም በኑፋቄ በመመላለስ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወይም ከምእመናን ሲርቅ በሥጋ ማሰቃየቱን፣ በሰው ፊት ማዋረዱን ሊተወው ይችላል:: ይህም ለዚህ ሰው፣ ለቤተሰቦቹ ወይም ለሌላው ተመልካች የተፈወሰ መስሎ ይታያል:: ያ የሆነው ግን ሰይጣን ከሕፃንነቱ ጀምሮ ያደረበት ዓላማ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወግቶ ለማስወጣት በመሆኑ ዓላማውን ሰውየው በራሱ ፈቃድ ከፈጸመለት፣ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን መርገም ከጀመረ በሥጋ ማሰቃየቱን ሊተውለት ይችላል:: ውጊያውንም ያቆማል:: ምርኮኛን ወደ ጦር ሜዳ እንዳይመለስ፣ ደግሞም እንዳይዋጋ ይጠብቃል እንጂ ማንስ በቅጽሩ አስገብቶ ይወጋዋል? ይህ በሰው ሥርዓትስ ያለ አይደለምን?

## የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር

ጌታችን ሰይጣን የሚሸነፍበት ዕቃ ጦር /ጦር መሣሪያ/ እምነት፣ ጾምና ጸሎት መሆኑን ለሐዋርያቱ ነገራቸው:: ለምእመናን ከምንም በላይ ኃይል የሚሆነው እምነት ነው:: እምነት ግን ህልዎተ እግዚአብሔርን መቀበልና ፈቃዱን መጠበቅ ብቻ አይደለም:: ሰይጣንን ለማሸነፍ ራሱን ሰይጣንን ለሰው ልጆች ሕይወት ጥፋት በትጋት የቆመ መንፈሳዊ ባላጋራ /፩ኛጴጥ.፭÷፰/፣ ጠላት /ማቴ.፲፫÷፴፰/ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል:: ጠላት እንዳለን ካላመንን ለውጊያ አንወጣምና:: ጌታም ለምእመናን ብርቱ ጠላታቸው ሰይጣን መሆኑን በጉልህ ሲገልጥ «ይህን ተራራ» /ማቴ.፲፯÷፳/ ብሎታል:: ቅዱስ ጳውሎስም «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፤ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር፤ በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ::» /ኤፌ.፮÷፲፪/ ብሏል:: ስለዚህ በቅድሚያ የሰይጣንን ጠላትነት አምኖ፤ «እክህደከ» በማለት ግንባርን ለይቶ፤ የመድኃኒታችንን ስም በመያዝ መዋጋት ለአሸናፊነት ያበቃል:: ከላይ በተጠቀሰው ታሪክ ላይም ጌታ ሐዋርያቱን «ስለእምነታችሁ ማነስ ነው::» ማለቱና የብላቴናውንም አባት «ለሚያምን ሁሉ ይቻላል» /ማር.፱÷፳፫/ በማለት መመለሱ ለአሸናፊነት እምነት ቁልፍ ሚና እንዳለው ያስረዳናል::

> በዚህ ትሩፋታችን እንደ ረቂቃን መላእክት በእግዚአብሔር አጋዥነት ክፉ መንፈስ የሆነውን የሰይጣንን ፍላፃ እንቋቋማለን:: መንፈሳዊ ውጊያው ተሸንፎ ከተሰደደ መንፈስ ጋር በመሆኑና ጦርነቱ የሰማያዊው ጦርነት ቀጣይ ክፍል በመሆኑ ካሸነፉ ቅዱሳን መላእክት ጋር በሃይማኖትም በግብርም መተባበር ያስፈልጋል::

ስለጸሎት ጉልበትነትም «ወደፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» በማለት ጌታ ሲያስተምር ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ደግሞ «ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች» ብሎናል:: /ያዕ.፭÷፲፮/

ጾም ደግሞ ከዚህ የጸሎት ትጋት ጋር ተዋሕዶ ተራራን የሚያፈልስ አቅም እንደሚሰጥ ጌታ «ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም» ባለው ቃሉ ግልጽ ሆኗል:: ጾም ሥጋን የሚያደክም ቢሆንም መንፈሳዊ ኃይልን በእጅጉ የሚያጐናጽፍ ነው:: ለመንፈሳውያን የሥጋ ድካም የሽንፈት ምክንያት ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሚገኘውን የኃይል ጸጋ የሚያድል ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ» /፪ኛቆሮ.፲፪÷፲/ ደካሞችን የእግዚአብሔር መንፈስ ያግዛቸዋል:: /ሮሜ.፰÷፳፮/ ይለናል:: ስለዚህ ጌታችን እንደነገረን ከእምነት ጋር የምንይዘው ጾም ጸሎት ጠላትን ድል የምንነሳበት ዕቃ ጦራችን ነው::

## ጾም ጸሎት ለምን

በመንፈሳዊ ተጋድሎ ውስጥ ጾምና ጸሎት እንደ ዕቃ ጦር የተመረጡበት ምክንያት አለ:: አስቀድሞ ሰይጣን በዓለመ መላእክት ከቅዱሳን መላእክት ጋር ተዋግቶ ወደ ምድር እንደተጣለ ቅዱስ መጽሐፍ ሲያስረዳ «በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፤ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፤ አልቻላቸውምም፤ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም፤ ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ:: ወደ ምድር ተጣለ» ይለናል:: /ራእ.፲፪÷፯-፱/ እነዚህ ቅዱሳን መላእክት ሰይጣንን ያሸነፉት በራሳቸው ኃይል አይደለም:: በረድኤተ እግዚአብሔር እንጂ:: ቅዱሳን መላእክት «ዘወትር የእግዚአብሔርን ፊት ያያሉ»፤ /ማቴ.፲፰÷፲/ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና የሚመጣውም፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ ያለው አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም» /ኢሳ.፮÷፪፣ ራእ.፬÷፰/፤ «ስሜም በእርሱ ስለሆነ ...» /ዘጸ.፳፫÷፳፩/ ተብሎ የተነገረላቸው የእምነትና የምጠስጋና ወገኖች ናቸው:: ሰዎችም ቅዱሳን መላእክት ያሸነፉትን የሰይጣን መንፈስ ድል ለመንሳት በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት ዘወትር ማየት፣ ስመ አምላክን መሸከም የግድ የሚያስፈልግ ነው:: ሰይጣንን በራሳችን ጉልበት ልንረታው አንችልም:: ጸሎት ረድኤተ እግዚአብሔር የምናቀርብበት፣ ለተሰጠንም ጸጋና ረድኤት ምስጋና የምናቀርብበት ሥርዓት ነውና::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በውጊያ የቅዱሳን መላእክትን ኃይል ገንዘብ ለማድረግ ጾም ወሳኝ ነው:: ከምድር /ለሥጋ/ የሆነውን እህል ውኃ ሳንቀምስ ያለምድራዊ መብልና መጠጥ እግዚአብሔርን በማመስገን ያለ እህል ውኃ ከሚኖሩ መላእክት ጋር አንድ እንሆናለን:: በዚህ ትሩፋታችን እንደ ረቂቃን መላእክት በእግዚአብሔር አጋዥነት ክፉ መንፈስ የሆነውን የሰይጣንን ፍላፃ እንቋቋማለን:: መንፈሳዊ ውጊያው ተሸንፎ ከተሰደደ መንፈስ ጋር በመሆኑና ጦርነቱ የሰማያዊው ጦርነት ቀጣይ ክፍል በመሆኑ ካሸነፉ ቅዱሳን መላእክት ጋር በሃይማኖትም በግብርም መተባበር ያስፈልጋል:: ቅዱስ መጽሐፍ ያንን ሲገልጽ «ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት ... ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሔደ» ብሎናልና:: /ራእ.፲፪÷፲፫-፲፯/ ስለዚህ በዚህ ጦርነት ከመላእክት ጋር በኃይል አቻ ሆነን እንድንገኝ በጾም ከሥጋ ፍትወት፣ ከስስት ጾድተን፤ በምጽዋት ሌላውን /ባልንጀሮቻችንን/ ለማገልገል መብረር አለብን:: በጸሎትም ደካማ መሆናችንን በማመን፣ ለበደላችን ይቅርታን በመጠየቅ በነፍስ ቅድስናችን አቻ ለመሆን መትጋት ያስፈልጋል:: እነዚህ ሁለቱ መልካም ሥራዎች ከምድር ከፍ ከፍ የሚያደርጉንና በጠላታችን ላይ ኃይል የሚሰጡን ሁለት አክናፈ ጸጋዎቻችን ይሆናሉ:: ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ ለአርባ ቀናት በጾመ ጊዜም መራቡን አይቶ ሰይጣን እንዲበላ በማግባባት ለመፈተን ሲሞክር «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም» ባለው ቃሉ ረትቶታል:: በዚህም ጾምን መስበር ለአጋንንት ደስታ እንደሚሰጣቸው፣ መጾም ደግሞ ድል የሚሸነፉበት መሣሪያ መሆኑን አውቀናል:: /ማቴ.፬÷፬/

ጾም ጸሎት አብሮ አደግ ለተባለ ከላይ ለጠቀስነው ጋኔን ብቻ ሳይሆን ሰውን በተለያየ መንገድ ለሚዋጉ ርኩሳን መናፍስት ሁሉ ማሸነፊያ ኃይል ነው:: በሥጋችን በማደር፣ በቤተሰባችን መካከል በመመላለስ፣


ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# መዝሙራችን ወዴት

## ያሬዳዊ ዜማን ማስጠበቅ ያለበት በተዋረድ ከላይ እስከ ታች ያለው የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር ነው



መሪጌታ ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ

*ከዚህ ቀደም በተከታታይ በወጡ እትሞች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ተዘጋጅተው እየ ወጡ በገበያ ላይ ስለሚውሉ መዝሙሮች የተለያዩ ወገኖችን አስተያየት ስናቀርብ መቆየታችን ይታወሳል። በዚህ እትም ደግሞ ከአንድ የዜማ ሊቅ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ እና የመጽሔቱን ዋና አዘጋጅ አስተያየት እናቀርባለን።*

*ሐመር፡-* ያሬዳዊ ዜማ ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው?

*መሪጌታ ዓምደ ወርቅ፡-* ይህንን ጥያቄ በመልስ ለመግለጥ «ያሬድ» የሚለውን ስብ ራይስጣዊ ቃል ወደ ግእዝ መመለስና ግእዙንም ወደ አማርኛ መተርጎም ግድ ሆኖ ይገኛል።

በዚህም መሠረት ያሬድ ማለት በግእዝ ቋንቋ ምላሹ ወረድ፣ ረደት ማለት ሲሆን፣ የአማርኛ ቋንቋ ትርጉሙ ደግሞ መውረድ፣ አወራረድ ማለት ነው።

የስሙን ትርጓሜ ይህንን ያህል ተረድ ተን ካወቅን ዘንድ ያሬዳዊ የሚል ወገናዊ ቅጥል ስለተሰጠው «ዜማ» ትርጉም ደግሞ በዝርዝሩም ባይሆን በጥቅሉ፣ በሰፊውም ባይሆን በጠባቡ፣ በረጅሙም ባይሆን በአጭሩ፣ በብዙውም ባይሆን በመጠኑ ጥቂት ልበል።

### ያሬዳዊ ዜማ ማለት

፩. ውሩድ /ዘወረደ/ እምሰማይ ማለት ከሰማይ የወረደ ምስጋና

፪. ስሙዕ /ዘተሰምዐ/ እም መላእክተ አዶናይ ማለት ከጌታ መላእክት የተሰማ ምስጋና

፫. ርኩብ /ዘተረክበ/ እምነ ሠለስቱ አዕዋፍ ማለት የአካል ሦስትነት፣ የድምፅ አንድነት ካላቸው ሦስት አዕዋፍ የተገኘ ስልት ያለው ጩኸታዊ ምስጋና፣ ተሰሚነት ያለው ማለት ነው።

የድርሰቱ ባለቤት የሆነው ራሱ ቅዱስ ያሬድም በአንክሮ በአስተዓጽቦ «ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እመላእክት ቅዱሳን እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር መልአ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ» በማለት ገልጦታል።

የዚህንም እውነታ ለማረጋገጥ አሥራው መጻሕፍትን፣ ድርሳናትንና ገድላትን ለማንበብ፣ አንብቦም ለመረዳት ማገላበጥ፣ በሙያው ጎዳና ተጉዘው ያለፉትን አባቶች ብሂልና መንፈሳዊ ታሪክ መስማት፣ ማዳመጥ ያስፈልጋል።

መጻሕፍትም ዜማ የሚለውን ጥሬ ቃል በየምዕራፋቸውና በየዐምዳቸው እንዲህ ይገልጡታል።

፩ አው እምቃለ አዕዋፍ ዘሠናይ ዜማሆሙ ጥበ.፲፩÷፳፫ /፲፯÷፲፯/

፪. ይሴብሕዎ በሠናይ ዜማ ወማሕሌት /ቀሌሚንጦስ/ ማለት ባማረ ዜማና ማሕሌት ያመሰግኑታል /ቀሌ/

፫. ኅብረተ ዜማ፡- የዜማ አንድነት /አርጋኖን/

፬. «ዜማ ግእዝ ወዕዝል ወአራራይ» /መጽ.ግንዘት/ ማለት «የግእዝ፣ የዕዝልና

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እያመራ ነው?

## «መዝሙራችንን ከችግሮቹ ተላቆ ሊሔድበት የሚገባውን ኦርቶዶክሳዊ ፍኖት ልናመላክተው ይገባል» ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ



ከሐምሌ/ነሐሴ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ዕትማችን ጀምረን በታተሙት ሦስት ተከታታይ ዕትሞቻችን አንባብያን መዝሙር ላይ ያላቸውን አሳብና ክርክራዊ ሒስ አቅርበን ነበር፡፡ ትንሽ ካቆየነው በኋላ ደግሞ ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞቻችን በዚህኛውም ዕትም ከመዝሙር ግጥምና ዜማ ደራስያን ከነገረ መለኮት መምህራን፣ ከዜማ ሊቃውንት፣ ከሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ እና ከአሳታሚዎች ጋር የተደረጉ ቃለ መጠይቆችን ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ ዕትም ደግሞ «ምን ቢደረግ ይሻላል?» የሚለውን ፍሬ ሐሳብ መሪ አድርጎ የመጽሔቱ ዋና አዘጋጅ ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ እንደ አንድ ተሳታፊ ይወያያል፡፡ ስለዚህም የዚህ ጽሑፍ አቋም እስካሁን በቃለ መጠይቅ እንደቀረቡት እንደሌሎቹ ሁሉ የአዘጋጁ እንጂ የማኅበሩ ወይም የመጽሔቷ እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡ የማኅበሩን አቋም ከማኅበሩ መልእክት ብቻ ይረዱ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

### ለመሆኑ ለምን ርእሰ ጉዳይ ሆነ?

ከቡራን የሐመር አንባብያን እስከ መጨረሻው በትዕግሥት እንደምታነቡት ብገምትም መጨረሻውን ሳታዩ ድምዳሜ ላይ እንዳትደርሱ እያሳሰብኩ ሐሳቤን ማቅረብ የምጀምረው ለምን ርእሰ ጉዳይ ሆነ ከሚለው በመጀመር ይሆናል፡፡

የመዝሙር ጉዳይ መነሣቱ ለምን አስፈለገ የሚሉም አይጠፉም፡፡ አንባብያን በተሳተፉባቸው የመጀመሪያዎቹ ጽሑፎችም ላይ «በዘማርያኑ ያለመደሰት፣ የመቅናት፣ አንዳንዴም እነርሱ ገቢ እንዳያገኙ የመመቅኘት» እና የመሰላቸውን ሁሉ በጽሑፍ የገለጹ ነበሩ፡፡ /ሐመር ኅዳር/ ታኅሣሥ ፳፻ ዓ.ም/፣ ገጽ.፲፯/ አንዳንዶቹ ደግሞ ዝግጅት ክፍሉ ሆነ ብሎ እነርሱን ለመተንኮስ እና በሌላም ምክንያት ይመስላቸዋል፡፡ እነዚህን የመሰሉ ሌሎች አስተሳሰቦችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የጽሑፉ ዓላማ ግን ይህ አይደለም፡፡ እስኪ ከአንድ ሁኔታ እንነሣ፡፡

የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ አቡነ ሰላማ /ፍሬምናጦስ/ ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ ሔደው ጵጵስና ተሹመው ተመለሱ፡፡ ሁለተኛውስ ለምን ከኢትዮጵያ አልሆነም? በዚያ ዘመን የነበሩ ነገሥታቱና አባቶችስ ሁኔታውን ለምን ታገሡት? በዚያ ዘመን የነበሩት አባቶቻችን በጊዜው ከነበረው የክርስትና ሕይወት ፍጹምነት የተነሣ ችግር እንኳ ላይመስላቸው ይችላል፡፡ አሁን ላይ ሆነን ስናስበው ግን አሁን ድረስ የዘለቁትን ችግሮች ከዚያ የመነጬ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም፡፡ የመዝሙር ችግርም ዛሬ ቀላል ሊመስለን ይችላል፡፡ ችግሩን አውቀን ካልፈታነው ግን በኋላ ለመፍታት የማይቻልበት ብቻ ሳይሆን አሁን ያለነውንም ዘላለም ተወቃሽ የሚያደርገን ሊሆን ይችላል፡፡ «ተቀምጦ የሰቀሉትን ቆሞ ማውረድ ይቸግራል» እንደተባለው፡፡

ከላይ የጠቀስኩትን አብነት ይዘን የቤተ ክርስቲያናችንን ሁለንተናዊ ይዘት የምናጤን ከሆነ ደረጃ በደረጃ ሊፈቱ የሚገባቸውን እጅግ ብዙና ውስብስብ ችግሮችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ባሉበትና ችግሮች መሆናቸውን እንኳ በአግባቡና በውል ባልተረዳንበት ጊዜ ሌሎች ችግሮችንን የምንጨምር ከሆነ ደግሞ ጉዳቱ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ችግሮቻችን ለመፍታት እንደ አንድ አማራጭ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ የሆነውና የመጀመሪያው እርምጃ በችግሮቻችን ዙሪያ መስማማት ነው፡፡ ካልተስማማን እንለያያለን፤ ከተለያየን ደግሞ እንጠፋለን፡፡ /በእነማን? እንዴት? . . . የዛሬ ጉዳዬ አይደለም፡፡/ ስለዚህ እንዳንጠፋ መስማማት፣ እንድንስማማም መወያየት፣ እንድንወያይ ደግሞ ደፍሮ ጉዳዩን ማንሣት አስፈላጊ ነበር፡፡

በርግጥ መስማማት እንዲህ ቅርብ ነገር አይደለም፡፡ ቢያንስ ግን ለመስማማት ቀዳሚ የሆነው መግባባት ላይ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ያሬዳዊ ዜማን ማስጠበቅ ...

የአራራይ ዜማ» በማለት ስልትና ዐይነት እንዳለው

፫. ዝብጠተ ክበሮ ወእንዚራ እለ ቦሙ ሠናይ ዜማ /መቃብ/ ማለት ያማረ ዜማ ያላቸው የእንዚራና የከበሮ ምት /ንዝርታ/ በማለት የዜማን ማንነት ይገልጣሉ።

*ሐመር፦ በአሁኑ ጊዜና ዘመን ስለሚወጡ መዝሙሮች ያለዎና የሚኖርዎ አስተያየት ምንድን ነው?*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* በእውነት እኔ በሙያዊ ሰብእናዬ መዝሙራት ከሚባሉት ስያሜዎቻቸው ጀምሮ አልቀበላቸውም። ምክንያቱም ብርሃነ ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ ቆሮንቶስ ክታቡ ፮፥፲፬-፲፮ ላይ ጽድቅን ከኀጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ደግሞም የሚያስተካክላት ማን ነው፤ ብርሃንንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅለው የሚያዋሕደው ማን ነው?

ክርስቶስን ከሰይጣን ጋር አንድ የሚያደርገው፣ የሚያስማማው፣ የሚያስተባብረው ማን ነው፤ ምእመናንንስ ከመናፍቃን ጋር አንድ ወገን፣ አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ የሚያደርጋቸው ማን ነው? ዳግመኛም የእግዚአብሔርን ታቦትስ እንደ ጣዖት ከጣዖት ጋር በጣዖት ቤት የሚያኖር ማን ነው፤ ሁለተኛ ቆሮ.፮፥፲፬-፲፮ ያለውን ከልብ በማስተዋል ነው።

መዝሙር ለሚለው ስሑት ስያሜያቸው ይህንን ያህል ካልኩ ወደ ምሳሌያዊ አቀራረጻቸውና አካላቸው ትምህርታዊ አባባል ልግባ በልዩ ልዩ ሕብረ ቀለም የተዋቀረ /የተነቀሰ/፣ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ሰብአዊ ጥበብ ፈጠር ጥርስ መንከስ፣ መጋጥ፣ መንጨት፣ መላጥ እንዳይችል በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በድርሳናትና በገድላት ቃላት ጉራማይሌነት ተሰኝተው ተገጥመው በመንፈሳዊ ዜማ ነፋስ ሳይሆን በዓለማዊ ዜማ ነፋስ የሚወዘወዙ ስመ መዝሙር ዜማዎች በዘመነ በልግ ዝናም በአረዳ ቦታ ላይ ከበቀለ፣ በነሐሴ ወር ጫፍ ከሚደርቅ ሙጃነት አልፎ ለቤት ክዳን የሚያገለግለውን፣ በጥቅምት፣ በኅዳር ወራት ደርሶ የሚታጨደውን ሰንበሌጥና ስንደዶ፣ ገርሳና ሰርዶ እንኳን ሊሆኑ አይችሉም። በድምፀታቸው ላይም የእግዚአብሔር መንፈስ የረበበበት አይደለም፤ ምክንያቱም የቅዱስ ያሬድን ዜማ ስልታዊ አጫጫህ የተከተሉ አይደሉምና።

ከዚህም በላይ መዝሙርን ዜማን ለመድረስ አረጋዊ መንፈሳዊ በመጽሐፉ /ድርሳን አምስት/ ላይ የዘረዘራቸው ከገድል ከትሩፋት የተነሣ የሚገኙ አሥራ ስድስት ሕዋጼያት ማለት መንፈስ ቅዱሳዊ ጉብኝታዎች /መኀብኛቶች/ የተፈጸሙለት፣ ያም ባይሆን በሙያው እውነተኛ በር ያለፈ መሆን አለበት።

ከገጽ ፳ የዞረ

ቅድመ ሁኔታዎች ተደርገው ከተቀመጡት ከሁለቱ ድልድዮች መካከል በአንደኛው ያላለፈ ሰው መዝሙርን መድረስ አይደለም ማዘጋጀት አይችልም።

እስኪ ይህ መንፈሳዊ አባት በመጽሐፈ ድርሳኑ ከገለጣቸው መንፈሳውያት ሕዋጼያት /ጉብኝታዎች/ ለአብነት ያህል ሁለቱን እንጥቀስ።

«ወቦ ዘትወዲ ውስተ ልቡ ዝማሬ» ማለት እግዚአብሔርን ማሰብ እግዚአብሔርን ማመስገን በልቡናው የምታሳድርበት ጊዜ አለ።

«ወቦ ዘትውህቦ አንብቦ ዘእንበለ ጽርዐት፤ ወትቶስሐ ሎቱ አንበዐ ወአስተጥዕም፤» /ድር.፭/

ማለት ዘወትር ያለማቋረጥ መጽሐፍን መመልከት እግዚአብሔርን ማሰብ የምታድለው የምትሰጠው አለ።

በአንብዐ ጸጋ ላይ አንብዐ ጸጋን /በእሴተ አንብዕ ላይ እሴተ አንብዕን/ እንዲታከልለት ጣዕመ ዝማሬ እንዲሰጠው የምታደርገው አለ በማለት ያስተምራል።

በእነዚህ መንፈሳውያት ጉብኝታዎችና በሙያው ያልደከመና ያልጣረ ሰው ዓለማዊ ነገርን ከመጮህ አልፎ ዘማሪ ሊባል አይችልም።

*ሐመር፦ በያሬዳዊ ዜማ ማመስገን ጥቅሙ ምንድን ነው?*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* እግዚአብሔርን በያሬዳዊ ዜማ የማመስገን ጥቅሙ «መልአከ ዘበምድር» ማለት ምድራዊ መልአክ ለመሆን፣ ዜማው መልአካዊ፣ ጽርሐ አርያማዊ ስለሆነ በመጨረሻው የዋጋ ክፍያ ጊዜ የሰማያዊ ዜማ አገልግሎት ዋጋን ለመቀበል ነው።

*ሐመር፦ የእስክንድርያና የሶርያ አብያተ ክርስቲያን ይህንን አያውቁም፤ እንዲህ ከሆነ ለእኛ ቤተ ክርስቲያን በያሬድ ዜማ የመገልገል ሥርዐት የሚያስገኘው መንፈሳዊ ዋጋ ምንድር ነው።*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* እውነት ነው የእስክንድርያና የሶርያ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን አያውቁም። በዚህም አይገለገሉም፤ አያገለግሉምም። የእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ለዚህ ጸጋ ብቸኛ የተለየች ባለቤት እንድትሆን በቅዱስ ያሬድ አማካይነት ከፈጣሪዋ ታድላለች። ምእመናዊት የነበረችና የሆነች ታላቂቱ ኢትዮጵያ እጆቿን ልቡናዋን፣ እጆቿን ሥጋዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋ እንደነበር በባለሚሉ ዳዊት አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮላታልና። መዝ.፷፯፥፴፩ ያለመመጸደቅ በዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን የመለመን ሙከራዋ ጸጋውን አብዝቶ እንደሰጣት ከልብ ያምኗል እንጂ ለምን ሆነ ወደሚለው ኑፋቄያዊ ጥያቄ ልንገባ አያሻም።

*ሐመር፦ ዜማ የኀጢአትና የጽድቅ ጉዳይ አይደለም የሚሉ አሉ። ዜማ ባያውቁት የሚያስፈርድ ቢያውቁት ደግሞ የሚያጸድቅ ነው?*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* ዜማ ተምረው፣ አውቀው በትሕትና እግዚአብሔርን ቢያገለግሉበት የግብረ ክርስትናን ዕጥፍ ድርብ ዋጋ ያሰጣል። ባያውቁትም እንደ ሕጉ እንደ ትእዛዙ ከተጓዙ ዋጋው ታናሽ አይደለም። መድረካዊ የማስተማር ጸጋ /ወንጌልን የመስበክ ሀብት/ ያለውም ቢሆን እንደ ሕጉ እንደ ትእዛዙ ካልተጓዘ ከፍርድ ከፍዳ ነጻ አይሆንም።

*ሐመር፦ ያሬዳዊ ዜማን መጠበቅና ማስጠበቅ ያለበት ማን መሆን አለበት?*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* ይህንን ሰማያዊ ጸጋ የመጠበቅና የማስጠበቅ ሓላፊነት ያለበት ለዚህ መንፈሳዊና መልአካዊ፣ ሰማያዊና አምላካዊ ሀብተ ዜማ ባለቤት የሆነችው ጥንታዊቷ ብሔራዊቷ፣ ታሪካዊቷ፣ ኦርቶዶክሳዊቷ፣ ሐዋርያዊቷና ሲኖዶሳዊቷ ቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደራዊ አካል /ከላዕላይ መዋቅር እስከ ታሕታይ መዋቅር በተዋረድ/ ነው።

፩ኛ. በየአድባራቱና በየገዳማቱ ለሚገኙ የዜማ ጉባኤ ቤቶች ዐቢይ ትኩረት በመስጠት ትምህርቱን ማጠናከር፣

፪ኛ. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶችም ቢሆን ከየመዝገበ ድምፅ የሚሰሙትን እንቶ ፈንቶ «መዝሙር» ከሚያጠኑ ይልቅ ባላቸው ቀለል ባለ ስልት አስተምህሮት የቤተ ክርስቲያኒቱ የሆነውን ዜማዊ የአብነት ትምህርት እንዲማሩ ትክክለኛ ሥርዐት በመዘርጋት የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ ይኖርበታል።

*ሐመር፦ በአጠቃላይ በመዝሙር ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለማቃለል መፍትሔው ምንድን ነው?*

*መሪጌታ ዓምደወርቅ፦* ከላይ እንደጠቀስኩት የቤተ ክርስ ቲያኒቱ አስተዳደር ማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግና በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ጉልላት ላይ እየተሰቀለ ያለው እንቶ ፈንቶ መዝሙር ወርዶ በምትኩ ሥርዓትን የጠበቁ መዝሙራት ከፍ ከፍ ሲደረጉ ችግሩ ሊወገድ ብሎም ከሥሩ ሊነቀል ይችላል ብዬ አስባለሁ።✤

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## መዝሙራችን ወዴት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «መዝሙራችንን ከችግሮቹ...»

ከገጽ ፱ የዞረ

ለመድረስ እንጥራለን:: የምንግባባውም በእኩልና በአንድ ዓይነት አመለካከት ላይሆን ይችላል:: ቢያንስ በጉዳቱ አሳሳቢነት ከተግባባን ለመፍትሔ መጣራችን አይቀርም:: ለምሳሌ ያህል በመዝሙሩ ጉዳይ ውይይቱ በሰፊው ያሳየን አንድ ጉልህ ነገር አለ:: መዝሙርን በተመለከተ ዘማርያንና ምእመናኑ በሁለት ሐሳብ ሲከፈሉ ሊቃውንቱ ግን በአንድ መንገድ /በሐዘን/ ላይ መሆቸውን አይተናል:: ይህ ማለት የትኛውንም አቅጣጫ ብንከተል «መዝሙር» መፍትሔ የሚሻ ችግር ውስጥ ያለ አገልገሎት መሆኑን አረጋግጠናል ማለት ነው:: ከዚህ በኋላ ያለው ሥራ መፍትሔ ቢሆንም ውይይቱን የወደደውም ሆነ የጠላው አካል «መዝ ሙር ላይ ችግር የለም?» የሚልበት ሁኔታ አለመኖሩ ላይ ተግባብተናል ማለት እንችላለን:: ስለዚህ ባንስማማም ተግባብተናል::

ተወያይተን እንደተግባባን፣ ተወያይተን መፍትሔ ማምጣትስ አንችልምን? አዎን እንችላለን:: ነገር ግን አሁንም አንዱ ችግራችን ውይይትን አለመልመድ ነው:: እንዲያውም እንፈራዋለን:: የምንፈራው ደግሞ ስለማናውቀውም ጭምር ነው፤ የማያውቀው ሰው ሊፈራው አይችልምና:: ሐሳብ ማቅረብን እንደ ቀኖና፣ መተቸትንም እንደ ውግዘት የምንቆጥረው ከሆነ፤ እኛን ይመለከተናል የምንለውም ጉዳይ መነሻቱን ከጠላነው አስቸጋሪ ይሆናል:: እንዲህ ያለው ፍርሃት ደግሞ ቅዱስ ጳዉሎስ እንደተናገረው ፍቅራችንን ያጠፋዋል:: በፍርሃት ውስጥ ፍቅር የለምና:: ፩ኛቆሮ.፲፫/ ይህ ደግሞ በራሱ አያበቃም:: ለሚሰጠው ሐሳብና ለሚቀርበው መፍትሔ ሁሉ ተቃውሞአችን የምንገልጽ እንዲያውም በእልህ ሳናውቀው ወደ ባሰው ሁኔታ ልንጓዝም እንችላለን::

ዝግጅት ክፍሉም በሀገራችን ይልቁንም በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን የውይይት ባህል ደካማነት እያወቀ የገባበት ከላይ የጠቀስናቸውን የመሰሉ ችግሮች አይከሰቱም በሚል ሳይሆን «ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም» እንደሚባለው ባህሉን ለማዳበርና በስሜታዊነት ከመነቃቀፍና በቲፎዞነት ጠበቃ ከመሆን አልፈን ሰከን ብለን በመወያየት ለእውነትና ለፍቅር አገልግሎት የተሻልን ሆነን የምንገኝበትን መንገድ ለመቀየስ ብቻ ነው::

## በአካል ለምን አትወያዩም?

አንዳንድ ሰዎች ውይይት የሚያስፈልግ ከሆነ በመጽሔት ከማውጣት ይልቅ በአካል ለምን አትወያዩም? የሚል ጥያቄ ያነሣሉ:: እውነት ነው፤ በአካልም መወያየት ያስፈልጋል:: ነገር ግን አንድ መሠረታዊ ጥያቄ አለ:: መዝሙር በራሱ ችግር እንዳልሆነ ይታወቃል:: መዝሙርን ችግር ውስጥ ያስገቡት ሌሎች ሁኔዎች ናቸውና:: ታዲያ እነዚህ ችግሮች የዘማርያኑ ብቻ ናቸው ወይስ የኅብረተሰቡም ጭምር? መፍትሔውስ የእነማን ነው? ሌላው ደግሞ መዝሙርን ያነሣነው ከመሠረታዊው የኀትመትና ሥርጭት ጠባዩ በመነሣት ነው:: በዚህ ውስጥ ደግሞ ብዙ አካላት አሉ፤ እነዚህ ሁሉ እንዴት ወደ ጋራ ግንዛቤ ይመጣሉ? ስንል ሁሉንም ሊደርስ የሚችል መድረክ አስፈላጊ ሆኖ ይመጣል:: ይህን ማለት ግን የአካል ውይይቱ አያስፈልግም ማለት አይደለም:: ነገር ግን ያኛው /የአካል/ ውይይት የራሱ ጠባያት አሉት:: ግለሰቦች በጋራ ጥቅም ቢጣሉ፤ ራሳቸው ግለሰቦቹ ተወያይተው ይፈቱታል:: መዝሙር ግን ግለሰቦች ይሳተፉበታል እንጂ የግለሰቦች ጉዳይ አይደለም:: ስለዚህ ለውይይት የሚሆን ጥናት፣ መድረክ፣ ... ያስፈልጉታል፤ በመሆኑም የገጽ ለገጽ ውይይቱ እኛን አይመለከተንም ባንልም የመጽሔቷ ጉዳይ ግን አይደለም:: ስለዚህም በጽሑፍ አወያይተናል፤ ወደፊትም ዕድሜ ቢሰጠን ሁላችንንም በቀናነትና በንጹሕ ልቡና ብቻ እንድንወያይ ቢረዳን በዚሁ መንፈስ በሌሎች ጉዳዮቻችንም ላይ እንቀጥላለን::

ጉዳዩን «ርእስ ጉዳይ» ያደረግንበትን ምክንያት ከተገነዘብን ወደሚቀጥለው የመፍትሔ ጥቆማ እንሸጋገራለን:: በዚህ ጽሑፍ መፍትሔ የምለው «መዝሙራችን ሊሔድበት ይገባዋል» የምለውን ሳይሆን ወደ ዚያ ለመሔድ መደረግ የሚገባው ምንድን ነው የሚለውን ሐሳብ ነው:: በዚህ መሠረት አንደኛ ለመግባባትና ለመስማማት ይረዱን ዘንድ መብራራት ይገባቸዋል የምላቸውን ነጥቦች፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለችግሩ መባባስ መንሥኤ የሆኑና አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጉዳዮችን በማስቀደም «ምን ቢደረግ ይሻላል» የሚለውን አስከትላለሁ::

### መሠረተ ነገር

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት ከሰጡት አንባብያን ከተረዳኋቸው ነገሮች መካከል በጥቂት መሠረታዊ ነገሮች ላይ አለመግናዘብ መኖሩን ተረድቻለሁ:: መዝሙር፣ ያሬዳዊ፣ ሀብት ማግኘት፣ . . . የሚሉት በሐሳብ ክርክሩ ውስጥ ጎልተው ታይተው ነበር:: ስለዚህ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አጫጭር ማስገንዘቢያዎችን በማየት እንጀምር::

ሀ. <u>መዝሙር</u>፦ ከመዝገበ ቃላት ትርጉም ሆነ ከምስጢራዊ ይዘቱ መነሣት አስፈላጊ ቢሆንም በእኛ መጽሔት ለውይይታችን «መዝሙር» እያልን የጠራነው በቤተ ክርስቲያናችን ያሉት ምእመናን ያደምጡትና ይዘምሩት ዘንድ በዘማርያን የተሰናዳውና ታትሞ በገበያ ላይ የሚወለውን ዜማዊና ግጥማዊ ሥራ ነው:: በዚህ ብያኔ ከተነሣን ይህን መዝሙር አያስፈልግም ያለ እስካሁን አላጋጠመኝም:: መዝሙር ጥቅም የለውም የሚልም የለም:: ሰዎችን አይሰብክም፤ ወደ እግዚአብሔር አይመልስም፤ ያለም የለም:: የሰማናቸው አልጠቀሙንም፤ ወደፊትም አይጠቅሙንም የሚልም የለም:: እነዚህ ሊዘነጉ የማይገባቸው ናቸው:: ይህን የምለው አንዳንድ ሀሳቦች እነዚህን የሚሉ ሰዎች እንዳሉ በማሰብ የተነገሩ ስለሚመስሉ ነው:: የሚሰጡትን ሐሳብም ወደ እነዚህ ጽንፎች ወስዶ መተርጎም እንዳይገባ አስቀድመን ግንዛቤ መያዝ ይገባናል::

ለ. <u>ያሬዳዊ</u>፦ ከመጀመሪያው ይልቅ አከራካሪ የነበረው ይኼኛው እሳቤ /Concept/ ነው:: ቅዱስ ያሬድ የሚባል የዜማ ሊቅ ነበር፤ የራሱ ዜማ ነበረው፤ ዜማውም ሥርዓት አለው:: ይህን ተከትሎ ደግሞ ሌላ ድርሰት በመድረስ ማመስገን፣ መዘመር ይቻላል:: ታዲያ አንድ የራስ ድርሰት የሆነ መዝሙር ያሬዳዊ የሚባለው መቼ ነው? በእኔ አስተሳሰብ አንድን ሥራ በሁለት መንገድ ያሬዳዊ ማድረግ ይቻላል:: አንደኛ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ላይ በአንዱ የሰማነውን ዜማ በወጥነት በመውሰድ የራሳችንን ግጥማዊ ድርሰት በዚያ ዜማ በመዘመር /በመጮኽ/ ያሬዳዊ ማድረግ ይቻላል:: ለምሳሌ ያህል የሰዓታትን ለ«ኖኅ ሐመሩ»ን ዜማ በመውሰድ እነ መሪጌታ ሐዲስና ሌሎችም እንደተጠቀሙበት ማለት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ከተለያዩ የዜማ ድርሰቶቹ የዜማ ቅንጣቶችን በመገጣጠም የራስን ዜማ ማዘጋጀት ይቻላል:: ይህ ማለት አንድ ጸሐፊ የምናውቃቸውን ቃላት አገጣጥሞ የራሱ ዓረፍተ ነገር በመሥራት የራሱን አሳብ እንደሚያስተላልፈው ማለት ነው:: «የዜማ ቅንጣቶቹን» የመሰልኳቸው በቃላት እንጂ በሆሄያት አለመሆኑን አስተውሉልኝ::

በሆሄያት ቢሆንስ የሚል ይኖራል:: አዎን ሆሄያት ልናውቃቸው እንችላለን፤ ነገር ግን በምናውቃቸው ሆሄያት የማናውቃቸው ቃላት ሊፈጠሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ «ጉድ ሞርኒንግ?» ብንል ማንኛውም አማርኛ አንባቢ ሊያነበው ይችላል:: ቃላቱ ግን የአማርኛ አይደሉም፤ የእንግሊዝኛ ናቸው:: ስለዚህ ይህ እንግሊዝኛን በአማርኛ ማንበብ እንጂ አማርኛ እንዳልሆነ ለመገንዘብ እንችላለን:: በሌላ አገላለጽ አንድ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሰው «ጉድ» ብሎ ቢናገር አማርኛ ተናጋሪ ሊሰማው ይችላል::

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል

## እየመራ ነው?



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቃለ በረከት ዘቅዱስ አትናቴዎስ


ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

መለከትን ለሚነፉ ነቢያት የታዘዙ የተለያዩ ዐዋጆች ነበሩ:: በተጨማሪም ወደ እውነት እንዲመለሱ፤ መለከትንም ለመንፋት እንዲዘጋጁ በነቢዩ አንደበት እንዲህ በማለት ተናግሯልና «በጽዮን መለከትን ንፉ፤ ጾምንም ቀድሱ» /ኢዩ.፪÷፲፭/ ይህ የመለከት ማስጠንቀቂያ እና በምን ጾምበት ጊዜ ጾምን እንቀድስ ዘንድ የተሰጠ ጥብቅ ትእዛዝ ነው:: ወደ እግዚአብሔር የተጠሩ ሁሉ እርሱን አይቀድሱም፤ እርሱን የሚያረክሱ አንዳንዶች አሉና:: በእርግጥ የሚያረክሱት እርሱን አይደለም፤ የማይቻል ነውና፤ ስለ እርሱ ያላቸውን የራሳቸውን ሐሳብ /ሕሊና/ እንጂ:: እርሱ ቅዱስ ነውና በቅዱሳኑ ደስ ይለዋል:: /መዝ.፲፮÷፫/ ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚንቁትን «ሕግ ተላላፊዎች እግዚአብሔርን ይንቃሉ::» በማለት ይወቅሳል:: /ሮሜ፪÷፳፫/ ስለዚህ እኒህን ከሚመስሉ ጾምንም ከሚያረክሱ መለየት እንደሚገባ ሲያመለክት «ጾምን ቀድሱ» አለ::

ብዙዎች ለጾም ሲሰበሰቡ በልባቸው ሐሳብ ራሳቸውን ያረክሳሉ፤ እነዚህም በወንድሞቻቸው ላይ ክፉን በማድረግ፤ አንዳንዴም ባልንጀራን በማታለል ለመንጠቅ የሚደፍሩ ናቸው:: ሌላውን ነገር ሁሉ ሳንጠቅስ ራሳቸውን ከባልንጀሮቻቸው በላይ የሚያደርጉ ብዙ አሉ:: በዚህም ታላቅ ክፉትን ያመጣሉ /ያስከትላሉ/::

ምንም እንኳን በሳምንት ሁለት ቀናትን ቢጾምም ከቀራጩ አስበልጦ ራሱን በማየቱና በጾሙ በመመካቱ ብቻ ለፈሪሳዊው አልበጀውም:: በዚሁ መንገድ የእስራኤል ልጆችም ተወቅሰዋል፤ በእንዲህ ያለ የማይበጅ ጾም ውስጥ ያልፉ ነበርና:: በነቢዩ በኢሳይያስ አንደበት «እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በውኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን?» በማለት ይወቅሳል፤ ያሳስባል:: /ኢሳ.፶፰÷፭/

ስንጾም ምን ዓይነት ሰብእና መላበስ እንዳለብን፣ ጾማችንም በምን መልክ መሆን እንዳለበት አሁንም ደግመን እንናገር:- «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ በዚህ በሰባተኛው ወር ዓሥረኛው ቀን የማስተሥረያ ቀን ነው፤ የተቀደሰ ጉባኤ ይሁንላችሁ፤ ሰውነታችሁን አስጨንቋት፤ ለእግዚአብሔርም የእሳት ቁርባንን አቅርቡ» /ዘሌ.፳፫÷፳፯/ ከዚያም አስከትሎ የዚህን ሕግ ሐሳብ የበለጠ ሲተረጉም እንዲህ አለ:- «በዚያም ቀን የማይዋረድ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ::» /ዘሌ.፳፫÷፳፱/ ወንድሞቼ ሆይ



ጾም ምን እንደሚያደርግ፤ ስንጾምም በምን መልክ /ሁኔታ/ መጾም እንዳለብን ሕጉ ያዘዘንን እናስተውል::

አሁን ነፍስ ክፉውን ሐሳብ ሁሉ ባልተከተለች ጊዜ ትሑት ናት:: ይልቁንም በትሩፋት የምትመላለስና ብቁም ለመሆን መልካምን ነገር ትመገባለች:: መልካም ሥራና ክፋት የነፍስ ምግቦች ናቸው:: ነፍስ ባላት ነጻ ፈቃድ መሠረት ከሁለቱ አንዱን ሥጋ /መልካም ሥራን ወይም ክፋትን/ ትመገባለች:: ከሁለቱ ወደ አንዱም ታዘነብላለች:: ወደ መልካም ሥራ ካዘነበለች በበጎ ሥራ ታድጋለች:: በጽድቅ፣ በእርጋታ በየዋሕነት፣ በጽናት ትፋፋለች:: ቅዱስ ጳውሎስ «በእምነትና በተከተልኸው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ» /፩ጢሞ.፬÷፮/ በማለት ተናገረ:: በጌታም ዘንድ ይህ እውነት ነበር:: «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው::» ብሏል:: /ዮሐ.፬÷፴፬/

ይህ ካልሆነ ግን ነፍስ ወደ ውርደት ታዘነብላለች፤ በኃጢአት እንጂ በሌላ በምንም አታድግምና:: የኃጥአን ምግብ የዲያብሎስን ፈቃድ መፈጸም ነው:: እርሱ የኃጥአን ምግብ ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰማያዊ እንጀራ በመሆኑ የቅዱሳን ምግብ ነው:: በዚህም መሠረት ነው «ሥጋዬን ካልበላችሁ ደሜንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» ያለው::/ዮሐ.፮÷፶፫/ እንዲህ ከሆነ ዲያብሎስ የብርሃን ከሆነው ነገር አንዳች የማያደርጉ፣ በጨለማም ሥራ የጸኑ የክፉዎች ምግብ ነው:: ከዚህም መውጣት ይችሉ ዘንድ፤ ከክፋትም ይመለሱ ዘንድ፤ የነፍስ የሕይወት ምግብ በሆነው መልካም ሥራ እንዲያድጉ ጌታ ያዛል:: እነዚህም ከልብ የሚመነጭ ትሕትና ለራስ ክብርን አለመስጠት እና እግዚአብሔርን ማክበር /ማመስገን/ ናቸው::

*የእነዚህ ቅዱሳን ጾም እጅግ የረዘመ፣ ቀኖቹም የበዙ በመሆናቸው ምክንያት ማንም በጥርጥር አይውደቅ! ይልቁንም እግዚአብሔርን ማሰብ፣ ከእርሱ የሆነው ቃሉም፤ የሚፈሩትንና በእምነት የጸኑትን ለማኖር በምግብ ሁሉ ፋንታ ብቁ ነው::*

እንዲህ ያለው ጾምም ለነፍስ ይቅርታን የሚያስገኝላት ብቻ አይደለም፤ ቅድስት ሆና ትጠበቃለች እንጂ:: ቅዱሳንንም ከምድር ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ ለዚያም ያዘጋጃል:: በእርግጥም የነገርኳችሁ ነገር ድንቅ ነው:: አዎን እጅግ ተአምራዊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ ነው:: ከእውነትም ያልራቀ፤ በቅዱሳት መጻሕፍትም የሚማሩት ነው:: ያ ታላቅ ሰው ሙሴ ጾምን በጾመ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ፤ ሕግንም ተቀበለ:: ታላቁና ቅዱሱ ኤልያስም በጾመ ጊዜ ለታላቁ የእግዚአብሔር ራእይ ተገብቶ ነበር:: በመጨረሻም ወደ ሰማይ እንደወጣው እንደ እርሱ ዐረገ:: ዳንኤልም በጾመ ጊዜ ምንም እንኳን ወጣት ቢሆን ለታላላቅ ምስጢራት የታመነ /የተገባ/ ነበር:: እርሱ ብቻውን የንጉሡን ምስጢራት ይረዳ ነበር:: ስለዚህም ለታላላቅ ራእያት የተገባ ሆነ::

የእነዚህ ቅዱሳን ጾም እጅግ የረዘመ፣ ቀኖቹም የበዙ በመሆናቸው ምክንያት ማንም በጥርጥር አይውደቅ! ይልቁንም እግዚአብሔርን ማሰብ፣ ከእርሱ የሆነው ቃሉም የሚፈሩትንና በእምነት የጸኑትን ለማኖር በምግብ ሁሉ ፋንታ ብቁ ነው::

ካልሆነማ በሰማይ ያሉ መላእክት የአብንና የመድኃኒታችንን ፊት ዘወትር ባያዩ ባልጸኑ ነበር:: እናም ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ባለበት ጊዜ ሁሉ በእውነት በሥጋው በነፍሱ ጾመ፤ በመለኮት ቃል ይኖር ነበርና:: ወደ ሰዎች በወረደ ጊዜ ግን እግዚአብሔርም ከእርሱ በተሰወረ ጊዜ እንደሌሎች ተራበ:: በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ከተነጋገረባቸው ከአርባ ቀናት በላይ /ከተራራው እንደወረደ/ ጾመ አይባልም:: በአጠቃላይ ቅዱሳን እያንዳንዳቸው ለዚህ ከፍተኛ ምግብና /ኑሮ/ የተገቡ ነበሩ::

/Letters of Athanasius, P.506/



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «መዝሙራችንን ከችግሮቹ...»

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ምክንያቱም «ጉድ» የሚል የአማርኛ ቃል ስላለ፣ ወይም ደግሞ «ጉ» እና «ድ» የሚባሉ ድምፆች በራሱ ቋንቋ ስላሉ:: ይሁን እንጂ የሰማው እርሱ የሚያውቀውን የአማርኛውን የመገረም ቃል እንጂ መልካም የሚል ትርጉም ያለውን እንግሊዝኛውን አይደለም:: ስለዚህ እነዚያን ድምጾች መስማት መቻሉ የራሱን ሆሄ ሊያደርግለት አይችልም:: «ዬ» ድምፁ በአማርኛም በእንግሊዝኛም አለ:: ነገር ግን ሆሄው አንድ አይደለም:: እንደዚሁ ሁሉ እንደ ሆሄ ያለች ታናሽ ቅንጣትን እያመጣን የያሬድ ዜማ ውስጥ አለች በማለት ዜማውን ያሬዳዊ ማድረግ አንችልም:: ሆሄውን ብናውቀው ቃሉን እንዳማናውቀው ቅንጣቱን በማወቅ ዜማውን ያሬዳዊ ማለት አንችልምና:: የማናውቀውን ቃል በአማርኛ ሆሄያት እስከተጻፈ ድረስ ሆሄያቱን በመቁጠር አንድ ላይ ልናነበው እንችላለን:: እንዲህ ዓይነት የአማርኛ ቃል ግን የለንም:: ሆሄያቱ የአማርኛ መሆናቸው ብቻ ቃሉን የአማርኛ አያደርገውም:: ስለዚህ አንድ አትኳሪ አድማጭ ፈረንሳይኛ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች የሚናገሩትን ድምፅ እየሰማ «ይህ ሁሉ ድምፅ» በእኛ አለ ቢል ወይም ደግሞ ከእኛ ድምፆች የወጣ ድምፅ የላቸውም ቢል ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ አማርኛ ሆኑ ማለት እንዳልሆነው ሁሉ አንድ ሊቅ የያሬድን ዜማ ለማድነቅ «ዜማ ሁሉ ከያሬድ አይወጣም» ቢል ሁሉም ያሬዳዊ ነው ማለት አይደለም:: የተለየ ነገር ከሌለውማ ጥንቱንስ «ያሬዳዊ» ለምን ይባላል:: ስለዚህ ያሬዳዊ የሚባል የታወቀ ሕግና ሥርዓት ያለው ዜማ አለን:: ጥያቄው መዝ ሙሮቻችንን ሁሉ ያሬዳዊ ብቻ መሆን ይችላሉን? ሕዝባዊስ መሆን አይችሉምን? የሚለው ነው:: በርግጥስ መዝሙሮቻችን ላይ የተነሣው ጥያቄ ያሬዳዊ ባለመሆናቸው ብቻ ነው ወይስ ከሕዝባዊነቱም አፈንግጠዋል በሚል ጭምር?

ሐ. <u>ህብት</u>፦ ብያኔዬ ላይ በመጽሔታችን «መዝሙር» ያልነውን ነገር ካስቀመጥኩበት ዐበይት ምክንያቶች አንዱ ከዚህ ጋር የተገናኘ ነው:: እንደምታውቁት በእኛ ቤተ ክርስቲያን «መዝሙር» የሚባለው በቅዱስ ያሬድ የተሰናዳውና በየሰንበቱ እና በየክብረ በዓሉ በማኅሌት የሚቆም የታወቀ ምስጋና ነው:: ነገር ግን አስቀድመን በሰጠነው ብያኔ መሠረት እኛ «መዝሙር» የምንለው የዜማና የግጥም ደራስያን የሆኑ ሰዎች ደርሰውት ወይም አቀናብረውት /ለያሬዳዊ/ ታትሞ በገበያ ላይ እየዋለ ያለውን አዲስ ሥራ ነው:: እንግዲህ «ታተመ»፣ «ገበያ ላይ ዋለ» የሚሉት ናቸው «ህብትን» ወደ መዝሙር ጎትተው የሚያመጡት::

በዚሁ መሠረት እስካሁን በተሰጡት ሐሳቦች ዘማርያን አዘጋጅተው አሳትመው በሚያወጡት መዝሙር ለምን ገንዘብ ያገኛሉ? ያለ የለም:: ጥያቄው «መዝሙሩ ተበላሽቷል» ብለን መስማማት ብን ችል ለመበላሸቱ ምክንያት የሆነው «ገቢያው» ወይም ከዚያ በኋላ የሚገኘውን «ገንዘብ» ማሰብ ነው ወይስ የአቅም ማነስ የሚለው ነው:: በርግጥ በዚህ ዙሪያ ዋና ተጠያቂ የሚሆኑትም ዘማርያኑ ብቻ አይደሉም:: ይልቁንም አሳታሚዎቹን የበለጠ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነገር አለ እንጂ::

«ህብት» ብለን ርእስ ያደረግነውም በመዝሙራችን ላይ የተጠቀሱትን ብዙዎቹን ችግሮች ጉትቶ ያመጣቸዋል በማለት ነው:: በተለይ በቪሲዲ /VCD/ በሚዘጋጁበት ጊዜ ያለውን የአለባበስ፣ ለቅንብር የሚጠቀሙባቸው ሥዕሎች /Back ground Icons/፣ ... እነዚህ ሁሉ ብዙ ለመሸጥ ከሚደረጉ ጭንቀቶች የመጡ በመሆናቸው ለመዝሙሩ አረም ሆነውበታል የሚሉ አስተያየቶች ተነብበዋል::

ብዙ የመሸጥ ፍላጎት መገለጫ የሚሆነው ሌላው ጉዳይ ደግሞ የማስታወቂያው ጉዳይ ነው:: በተለይም በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ደጆች ላይ በበዓላትና በንግሥ ቀን በታላቅ የድምፅ መሣሪያዎች /በሞንታርቮ/ በመታገዝ የሚደረጉት ቅስቀሳዎች ጭራሹኑ ጥቅም የላቸውም ማለት ባይቻልም ጉዳታቸው ከፍተኛ ሆኖአል የሚለው አሳብ ብዙዎች የሚጋሩት ሆኖአል:: ቅዳሴውን፣ ትምህርቱን ሲያውኩ ደግሞ ሰሚዎቹ ሁሉ በእጅጉ ይማረሩባቸዋል::

## ችግሩ ምንድን ነው?

ከላይ የጠቀስናቸውን ሦስት ነጥቦች ይዘን መዝሙር ላይ ያለውን ችግርና መንሥኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በመጠቆም «ምን ይሻላል?» ወደሚለው እናመራለን::

ችግሩንና መንሥኤውን ከዮቆምንበት የአመለካከት ማዕዘን የተነሣ እንዳናዛባው ለመጠንቀቅ ያህል አንድ መነሻ ሐሳብ አስቀድመን እንመልከት:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያትን በ«ዘር» መስሎ ያስተማረበት ምክንያት ስንዴው /ዘሩ/ ንጹሕ መሆኑ ጠላትን እንክርዳድ እንዳይዘራ፣ መሬቱንም አረም እንዳያበቅል አያግደውም ለማለት ነው:: ይህ ሁልጊዜ የሚኖር ነገር ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ዘር መሆን መናፍቃንን እንዳይነሡ ወይም እንደ ሐሳባቸው /እንደተረዱት/ እንዳይተረጉሙ አላደረጋቸውም:: እንክርዳዱን አጉልቶ ያነሣውም አረም በገበሬው ዘንድ ገና ሲበቀል ጀምሮ ስለሚታወቅ በጊዜው ለማስወገድ አያስቸግርም:: እንክርዳድ ግን በአበቃቀልም ሆነ በቅጠሉ ስንዴን /ዘሩን/ ስለሚመስል አስቸጋሪ ነው:: የሚለየው ሰው

*እስከ አሁን ካሉን መዝሙሮች አብዛኞዎቹ ሕዝባዊ ዜማን መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ቤተክርስቲያኒቱም እንደ ተቋም ሕዝባዊ መዝሙራትን ምእመናን እንዳይጠቀሙ የከለከለችበት ጊዜ የለም:: ከታተሙትም አብዛኞዎቹ በዚሁ በሕዝባዊ ዜማ ስር የሚደመሩ ናቸው:: ስለዚህ ያሬዳዊ ብቻ መሆን እና አለመሆንን ከማንሣት ይልቅ ኦርቶዶክሳዊነት /በትውፊት፣ በሥርዓትና በባሕል /Church culture/ መጠበቅ አለመጠበቃቸውን መመርመር የሚሻል ይመስላል::*



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

እንኳ ቢኖር መንቀሉም አስቸጋሪ ነው፣ ጌታ እንዳስተማረን በርግጥም እንደሚሆነው እንክርዳድን ብቻውን መንቀል አይቻልም፣ ስንዴውንም አብሮ ይጎዳዋል። በዚህ ትምህርት ውስጥ በትንሹ ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን እንማርበታለን። የመጀመሪያው ከላይ እንደተገለጸው የዘሩ ንጽሕና ጥሩ መሆን ብቻ እንክርዳድና አረምን ሊያስቀር አለመቻሉን ነው። ሁለተኛው ደግሞ እንክርዳዱ ከጠላት አረሙ ግን ያለምንም ዘር ከዚያው ከመሬት የሚበቅል ጸረ ስንዴ /ዘር/ መሆናቸውን ነው። ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ እንክርዳዱን ያለጊዜው መንቀል ስንዴውን የሚጎዳ መሆኑን ወይንም ደግሞ ለስንዴ ሲባል ለእንክርዳዱም የሚሰጠው ጊዜ መኖሩን ነው። ይህም ማለት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ሁልጊዜም በጎው ነገር ላይ ሰይጣን አሾልኮ የሚያስገባው ስህተት አብሮ ሊኖር መቻሉን መረዳት ነው።

በዚህ ትምህርተ ወንጌል መሠረት «መዝሙር» ካልነው የአማርኛና መሰል የካሴት ኅትመት በፊት ያሬዳዊ ዜማንም ብንመለከተው የተሻለ ሊሆን ይችላል። ቅዱስ ያሬድ አንድ ሰው ነው። /ባለ ዜማው/ የደረሰውም ዜማ አንድና ወጥ ነው። በኋላ ዘመን ያሉ አበውም በሱባኤና በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ የእርሱን ዜማ መሠረቱን ሳይለቅ አስፋፍተውታል። በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን የአሁኑን ቅርጹን ያገኘው አቋቋም ከቅዱስ ያሬድ የቁም ዜማ ተወስዶ ዝማሜ፣ አደራረስ፣ አመላለስ፣ መረግድ፣ ጽፋትና ወረብ ወጥቶለት በአገልግሎት ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ ዘመነ መሳፍንት ያመጣውን መለያየት ተከትሎ ደግሞ ይኸው አቋቋም ብዙ ዓይነት መልክና ቅርጽን ወርሷል። እንኳን አቋቋሙ ድጓው /ቁም ዜማው/ እንኳን ከሦስት በላይ በሆኑ ዜማዎች ይዜማል። ምንም እንኳ ልዩነታቸው ብዙ ባይራራቅም በዘመን ብዛት ልዩ ልዩ መሆን ግን አልቀረለትም። በእውነት ለመናገር ችግሩ የአቋቋሙ መለያየት አልነበረም፣ ለየአቋቋሙ ያለን አመለካከት ግን ሁልጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ሲጎዳ ይኖራል።

የተክሌው ከጎንደሬው፣ የአጫብሩ ከቆሜው፣ ፋኖው ከሳንኳው፣ . . . አንዱ ከሌላው ጋር በሚፈጥረው መናናቅና መጠላላት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ መራበሽ የተለመደ ሆኖአል። አረም ማለት ይህ ነው። የራሱ የአቋቋሙ ችግር ሳይሆን አቋቋሙን የተማሩት የሰዎቹ /የመሬቱ/ ችግር ነው። መሬት ከራሷ አረም እንድታበቅል ሰዎቹም መሬታውያን ናቸውና ከመሬታዊ ባሕርያቸው የሚመነጭ ቅንዓትና ትዕቢት ወይም ይህን የመሰለ ነገር አይጠፋባቸውም። ይህ አረም በትምህርትና በምክር ሳይታረም ሲቀር ደግሞ ጠብና ግጭት የመሰሉትን የራሱን ፍሬ ማፍራቱ አይቀርም። አንባቢ ሆይ አስተውል፣ ዛሬ ጉዳያችን ስለ አቋቋም ችግር ማየት አይደለም፣ ነገር ግን የትኛውም

> የባህል ተጽእኖው ... እንደ ሰውነት ውፍረት እና እንደ ቁመት ዕድገት ያለ ነው። ሰውነቱ ሲወፍር ወይም ቁመቱ ሲያድግ የሚያውቅ የለም። ከወፈረ እና ካደገ በኋላ ግን ይህን ያህል ሆኛለሁ ይላል። እነዚህም ለውጦች ልክ እንደዚሁ ካለበለዚያም በበለጠ ሁኔታ ሳናውቃቸው በእኛ ውስጥ የሚያድጉና የራሳችን ክፍሎች ሆነው የሚሰሙን ነገሮች ናቸው።

መንፈሳዊ ስጦታ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮችን መጠቆም ነው። ስለዚህ በዜማችንና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይህን ያህል ከጠቆምን አሁን በቀጥታ ወደ /አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ. . / መዝሙሮቻችን ችግር እናቅና።

### የመዝሙሮቻችን ፈተና

በመዝሙር አስፈላጊነትና ጥቅም ላይ የማያከራክር ሐሳብ /መግባባት/ ስላለን በዚህ መድከም የለብንም። የትችቱና የውይይቱም መነሻ ችግራቸው ይፈታላቸው እንጂ አላስፈላጊ ናቸው፣ ይቅሩ የሚል አይደለም። እውነት ለመናገር አሁን ያሉትም ችግሮች እጅግ ግዙፎች ናቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን ግዙፉን ችግር ለማምጣት እጅግ ምቹዎች ናቸው። የፍልስፍና መምህራን የአንድን ነገር የወደፊት ሁኔታ /Potentiality/ ከሚያመለክቱበት ምሳሌ አንዱ እንጨት ነው። እንጨት እሳት አይደለም፣ እሳት የመሆን ዕድሉ ግን ከፍተኛ ነው። እሳት በደረቁ ከጀመረ እርጥቡንም እያደረቀ እንዴት እሳት እንደሚያደርገው እናውቃለን። ስለዚህ ክርክሩ «እንጨት እሳት ነው ወይስ አይደለም?» የሚለው አይደለም። ዋናው ፍሬ ነገር ከጥቂት ደረቅ እንጨት ተነሥቶ ትልቁን ጫካ ሳይቀር በቀላሉ የሚያነደውን እሳት የመፍራት ጉዳይ ነው። እሳትን የሚፈልጉት ሁሉ ይጠነቀቁበታል እንጂ እንዳሻቸው አይጫወቱበትምና። የመዝሙራችን ፈተናም ይኼው ነው። በቀላሉ ሊነድ፣ ሊጠፉና ሊያጠፉ የሚችል ዓይነት «እንጨት» /ምሳሌ ዘየሐጽጽን አይርሱ/ መሆኑን መዘንጋት አይገባንም የሚል ነው።

ታሪክንም ማስታወስ ይቻላል። አርዮስን የረዳው ትምህርቱ ሳይሆን የሚያስተላልፍበት መንገድ ነበር። አርዮስ ተከታዮችን ያፈራው በፍልስፍናው ወይም በእምነቱ ሳይሆን በተወዳጅ ግጥሙ ነበር። «ግጥሙን» እንደ ሥነ ጽሑፍ ስናየው ግጥም በራሱ ችግር አልነበረም። ችግሩ በግጥሙ ይተላለፍ የነበረው ክህደት ነው። ለዚያ ዘመን ሰዎች ግን ሁለቱን /ዘሩንና እንክርዳዱን/ መለየት በእጅጉ ከብዶ ነበር። የአሁኑም ስጋት ይኸው ነው። ለማንኛውም ወደ ችግሮቹ ልግባ።

### ሀ. የኦርቶዶክሳዊነት ችግር

ኦርቶዶክሳዊነት /Ortodoxy/ በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ አንድ ነገር ለባለቤቶቹ ትክክል /እውነት/ በሚሉት ነገር የመጓዝና ያለመጓዝ ጉዳይ ነው። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ ኦርቶዶክሳዊ ስንል ቃሉን ለቤተክርስቲያኒቱ መጠሪያነት ከምንጠቀምበት አግባብ ባይርቅም የሚወክለው ግን ግሳዊ ስምነቱን ነው። ይህን ቃል የተጠቀምኩትም ወደፊት ቤተክርስቲያኒቱ ልትወስንበት የሚገባውን ነጥብ እንዳልዳፈረው በመፍራት ነው። ይህም መዝሙሮቻችን በሙሉ «ያሬዳዊ» ብቻ መሆን አለባቸው ወይስ ሕዝባዊ መዝሙሮችም ሊኖሩን ይገባል? የሚለው ነጥብ ነው። እስከ አሁን ካሉን መዝሙሮች አብዛኞዎቹ ሕዝባዊ ዜማን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ቤተክርስቲያኒቱም እንደ ተቋም ሕዝባዊ መዝሙራትን ምእመናን እንዳይጠቀሙ የከለከለችበት ጊዜ የለም። ከታተሙትም አብዛኞዎቹ በዚሁ በሕዝባዊ ዜማ ስር የሚደመሩ ናቸው። ስለዚህ ያሬዳዊ ብቻ መሆን እና አለመሆንን ከማንሣት ይልቅ ኦርቶዶክሳዊነት /በትውፊት፣ በሥርዓትና በባሕል /Church culture/ መጠበቅ አለመጠበቃቸውን መመርመር የሚሻል ይመስላል።

የቤተክርስቲያን ባህል የሚባለው አብያተ ክርስቲያናት በዶግማና በቀኖና ተመሳስለው በሒደት እነዚሁ እንደተጠበቁ የሚፈጠሩ ጥቃቅን ሀገራዊና ትውፊታዊ ክስተቶች የሚፈጥሩት ልዩነት ነው። ለምሳሌ በእኛ ቤተክርስቲያን ማንኛውም ጸሎት የሚያርገው /የሚጠቃለለው/ በአቡነ ዘበሰማያት ነው፣ በግብጾች ግን እንዲህ ላይሆን ይችላል። የባህል ልዩነት የሚባለው ይህ ነው። በእነርሱና በእኛ የቅዳሴ አፈጻጸም መካከል እንዲሁ የባህል ልዩነቶች ይኖራሉ። ይህ ጉዳይ ሰፊ ነው። በዚህ ጽሑፍ ያነሣሁት ግን የእኛን መዝሙሮች ኦርቶዶክሳዊነት የምንለካው ይህን ከመሰለው ባህላችን፣ ሥርዓታችንና በመሳሰሉት ሀብቶቻችን መሆን ይገባዋል ለማለት ነው።

በዚሁ መሠረት ስንሔድ በግብጽ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የራሷ የሆነ የመዝሙር ባህል አላት። ከዚያ የወጣውን ሁሉ በፍጹም አትቀበለውም። ምእመናኑም ለይተው ያውቁታል። በርግጥ በአንድ ወቅት በእነርሱ ሀገር ያሉትን ፕሮቴስታንቶችን ለመመለስ ሲባል ዜማቸውን ማዘመን ጀምረው ነበር። ነገር ግን የእነርሱ አባላት ተጎዱ እንጂ እንደታሰበው የሔዱትን ሊመልሱ አልቻሉም። ስለዚህም ነበር ሊቁ «እነርሱን እንመልሳለን ብለን መንገድ ወጣን። ነገር ግን እኛ እንደወጣን ቀረን እንጂ እነርሱ አልተመለሱም» ያሉት። በእኛም ቤተ ክርስቲያን ያሬዳዊ ያልሆኑ መዝሙራት



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

መውጣት የጀመሩት /በካሴት ባይታተሙም/ ቀደም ብሎ ነው:: ቢያንስ በንጉሡ ዘመን:: ይሁን እንጂ ኦርቶዶክሳዊነት /ትውፊታዊውን ሕዝባዊነት/ ስላልጣሱ ጥያቄ አልተነሣባቸውም ነበር:: ስለዚህ የአሁኖቹ ጥያቄ ይነሣባቸዋል ማለት ጥያቄው ኦርቶዶክሳዊነታቸው /ርቱዕነታቸው/ ላይ ነው ማለት ነው:: በያሬዳዊነት ከሆነ የቀደሙትም ከጥያቄው አያመልጡምና::

በአሁኑ ጊዜ ያለውን ችግርም በግርድፉ ይህ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ችግር በራሱ የሚመጣ አይደለም፤ መንሥኤ የሚሆኑ ሌሎች ብዙ ችግሮች አሉ:: ለምሳሌ ጥቂቶቹን እንመልከት::

## ፩. የፖሊሲ አለመኖር

ቤተክርስቲያኒቱ በመዋቅር ደረጃ በተለይም የራሷ ሲኖዶስ ከኖራት እጅግ ጥቂት ዓመታት በመሆኑ ብዙም ላያስፈርድባት ቢችልም በዚህ በኩል ተጠያቂ መሆኗ አይቀርም:: እንዳሏት ሊቃውንት እንደ ጥንታዊነቷና ሐዋርያዊነቷ መጠን በዚህ ዙሪያ ዘመኑን የዋጀ ፖሊሲ አውጥታ እርሱን ብትተገብር ችግሩን እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይቻል ነበር:: አሁን ያሉት መዘምራንም ሙሉ በሙሉ ሊፈረድባቸው የማይገባው ይህ ባለመኖሩ ምክንያት ነው:: «ሕዝቡ ይቀበለዋል፣ ጥሩ ነው» በሚሉትና አቅማቸው በፈቀደው መጠን የሚሔዱትም ለዚህ ነው:: ይህ ፖሊሲ ላይጻፍም ይችላል፤ እንደ እንግሊዞች ሕገ መንግሥት:: ነገር ግን ሁሉም የሚያውቀውና የሚያከብረው መሆን መቻል አለበት:: ይህ በሌለበት ወደ የት መሔድ፣ ማደግ እንዳለባቸው ሳያውቁ ከየመጡበት ወይም ሳይፈልጉም ቢሆን ከሚያውቁት ዕውቀት የሆነ ነገር መውሰዳቸው አይቀርም:: ሌላው ቀርቶ «ይስተካከል» የምንለውን ሰዎች «ወደ የት?» ቢሉን ግልጽ አቅጣጫ ማሳየት የሚያቅተን ይመስለኛል:: ምክንያቱም ትክክል እንዳልሆነ ተሰማን እንጂ ወደ የት መውሰድ እንዳለብን የተረዳን አይመስልም:: ይህ ግን በጉዳዩ ዕውቀት ያላቸውን አያጠቃልልም:: ስለዚህ ለመወቃቀስና ለመነታረክ «አንተ ማን ሆነህ ነው? አንተስ? ለመባባልም የዳረገን ይኸው ወጥ መሔጃ ነገር /ፖሊሲ/ አለመኖሩ ነው::

## ፪. የባህል ተጽእኖ

የባህል ተጽእኖ የሚለው ነገርም ሙያዊ ብያኔ ቢያሻውም፤ በዚህ ጽሑፍ ከእኛ ውጭ በሆነ ባህል መማረክን ያመለክታል:: አንዳንድ ጊዜ የማንፈልገው ሽቱም ቢሆን ቤቱ ከተረጨ እዚያ ውስጥ ቆይተን ስንወጣ ያንኑ ዓይነት መዓዛ መሽተታችን አይቀርም:: ልክ እንደዚያው የምንጠላው የፕሮቴስታንት የመዝሙር ባህል፣ የምንሸሸው ዘፈንና ጠባዩ /ምንአልባት የምንሸሸው ከሆነ ነው/፣ አጠቃላይ ሌላው የባህል ተጽእኖው በእኛ ላይ የሚያመጧቸው ተጽእኖዎች መኖራቸው ልንሸሽገው የምንችለው ነገር አይደለም:: ይህ ደግሞ እንደ ሰውነት ውፍረት እና እንደ ቁመት ዕድገት ያለ ነው:: ሰውነቱ ሲወፍር ወይም ቁመቱ ሲያድግ የሚያውቅ የለም:: ከወፈረ እና ካደገ በኋላ ግን ይህን ያህል ሆኛለሁ ይላል:: እነዚህም ለውጦች ልክ እንደዚሁ ካለበለዚያም በበለጠ ሁኔታ ሳናውቃቸው በእኛ ውስጥ የሚያድጉና የራሳችን ክፍሎች ሆነው የሚሰሙን ነገሮች ናቸው:: ከዚያም በሥራዎቻችን እንዳይገለጡ ማድረግ ከባድ ይሆናል:: ምክንያቱም መጀመሪያ በሰው ውስጥ የሚካሔደው ለውጥ የመለኪያ /Parameter/ ለውጥ ነውና::

«ጨው የሌለው ምግብ ጥሩ ነው» የሚለው መለኪያ በውስጡ /በኅሊናው/ ሳይኖር ጨው የሌለው ምግብ በእጅጉ ያስጠላዋል:: «ጥሩ ነው» የሚለውን ከተቀበለ በኋላ ግን ጨው ካለው በላይ ጨው የሌለው ምግብ ይጣፍጠዋል:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ መዝሙራችን «ጥሩ ነው» የምንልበት መለኪያ በባህል ተጽእኖው ስለተለወጠ የቀድሞው ጨው /ወንጌላዊ ጠባይ፣ ኦርቶዶክሳዊ ላህይ/ ያለው መዝሙራችን ዛሬ ለብዙ ሰው አልጣፍጠው ብሏል:: ስለዚህ አዲሱን ጨው የለሽ ምግብ /የነፍስ/ እየጣፈጠው ለመብላት ይቋምጣል:: ይህ ደግሞ ዘማርያንንም አብሮ ይገፋቸዋል:: ይህን ያነሣሁት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከምሰማው የመዝሙር መለኪያ የተነሣ ነው:: አሁን አሁን «እገሌ ጉባኤያችን ያቀዘቅዝብናል፣ ሞቅ የሚያደርገው እገሌ ነው፤ ልዝዝ አትበይ፣ ...» የሚሉ ቃላት ይደመጣሉ:: ከዚህም የተነሣ የሰውነት እንቅስቃሴያቸው ዝላይን እስከማካተት ደርሷል:: በእውነት ለመናገር ዝላይ በዘፈን እንኳ አልፎ አልፎ የሚታይ ክስተት ብቻ ነበር:: ይህን የመሰሉ ሌሎች ብዙ የባህል ተጽእኖዎች አሉ:: በእኔ እምነት እንኳን በመዝሙሩ በጸሎታችንም የሌሎቹ ደመና ተጋርዶ ጥላውን ያጠላብን ይመስለኛል::

## ፫. የተንሸዋረረ አመለካከት

ብዙ የተዛቡ፣ የተንሸዋረሩ አመለካከቶች አሉ:: ብዙ ሰዎች አንድን ነገር «ዘመናዊ» በማድረግ ይስማማሉ:: «ዘመናዊ» ሲያደርጉት ግን አይታዩም:: የዚህ አንዱ ችግር ለዘመናዊነት ያለው የተዛባ አመለካከት ነው:: «መዝሙርን ማዘመን ምንድን ነው?» መጤን ያለበት ጉዳይ ነው:: አንድን ነገር ዘመናዊ ማድረግ ማለት እስከሚገባኝ ድረስ ያለህን ነገር ሌላው ሙሉ በሙሉ እንዲቀበለው ማድረግ ይህም ካልተቻለ ቢያንስ ለሐሳቡ ተገዢ እንዲሆን ማድረግ መቻል ነው::

ታዲያ መዝሙራችን እንዲህ ያለ ተጽእኖ እየፈጠረ ነው ወይስ እየተፈጠረበት? ... መጤን ያለበት ነገር ነው:: ፈረንጆቹ አስበው ሠሪዎች ስለሆኑ አዲስ ያመረቱትን ነገር «ዘመናዊ» /Modern/ እያሉ መጀመሪያ ዜጋቸውን ከዚያም ቀሪውን ዓለም ያግባቡታል:: በዚህም ውጤታማ ሆነዋል:: ሌላውን በአስተሳሰብ በራሳቸው መለኪያ ለመምራት ችለዋል:: አሁን እኛ «ዘመናዊ» የምንለው ያንን የእነርሱን ሐሳብ የተቀበለውን ይመስላል:: መሆን የነበረበት ግን እኛም በራሳችን ያንኑ ትውልድ ለመያዝ የምንጠቀምበት አዲስ ስልት መፍጠር ነበር:: የጥንቶቹ አበው የያሬድን ዜማ የተቀባበሉበት መንገድ አለ፤ አሁን ያን መንገድ ለውጠን ዜማውን ማስተላለፍ ብንችል ዘመናዊ አደረግነው ልንል እንችላለን:: ዜማውን ካጠፋነው ግን በሌሎች ዘመናዊ የማጥቃት ዘዴ ተጠቅተን ወደቅን እንጂ እኛ ዘመናዊ ልንሆን አንችልም:: ቢቻል ቢቻል የያሬድን ዜማ ፈረንጅ እንዲቀበለው ማድረግ ብንችል ዘመናዊ የምንሆነው /የምናደርገው/ ያን ጊዜ ነበር:: በእኛ ሀገር ሁኔታ ግን ሌሎቹ ቀድመው አስበው ነድፈው በሰጡን ዘልሎ ጥልቅ ብሎ መጓዝ ዘመናዊነት ይባላል:: ለማንኛውም ዘመናዊነት እንዲህ ቀላል ባለመሆኑ እተወዋለሁ:: ለመዝሙራችን ፈተና ውስጥ መግባት አንዱ ምክንያት ግን ይህን የመሰሉ አስተሳሰቦችን በበቂ ሳይረዱ ሌሎቹ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብሎ የመግባት ችግር ነው:: የተንሸዋረረ አመለካከት የገጠመው ግን መዝሙር ብቻ አይደለም:: እጅግ ብዙ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ነው:: ችግሩ የጋራና የሁላችንም ቢሆንም መዝሙርም ላይ ሊታወስ የሚገባው ስለሆነ ተነሥቷል::

## ፬. የትምህርት ማነስ

መዘምራን ወደ መዝሙር የገቡበት ሁኔታ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ቤተክርስቲያንን ለማገልገል ወስነው፤ ለዚያም የሚገባውን ተምረው፤ በዚህ ላይ ጸጋቸውን አውቀው ነው ለማለት ግን አይቻልም:: ቀደም ብዬ የጠቆምኩት የፖሊሲ ጉዳይም የሚያያዘው ከዚህ ጋር ነው:: አንባብያን ልትረዱልኝ የምፈልገው «የሚዘምሩ ሰዎች ያልተማሩ ናቸው» እያልኩ አለመሆኔን ነው:: ነገር ግን ዲግሪ ካላቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ በአጋጣሚ ዳኛ ሌላው ሐኪም እንደማይሆነው ሁሉ ይልቁንም ለዚያ ለሚሰጠው ሓላፊነት የሚገባውን ልዩ ትምህርት እንደማያልፈው ሁሉ ለመዝሙርና ለዘማርያንም በዚህ አገልግሎት ያበቃ ዘንድ የተዘጋጀ ትምህርት እስካሁን በእኛ ሀገር የለም፤ ስለዚህም ተምሮ የሚዘምርም የለም:: ሌላው ቀርቶ የቤተክርስቲያኒቱን ዜማ በደንብ የተማሩትና ትምህርተ ሃይማኖቷንም ጠንቅቀው የሚያውቁት /በእኛ ሀገር እንደነ ሊቀመዘምራን ኪነጥበብ ወልደ ቂርቆስ፣ መሪጌታ ፀሐይ እና ቀሲስ አበበ ያሉት/ እንኳ የቤተክርስቲያን ትምህርት ዕውቀታቸው ረድቷቸው ጥሩ መዝሙር አቀረቡልን እንጂ መዝሙርን የተመለከተ የተማሩት ትምህርት እስከማውቀው ድረስ የለም::

ይህ ትምህርት በቤተክርስቲያኒቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደ ነገረ ሃይማኖቱ /Theology/ የሚሰጥ፣ በትምህርት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዓይነት ዜማ፣ ንባብ፣ ከላይ የጠቀስነው የፖሊሲ፣ የትውፊት፣ የባህልና የነገረ ሃይማኖት /በተለይም ከመዝሙር የተገናኙ፣ የሥነ ጥበብ /ግጥም፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ... ወዘተ/ የሚሉትን የትምህርት ዓይነቶች ያካተተና ምስክርነት /ሰርተፍኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ/ የሚሰጥበት ሆኖ መኖር ነበረበት:: ይህ በሌሎች አብያተ ክርስቲያን አለ፤ በእኛ ነው የሌለው:: ይህ ባለመኖሩ መዘምራኑ በሌለው ነገር ባይወቀሱም ካለን ነገር ቢያንስ ጥቂቱን እንኳ መማር ግን የሚገባ ነበር:: ይህ ባልሆነበት አንድን ዘማሪ በማየት፣ ሰንበት ትምህርት ቤት መዝሙር ሲዘምር ጥሩ ነው ድምፅህ/ሽ/ በመባሉ ብቻ የሚታተም ካሴት ለማው ጣት መምጣቱ አንዱና መሠረታዊው ችግር ነው:: በጣም በትንሹ ሊስተካከሉና ሊታረሙ የሚችሉ ችግሮች ሳይታረሙ የሚወጡበት አንዱ ምክንያትም ይኸው የትምህርት ማነስ ነው:: ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ ትንሽ ንባብ፣ የዜማም ወግና የመሳሰሉትን ሳይማሩ በቀጥታ ዘማሪ መሆን መዝሙሩንም ዘማሪውንም እየጎዳ ያለ ችግችን ነው:: በዚሁ ሥር የማላልፈው የትምህርተ ሃይማኖቱንም ጉዳይ ነው:: አንዳንድ ግጥሞች በቅኔና በምስጢራት ቀርቶ ከሥነ ጽሑፍ ዘርፍ አንዱ ከሆነው ከሥነ ግጥም /Poetry/ አንጻር እንኳ ቢተነተኑ ምን እንደሚወጣቸው እግ ዚአብሔር ይወቀው:: ይህም ብቻ አይደለም፤ አሁን አሁን እንደ ጥቁር አሜሪካውያን ለመዝሙር ግጥሞ ፓለቲካዊ አንድምታ ማሳዘል የተጀመረ ይመስላል:: ይህም ቢሆን ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ ብቻ ሳይሆን ባዕድ ነገር ነው:: የዚህን መንገድ የተጠቀሙበትም ሌሎች ናቸው:: በዚህ ጽሑፍ እነዚያን አካላት ማንሣት አያስፈልግኝም:: ይሁን እንጂ የትምህርተ ሃይማኖትና በዚህ ዙሪያ ላለው የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማነስ ጉልህ አስረጂ ሆኖ እናገኘዋለን::

፩. ግዴለሽነት

ይህ በሦስት አካላት ላይ ጎልቶ ይታያል:: በዘማርያኑ፣ በአሳታሚውና በቤተክርስቲያን አባቶች:: በእኛ ባህል ሰውን ላለማስቀየም መጣር ጎልቶ የሚታየው የመተራረም ባህሉን በመጉዳት ነው:: አለማስቀየም አለመበደልን እንጂ አለማረምን የሚመለከት አልነበረም::

በመጀመሪያ ደረጃ ዘማርያኑ ለመማርና ለማወቅ ሲጥሩ ነቃፊቹን /Criticals/ ለመፈለግ ግድ ያላቸው አይመስሉም:: በቅርባቸው ያሉትንና የሚያውቋቸውን /ሊያደርጉት የሚችሉትም ይህንኑ ነው/ አሳይተው ትክክል ነው ካሏቸው በዚያው የመርካትና ነቅሰው የሚያዩትንና የሚያደምጡትን ለመፈለግ ግድ የለሽ ይሆናሉ:: በርግጥ ራሱን የቻለ ተቋም ስለሌለና ሁሉም የግሉን ኑሮ ስለሚኖር ቢፈልጉም ማግኘታቸውን እጠራጠራለሁ፤ ይሁን እንጂ


ርእሰ ደብር ገብረ መስቀል ዘሓሊበላ

**በእውነት ለመናገር ችግሩ የአቋቋሙ መለያየት አልነበረም፤ ለየአቋቋሙ ያለን አመለካከት ግን ሁልጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ሲጎዳ ይኖራል::**

የተለየ ትጋት ቢያደርጉ ራሳቸውም ቀስ በቀስ ሊያርሟቸው የሚችሏቸውን ነገሮች እንዲሁም የእኔ ቢጤ እንኳን ሊያያቸው የሚችላቸውን ስሕተቶች የሚፈጽሙት በግድየለሽነት ይመስለኛል::

አሳታሚዎችም ዋና ጉዳያቸው የገበያ ጉዳይ ስለሆነ መታየቱን እንኳን የሚወዱት ለገበያ ካልሆነ በቀር በትክክል ለመጠበቅ የሚያደርጉት ጥረት አይታይም:: ምክንያቱም ጥሩ መዝሙሮችን የምናየው ከዘማሪው/ዋ/ ትጋትና ጥንቃቄ እንጂ ከአሳታሚው ባለመሆኑ:: ይህም ለውጥ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው::

«አባቶች» ያልኩት ከጵጵስና እስከ ዲቁና በቤተክርስቲያን በማገልገል ላይ ሆነው በዘማርያኑ የሚጠየቁትን ሁሉ ነው:: ይህን ለማሳየት አንድ ገጠመኝ ላቅርብ:: በአንድ ወቅት ክፍለ ሀገር ጉባኤ ሔደን የክፍሉ ሊቀጳጳስ ተገኝተው ነበር:: በዚያ ዕለት ከዘመሩት /አንዱ/ እጅግ በዝላይ የተመላ እንቅስቃሴና ሕዝቡን ስሜት ውስጥ ከትቶ ከመቀመጫቸው ባስነሣ አቀራረብ ይዘምራል:: መዝሙሩ ሲያልቅ ዘማሪው ወደ ሊቀጳጳሱ ሔዶ መስቀል ሲሳለም «እግዚአብሔር ይባርክህ» ብለው ጨመርም አድርገው ይመርቁታል:: ዘማሪውም ተደስቶ ሔደ:: ምሳ ስንበላ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሊቀጳጳሱ ወደሚስተናገዱባት /የደብሩ አስተዳዳሪ/ ቤት አስተዳዳሪው እኔንም ጋበዙኝ:: በዚያ የምሳ ሰዓት ግን አባታችን እጅግ ጥልቅ ሐዘናቸውን ገለጡ:: «ሕዝቡ እኮ በከተማ የሚገኘውን ዘፈኑን እዚህ ስላገኘ ነው የተደሰተው፣. . .» እያሉ ስሜታቸውን ገለጹ:: በጊዜው እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ስላየኋቸው ሐሳቤን አልገለጽኩም:: ግን «ለምን በግልጽ አይነግሩትም?» የሚለው ጥያቄዬ ነበር:: በርግጥ እነርሱ ሕዝቡ እንዳይደነብር ዘማሪውም እንዳይደነግጥ ብለው ሊሆን ይችላል:: እውነት ነው፤ ነገር ግን ቦታና ጊዜ መርጦ ቀስ አድርጎ መምከርም የሚገባ ነው:: ሁሉም በዚህ መጣላትን ስለሚፈራ ግድ የለሽ ሆኖአል:: አንዳንዶች እንዲያውም «በጣም ጥሩ ነው» ሁሉ ይላሉ፤ ይህ ደግሞ ሽንገላ ነው:: ይህን ገጠመኝ ያስነሣኝ ግን ጉባኤው አልቆ ከዘማሪው ጋር በአንድ መኪና ወደ አዲስ አበባ ስንመለስ ከዘማሪው የሰማሁት ነው:: ዘማሪው አባታችን እስኪ ገረሙ ድረስ በመዝሙሩ እንደተደሰቱ ነገረኝ:: ዘማሪው እውነቱን ነው፤ በእርሱ መረዳት «ይባርክህ፣ ያሳድግህ» ሲሉት ማድነቅ ሊመስለው ይችላል:: እነርሱም እንደዚያ ማለታቸው ማበረታታት ይገባል ብለው ይሆናል:: በኋላ ጠርቶ ትንሽ መምከሩን መተዋቸው ዘማሪውን ይህን የመሰለ ሐሳብ አስያዘው፤ ከዚህ በኋላ እኔ ልነግረው ብችል እንኳ፤ መታረም የሚገባው ነገር መኖሩን ይቀበላል ለማለት ያስቸግረኛል:: ይህ ሁሉ የግዴለሽነት ውጤት ነው:: ምክንያቱም የዕውቀት ችግር አይደለምና::❖

*ይቆየን::*



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት

በዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

*በ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፫ እትማችን ያለልምድና ያለችሎታ ክህነትን መሾም ስለሚያስከትለው ጉዳት፣ በዕድሜ በመግፋቱ ብቻ አንድን ሰው ከፍ ወዳለ የክህነት ደረጃ ማምጣት ተገቢ ስላለመሆኑና፣ ካህኑ ያለፈቃዱ ክህነትን ቢሾም እንኳ ባልተወጣው ሓላፊነት ከተጠያቂነት እንደማይድን ... ወዘተ በተመለከተ ጠቃሚ ነጥቦችን መርጠን ማቅረባችን ይታወሳል። ለዚህ እትም ያጠናቀርነውን ደግሞ እነሆ።*



«ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ...»

## የካህናት ዋና መሣሪያ

የካህናት ዋና መሣሪያ፣ የሚያጠቁበትም ሆነ የሚከላከሉበት፣ ራሳቸውንም ሆነ የክርስቶስን መንጋ የሚጠብቁበት ቃለ እግዚአብሔር ነው።

«በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።» /ኤፌ.፮፥፲፮-፲፯/።

ቅዱስ ጳዉሎስ ብዙ ተአምራት ማድረግ እየቻለ እንኳ ዋናው መሣሪያው ቃለ እግዚአብሔር ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስም «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ» በማለት ይህንን ኃይል ገንዘብ እንድናደርግ መከረን። /፩ጴጥ.፫፥፲/። እንዲሁም ሁሉም በአንድነት ድሆችንና መበለቶችን የማገልገሉን ሓላፊነት ለእስጢፋኖስ የሰጡት «ቃሉን ለማገልገል» ነው። /ሐዋ.፮፥፬/። እኛም ራሳችንን እንዲሁ ለቃለ እግዚአብሔር ማዋል አለብን። «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ»። /ቆላ.፫፥፲፮/ ፍላጎታችንንና ዓላማችን የክርስቶስ ቃል በሙላት እንዲኖርብን ሊሆን ይገባል። የምንዘጋጀው ለአንድ ዓይነት ጦርነት አይደለምና፤ ጠላታችንም አንድ ዓይነትና የሚጠቀመው ሥልትና መሣሪያም የተወሰነና አንድ ዓይነት አይደለምና። ጦርነቱ ብዙና የተለያየ፤ እያንዳንዳቸውም የተለያየ መሣሪያ የሚጠቀሙ ስለሆኑ ከእነርሱ ጋር ጦርነት የሚገጥም ሰው የእያንዳንዳቸውን ተንኮልና ዘዴ ሊያውቅ ይገባዋል።

ስለዚህ በሁሉም አቅጣጫ በሚገባ የታጠርንና የጸናን ልንሆን ይገባል። አለበለዚያ ጠላታችን በደካማ ጎናችን በኩል ገብቶ ይወጋናል።

አይሁዳዊ አስተሳሰብ ላላቸው ሰዎች ቀለብ የሚሆን ከሆነ ከአሕዛብ ጋር ጸንቶ መጋደሉ /ጸንቶ መቆሙ/ ምን ይጠቅመዋል? ወይንም ደግሞ እነዚህን ሁለቱንም ሠልጥኖባቸው ነገር ግን ወግ አጥባቂነትንና ጽንፈኝነትን የሚያራምዱ ወደ ውስጥ ዘልቀው ከገቡና መንጋውን ከረበሹ ምን ጥቅም አለው? ዲያብሎስ የሚያመነጫቸውን ኑፋቄዎች ሁሉ ስንዘረዝር ላለመዋል እንዲህ ማለት ይበቃል። እረኛው ሁሉንም እንዳመጣጣቸው ድል እያደረገና በቃለ እግዚአብሔር ስሕተታቸውን ካልገለጠባቸው በስተቀር ተኩላው በአንድ መንገድ ገብቶ ከመንጋው ብዙዎችን ሊያጠፋ ይችላል።

ለምሳሌ - የቫሌንቲነስንና የመርቅያንን ከንቱ ትምህርት የሚቀበሉና እነርሱን በመሰለ በሽታ የተያዙ ሁሉ በእግዚአብሔር ለሙሴ የተሰጠውን ሕግ በሙሉ ከቅዱሳት መጻሕፍትነት ተርታ ያወጧቸዋል።

አይሁድ ደግሞ የሕጉ መፈጸሚያ ጊዜ የደረሰና ተፈጽሞ ያለፈ ቢሆንም ሁሉንም ነገር እንደ መጀመሪያው አድርቆን ማክበርና መፈጸም አለብን እያሉ ከእግዚአብሔር አሠራርና ዓላማ ውጭ ሆነው ይገኛሉ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሁለቱንም ጽንፍ በመተው ማዕከላዊ መንገድን ትከተላለች። በአንድ በኩል እንደ አይሁድ በኦሪት ቀንበር ሥር አትወድቅም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉን የሚነቅፉትን አትታገሣቸውም፥ ነገር ግን ጊዜው ቢያልፍም በጊዜው ጠቃሚ ስለነበር ታከብረዋለች፤ አትነቅፈውምም። ከእነዚህ ከሁለቱ ጠላቶች ጋር የሚፋለም ሰው ይህንን ማዕከላዊ መንገድ መረዳትና ማስረዳት ይገባዋል።

አይሁድን ሕጉን እንዳለ እንፈጽም ማለታቸው ጊዜው ያለፈበት መሆኑን ለማስረዳት ሲል ሕጉን አለመጠን ቢያብጠለጥለውና ቢያሔሰው ሊያጠፉትና ከቅዱሳት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መጻሕፍትነት ተርታ ሊያወጡት ለሚቋምጡት መናፍቃን ደኅና ድንጋይ ያቀብላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእነዚህን መናፍቃን አፍ ለማስያዝ ሲል ከመጠን በላይ እያደነቀና እያከበረ ለዚህ ለአሁኑ ጊዜም እንደሚያስፈልግ እያደረገ ቢናገር ደግሞ የአይሁድ አፍ እንዲከፈት መንገድ ይሰጣል፡፡

እንደገናም በሰባልዮስና በአርዮስ ዕብደት የሚሰቃዩትም ማዕከላዊውን መንገድ ባለመያዛቸው ከቀናችው ሃይማኖት ወጥተዋል፡፡ በስም ክርስቲያን ቢባሉም እምነታቸውን ለሚመረምረው ግን አንዱ ከአይሁድ ብዙም ያልተሻለ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ከእነርሱ የሚለየው በስም ብቻ ነው፡፡ ሁለቱም ከእውነት እጅግ በጣም የራቁ ናቸው፡፡

ስለዚህ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አደጋው ከባድ ነው፡፡ የኦርቶዶክሳዊነት መንገድ ጠባብ ነው፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ አስፈሪ በሆኑ አደጋዎች የተከበበ ነው፡፡ አንዱን ጠላት እናጠቃለን ስንል በሌላው ጠላት እንዳን ወጋ ልንሰጋና ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ እነዚህም ከውጭ ባሉት ከሚሰነዘረው ያላነሰ ፈታኞችና አስቸጋሪዎች ናቸው፡፡ እንዲያውም ለመምህሩ የበለጠ የሚያስቸግሩ ናቸው፡፡

አንዳንዶች ትርጉም የለሽና ጥቅም አልባ ከሆነ የማወቅና የመጠየቅ ፍላጎት ብቻ ሊያውቋቸው ስለማይቻላቸው፣ ቢያውቋቸውም ምንም ስለማይጠቅሟቸው ጉዳዮች በመጠየቅ ራሳቸውን ያባዝናሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔርን ስለ ፍርዱ ይጠይቁታል፡፡ ሊደረስበት የማይችለውን ጥልቅ ለመለካትና ለመድረስ ይሞክራሉ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ግን «ኵነኔከ ዕሙቅ ጥቀ፤ ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ናት»/መዝ.፴፭፥፮/

*የኦርቶዶክሳዊነት መንገድ ጠባብ ነው፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ አስፈሪ በሆኑ አደጋዎች የተከበበ ነው፡፡ አንዱን ጠላት እናጠቃለን ስንል ለሌላው ጠላት እንዳንዋጋ ልንሰጋና ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡*

**ትምህርተ ሃይማኖትን የተመለከተ ጸብ፣ ክርክር በተነሣ ጊዜ፥ ሁሉም መሣሪያውን ከአንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጠቀሰ ጊዜ፤ የሕይወት ምግባር ብቻውን ምን ይረባል? ከካህኑ የዕውቀት ጉድለትና የጥበብ ማነስ የተነሣ አንዱ ወደ ኑፋቄ ቢሄድና ከቤተክርስቲያን አካልነት ቢለይ የትህርምቱና የሕይወቱ መልካምነት ጠቀሜታ ምን ላይ ነው?**

ይላሉ፡፡ ስለ እምነታቸውና ስለክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ግን ሲያስቡና ሲጠነቀቁ የሚገኙት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ብዙኃኑ ግን ሊታወቅና ሊደረስበት ስለማይቻለው ነገር እንዲሁ ሲጠይቁ ይገኛሉ፡፡ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣውን ነገር ሲጠይቁ ይገኛሉ፡፡ እርሱ እኛ እናውቀው ዘንድ ያልፈለገውን ነገር ለማወቅ አጥብቀን ስንታገል ጥቅምና ረብህ አናገኝም /ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተቃራኒ በመሄድ እንዴት ውጤት ልናገኝ እንችላለን?/ ከመጠየቃችን የሚተርፈን አደጋ ብቻ ነው፡፡

ሁኔታው ይህ ቢሆንም እንዲህ ጥልቀቱ ወደማይታወቀው /ዕሙቅ/ የሚደረገው ፍለጋ ተገቢ አይደለም ብሎ ቢያስቆማቸው ትዕቢተኛና አላዋቂ ነው ይሉታል፡፡ ስለዚህ እርሱም ከእንዲህ ዓይነት ስድብና ነቀፋ ለመዳን፤ ሕዝቡንም ጥቅም ከሌላቸው ጥያቄዎችና ሐተታዎች ለማውጣትና ወደ ሚጠቅማቸው እንዲያተኩሩ ለማድረግ ካህኑ ብዙ ፈሊጥ ያስፈልገዋል፡፡

ለዚህም ሊረዳውና መሣሪያ ሊሆነው የሚችለው በቃለ እግዚአብሔር በሚገባ መብሰልና ጥልቅ የሆነ ዕውቀትን ገንዘብ ማድረግ ነው፡፡ ካህኑ በዚህ በኩል ደካማ ከሆነ በእርሱ ሐላፊነት ያሉት ብዙዎቹ /ደካሞቹና ማዕከላውያን መሐል ሰፋሪ የሆኑት/ ሁል ጊዜ በነፋስ እንደሚመቱ መርከቦች ከመሆን የተሻሉ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ካህኑ በትምህርት የበሰለ ሆኖ ሌሎችን ለመጥቀምና ለመርዳት እንዲችል በአቅሙ ሁሉን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ቅዱስ ጳዉሎስ ደቀ መዝሙሩን እንዲህ ያለው ለዚህ ነው፡- «ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ» /፩ጢሞ፬፥፲፫/፡፡ የዚህንም ጠቀሜታ እንዲህ በማለት ከዚያው ቀጥሎ አስረዳ፡- «ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና፡፡» /ቁ.፲፮/ እንደገናም እንዲህ ይላል፡- «ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ፤ የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማርም የሚበቃ፣ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም፡፡» /፪ጢሞ፪፥፳፫-፳፬/፡፡ ቲቶን ሲመክር ስለጳጳሳት ሹመት ጨምሮ

የተናገረውን ተመልከት «ጳጳስ... ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ሊመክር፥ ተቃዋሚዎችንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና. . . » /ቲቶ.፩፥፱-፲/፡፡

ታዲያ ልራሱ ያልተማረ ሰው ሌሎችን ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት እንዴት አድርጎ ሊመክር፤ ተቃዋሚዎችንስ እንዴት አድርጎ አፋቸውን ሊዘጋ ይችላል? «... የማይታዘዙና ከንቱ የሚናገሩ፤ የሚያታልሉም፤ ይልቁንም ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና፡፡ እነዚህም ስለ ነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ስለሚገለብጡ፤ አፋቸውን መዝጋት ይገባል፡፡» /ቲቶ.፩፥፲-፲፩/፡፡ «ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን፡፡» /ቈላ.፬፥፮/፡፡ እንዲሁም «በመልካም የሚያስተዳድሩ ቀሳውስት ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል፡፡» /፩ጢሞ. ፭፥፲፯/፡፡ ተብሏል፡፡

ማስተማር ፍጹም የሚሆነው መምህራን በሚያደረጉትም በሚያስተምሩትም መልካም አርአያ ሆነው የሚያስተምሯቸውን ወደ ቅድስና ሕይወት ሲመሯቸው ነውና አንዱ ብቻ ለማስተማር አያበቃም፡፡ ጌታችን እንደተናገረ፡- «የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፡፡» /ማቴ.፭፥፲፱/፡፡ ማድረግና ማስተማር አንድ ቢሆኑ ኖሮ ሁለተኛው ቃል /የሚያስተምርም/ የሚለው አያስፈልግም ነበር፤ እንዲሁ «የሚያደርግ ቢኖር» ማለት ይበቃው ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱንም ለይቶ በማስቀመጥና በመግለጽ በተግባር ማድረግ አንድ ነገር፤ ዶክትሪን /ትምህርት/ ደግሞ ሌላ ነገር መሆኑን እንዲሁም የሚማሩትን ለመጥቀም አንዱ የሌላውን ድጋፍና ርዳታ የሚፈልግ መሆኑን አስረዳ /አሳየ/፡፡

የክርስቶስ ምርጥ ዕቃ ሐዋርያው ቅዱስ ጳዉሎስ ለኤፌሶን ቀሳውስት ያላቸውንም እናስታውስ፤ «ስለዚህ ሦስት ዓመት

ወደ ገጽ ፵ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ጫትን በመጠኑ ብንጠቀምበት ምን ይጎዳል?

*በሊቀጠበብት ሐረገወይን አገዘ*

*እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ንጹሕና ቅዱስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ሰውም በሥነ ፍጥረቱ በአግባቡ ቢጠቀምበት ክፋት ያለው አይመስለኝም፡፡ መብልም ሆነ መጠጥ በሚበጅ መንገድ ከተጠቀምንበት መልካም ነው፡፡ በመሆኑም በትምህርት ዓለም ላለነው ወጣቶች ለትምህርታችን ስኬት የሚያግዘን ነገር አለ፡፡ እርሱም ጫት ነው፡፡ በቶሎ እንዳንተኛ፣ ተጠንቅቀንና ነቅተን እንድናጠና በማድረግ ጫት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ታዲያ ጫትን እንደቡና ሁሉ በመጠኑ ብንጠቀም ምን ይከለክለናል? ጫት የተከለከለ ከሆነ ምን ስለሆነ ነው? እንደዚህ የሚያነቃቁ ነገሮችን ተጠቅሞ በትምህርት ስኬታማ መሆን በቤተክርስቲያን የተለመደ አይደለምን?*

*ተከለጻድቅ*

*ከደብረ ዘይት*

የተከበሩ ጠያቂያችን በመጀመሪያ መልካም ነው፣ መልካም አይደለም፣ አስፈላጊ ነው፣ አስፈላጊ አይደለም፣ በሚሉ ግምታዊ ጉዞዎች ከመጠመድዎ በፊት የተቸገሩበትን ነገር ለማወቅ ጥረት በማድረግዎ እናመሰግንዎታለን፡፡

በመቀጠልም ይበላሉ አይበሉም፣ ይጠጣሉ አይጠጡም ወደሚለው ድምዳሜ ከመግባታችን በፊት የሰውን የአፈጣጠር ክቡርነትና ቅዱስነት መረዳቱ ቢቀድም መልካም ነው፡፡ የሰው አፈጣጠር ከሌሎች ሥነ ፍጥረታት የተለየ በመሆኑ የሚጠቅመውን ብቻ ሳይሆን የጠቀመ መስሎ የሚጎዳውንም የሚገነዘብ፣ የሚጎዳውን ብቻ ሳይሆን የጎዳ መስሎ የሚጠቅመውንም የሚረዳ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

የሰው ልጅ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ፣ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ መፈጠሩም ነበር በሌሎች ሥነ ፍጥረት ላይ ለመሾም ያበቃው፡፡ ምክንያቱም በአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እንስሳትን ቢመስልም በሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ መላእክትን በመምሰሉ ከራሱ አልፎ ለሌሎች ፍጥረታት ገዥም፣ አስተዳዳሪም ሆኖ ተሹሟል፡፡ ማስተዳደር ደግሞ የሚጀመረው ከራሱ ሕይወት መሆኑ ይታወቃል፡፡

ልዑል እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ሆኖ የተገኘው ያለ ምክንያት አይደለም፣ ፈጣሪው በባሕርዩ ንጹሕ ቅዱስ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ጠያቂው እንደገለጡት እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም መሆኑን በአንድነት እንመሰክራለን፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና፡፡ «ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደወገኑ አበቀለች፡፡ እግዚብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ» በማለት የአዝርዕት፣ የዕፀዋትንና የአትክልትን መልካምነት አስረድቷል /ዘፍ. ፩፥፲፪/

የዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መሠረት በማድረግ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡ «ንብል እንከ ከመ ኲሉ ሰናይ ፍጥረተ እግዚአብሔር ወአልቦ ግዱፍ ወመንፈስሰ ሕይወተ ሥጋ ይእቲ ንጽሕት ወቅድስት በኲሉ» ይላል፡፡ ትርጉሙም «እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልም እንደሌለ እንናገራለን፣ የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽሕት ቅድስት ናት» ማለት ነው፡፡ /ጸሎተ ሃይማኖት/

በትእዛዘ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሁሉ መልካም ነው ብሎ ማመን የፈጣሪውን ቅድስና መመስከር እንደሆነ ከተማመን የተፈጠረውን ሁሉ መብላትና መጠጣት ወደሚለው ፍላጎት ግን ሊያመራን አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ ይህን ብላ ይህን አትብላ የሚል መመሪያ ሊሰጠው የቻለው የምግቡን ርኩሰት ለመግለጥ ሳይሆን የአምላክን የሕግ ምንጭነትና የሰውን ሕግ አክባሪነት እንዲሁም የዕውቀቱን መጠን ለማሳየት መሆኑን ማስተዋል ነው፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያ ትእዛዝ የሚታወቀው «አትብላ» በሚል ነበር፡፡ ዘፍ. ፪፥፲፯ አዳም ዕፀ በለስን እንዳይበላ የተከለከለው ዕፀ በለሱ ርኩሰት ስለነበረበት አይደለም፣ አዳም ሕጉን በመጣሱ እንደሚረክስ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ አትብላ አለው እንጂ፡፡

በሌላ ትእዛዝም ንጹሐኑን እንስሳት ከርኩሳኑ ለይተው እንዲመገቡ ቅዱስ እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን አዟቸው ነበር፡፡ የዚህ መመሪያም ታላቅ ምክንያት ነበረው፡፡ ሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔር የበኩር ልጆች ናቸውና በሥርዓተ አምልኮ፣ በአመጋገብ፣ በአለባበስ በአኗኗር ከግብረ አሕዛብ መለየት ነበረባቸው፡፡ አሕዛብ የሚመገቡትን ሁሉ እንዳይመገቡ፣ ለይተው እንዲመገቡ ታዘዋል፡፡ ዘሌ.፳.፳፬ አሁንም እስራኤል የሚረክሱት ምግቡን በመጠቀማቸው ብቻ ሳይሆን የአምላካቸውን ትእዛዝ በመተዋቸው እንደሚረክሱ ለማስጠንቀቅ የተሰጣቸው መመሪያ መሆኑን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው፡፡

ቅዱስ እግዚብሔር በዘመነ ብሉይ በዓመተ ፍዳ /በዓመተ ኩነኔ/ ለነበረው ሕዝብ በዚህ መልኩ የሕግና የሥርዓት ሕይወት እንዲኖረው ካሰበ፣ በዘመነ ሐዲስ በዓመተ ምሕረት ውስጥ ላለው ሕዝበ እግዚአብሔር እንዴት የበለጠ ቅድስናና ንጽሕና እንዲኖረው አይፈቅድ ይሆን? አልፎ አልፎ እንደሚሰማው አንዳንድ ወገኖች «ብላ፣ አትብላ» የሚል ትእዛዝ በዘመነ አዲስ ኪዳን እንደማያስፈልግ ይናገራሉ፣ ነገር ግን በዘመነ ክርስትናም የሰው ልጅ የበለጠ ተቀደሰ፣ የበለጠም ከበረ እንጂ አልረከሰም፡፡

የበለጠ ከበረ፣ የበለጠ ተቀደሰ ማለታችንም እንዲሁ አይደለም፡፡ «አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» ተብሎ የተጻፈበት ምክንያት በአዲስ ኪዳን የሰው ልጅ ወደተሻለ ጥንቃቄና ሕይወት እንዲያመራ እንጂ ወደ ግብረ እንስሳት ተመልሶ ክርስትናውን እንዲንቅ

> **በተለያዩ የሱሰኝነት ማዕበል እየተንገላቱ ከዚህ ማዕበል ለመውጣትም መንገዱ ጠፍቶባቸው እየተቸገሩ እያስቸገሩም የሚንቀሳቀሱት አጀማመራቸው በየጥቂቱ ነበር፡፡ በጥቂቱ የተጀመረው በየወቅቱ አድጎ ከቁጥጥራቸው በላይ ሆኖ ሲታወቅ ማየታችን ግን የተለመደ ነው፡፡**



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አልተመከረም:: በሕገ ብሉይ ያልተሻለ ሕይወት የነበራቸውን አሕዛብ ወደ ክርስትና ለመመለስ ቅዱስ ጳውሎስ በተጠቀመበት የስብከት ዘዴም እንዲህ ብሎ አስተምሯል «ሁሉም ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም» ፩ቆሮ. ፲፥፳፫:: የተፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም መልካም የሚሆነው ግን በአግባቡና ለተፈጠረበት ዓላማ ሲውል ወይም ስንጠቀምበት ነው:: ለምሳሌ የእባብ መርዝ ጎጂ ነው፤ ነገር ግን በሂደት የሰው ልጅ ለመድኃኒትነት ተጠቅሞበታል:: ይህን ለሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ጎን አውቆ መጠቀምን በጊዜው ፈጣሪ ለሰው ልጆች ገልጧል:: ጫት ሲፈጠር ጀምሮ መልካም አይደለም የማንለውም ለዚያ ነው፤ መልካምነቱ ግን እግዚአብሔር ለሰዎች ሳይጎዳ የሚጠቅምበትን ምስጢር በገለጠው ጊዜ የሚታይ ነው:: «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» ብሎ ራሱን ያሳመነ ሰው ቢኖር በሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ቀድሞ መመርመር አለበት::

የጥያቄውን ዐቢይ ቁምነገር ስንመለከተው ተነቃቅተን ለማጥናት በትምህርታችንም ስኬታማ ለመሆን ጫት መቃም መልካም እንደሆነ ለማወጅ ይሞክራል:: ጠያቂያችን ለዘመናዊ ትምህርትዎ ጫት ቅመው ተነቃቅተው አጠኑ ከዚያ ቀጥሎስ? አሁን መነቃቃት የለመደ ሰውነትዎ በዘወትር እንቅስቃሴዎ የለመደውን ቢያጣ ምን ሊከሰት ይችላል ብለው ገምተው ያውቃሉ? የተማሩትን ለመፈተን ወደ ክፍል መግባትዎ አይቀርም፤ እንደተባለው ቅመው፤ ተነቃቅተው ሊገቡ ወይስ ስሜትዎን ደብቀው በመያዝ ለፈተና ሊቀመጡ? በመግቢያዬ ላይ የሚጠቅም መስሎ የሚጎዳ ያልኩት ይህንን ነው::

መጥኖ መቃምን እንደመፍትሔ አስቀምጠዋል መጠኑ በምን ዐይነት የቅጠል

# የተፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም መልካም የሚሆነው ግን በአግባቡና ለተፈጠረበት ዓላማ ሲውል ወይም ስንጠቀምበት ነው::

መለኪያ ምን ያሕል እንደሆነ ባይታወቅም መመለስ ወደማይቻልበት የሱሰኝነት ልምምድ ውስጥ እየተገባ እንደሆነ ግን ማረጋገጥ አለብን:: በተለያየ የሱሰኝነት ማዕበል እየተንገላቱ ከዚህ ማዕበል ለመውጣትም መንገዱ ጠፍቶባቸው እየተቸገሩ እያስቸገሩም የሚንቀሳቀሱት አጀማመራቸው በየጥቂቱ ነበር:: በጥቂቱ የተጀመረው በየወቅቱ አድጎ ከቁጥጥራቸው በላይ ሆኖ ሲታወኩ ማየታችን ግን የተለመደ ነው:: ጫትና ቡናን አቀራርቦ በመውሰድ ችግር የለውም ማለትም ተገቢ አይሆንም:: በዓለም ውስጥም ቢሆን ጫት የሚያስከትለው ጉዳት ከግምት ገብቶ ከሀገር ወደ ሀገር በቀላሉ እንዳይዘዋወር መደረጉ ያሳሳቢነቱን ልክ ያስረዳናል:: ጫት ከሌሎች ቡናን ከመሰሉ ሱስ አምጪ ነገሮች ጋር ሲነፃፀር ናርኮቲክ /አደንዛዥ/ መሆኑ መረሳት የለበትም::

የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት የጽድቅና የኃጢአት መንገዶችን በማሳየት ብቻ የሚወሰን አይደለም:: ቤተክርስቲያናችን በሥጋዊ፣ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ክንውኖች ዙሪያ አሳስፈላጊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችንም ጭምር የምታሳይበት የአስተምህሮ ሒደት አላት:: «... ወንድምህ የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው» /ሮሜ.፲፬ / ሰውነትን የሚጎዳ ማንኛውም ቅጠላ ቅጠል በተለይ ለክርስቲያኖች አስፈላጊ አለመሆኑን አበው ያስተምራሉ:: «ወብውሕ ለነ ከመ ኢንትከላእ እምነ ኩሉ ግብር ዘእንበለ ዘአሕረሞ ፍትሐ ሕግ በእንተ ከዊኖቱ ዘያበጽሕ ኀበ ሙስና ሕሊና ወአማስኖ ጠባይዕ ወሙስና ሥጋ፤ አእምሮን ወደ ማጥፋት ባሕርይን ወደ ማናወጽ አካልን ወደ ማጉደል የሚያደርስ ስለሆነ የሕግ መጽሐፍ ከከለከለው በቀር ከምግብ ሁሉ እንዳንከለከል መሆን ይገባናል::» በማለት ይገልጧቸዋል:: /ፍ.ነገሥት አንቀጽ ፳፫፥፰፻፺፯/ ሰውን የሚገድሉ አእምሮን የሚያጠፉ የማይጣፍጡ የማያጠግቡ ዕፅዋት አሉና::

## ጫት የሚያስከትለው ችግር

### ሀ. በሥጋዊ ሕይወት

ሥጋ በባሕርዩ ተመጋቢ ነው:: በተመጋቢነቱ ግን የሰጡትን ሁሉ የሚቀበል፣ የሚስማማውም አይደለም:: የዚህን እውነት ለመቀበል ጫትን አዘውትረው በመቃም የተጠመዱ ወገኖቻችን የጥርሳቸው ውበት አልቆ ደቆ፣ የአፋቸው ጠረን ተለውጦ፣ የአእምሮአቸው ሚዛን ተዛብቶ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ሥጋዊነትን፣ ከመልአካዊነት ይልቅ እንስሳዊነትን ተላብሰው እንዲታዩ ያደርጋቸዋል::

### ኢኮኖሚያዊ ችግር

በጫት ሱሰኝነት የተጠመዱ ወገኖች ከሚያለሙት የሚያጠፉት፣ ከሚያተርፉት የሚከሥሩት፣ ከሚያገኙት የሚያጡት የበለጠ መሆኑን የባለሙያ ጥናት አያስፈልገውም:: በየዕለቱ በሚደርሱ የተሽከርካሪ አደጋዎችና የሰው ሕይወት ማለፍ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የጫት ተጠቃሚ አሽከርካሪዎች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በየትምህርት ቤቱ የሚታየው የመምህራንና ተማሪዎች የሥነ ምግባር ጉድለትም የዚሁ ዕፅ ተጠቃሚዎች እርሾ መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃል:: ወደ ሌላ የከፋ አደንዛዥ ዕፅ መሸጋገሪያ ድልድይ እንደሆነም ይታመናል::

### ማኅበራዊ ችግር

ጫት መቃም ለጋብቻ መፍረስ፣ ለማኅበራዊ ሕይወት መናጋት፣ ዓይነተኛውን ቦታ ይይዛል:: ጫት በመቃም አባዜ የተለከፉ ሰዎች ለትዳራቸው፣ ለማኅበራዊ ሕይወታቸው፣ የሚያስቡበት አጋጣሚ ሁሉ የቀዘቀዘ ይሆንባቸዋል:: ጫቱ ሲገኝ በምርቃና፣ ጫቱ ሲጠፋ በድንዛዜ በመያዛቸው ሌላ የተስተካከለ ጉዳይ የሚያስቡበት ጊዜ ሊኖራቸው አይችልም:: ከላይ እንደተመለከትነው የጫት መቃም ውጤት ለጥናት፣ ለምርምር፣ ለንቃት ወዘተ በሚሉ ቃላት እየተዋበ ቢጀመርም የፍጻሜው ውጤት ግን በጋብቻ ሕይወት፣ በማኅበራዊ እሴት፣ በሥራ ተነሣሽነት፣ በባሕል ተጽዕኖ፣ በጠባቂነት፣ በምግባረ ቢስነት፣ በሀገር ዕድገት ላይ እያስመዘገበው ያለው ጥፋት ምስክር ነው:: በመሆኑም ጫት አለመቃም ዓለምን መልካም ከማድረግ አንፃር ያለው ድርሻ ታላቅ ነው:: ልዑል እግዚአብሔር ግን በመልካም ሥራ ሰውነትን ማክበር እንደሚቻል በቅዱሳኑ ላይ አድሮ አስተማረ:: «ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት ክርስቶስ በግልጽነት ሁሉ እንደወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዬ ይከብራል::» /ፊል.፩፥፳/ አካልን ከሚጎዳ ማንኛውም ነገር መከልከልና መጠበቅ እግዚአብሔርን በሥጋ ቅድስና ማክበር ነው::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

> **የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት የጽድቅና የኃጢአት መንገዶችን በማሳየት ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያናችን በሥጋዊ፣ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ክንውኖች ዙሪያ አሳስፈላጊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችንም ጭምር የምታሳይበት የአስተ ምህሮ ሒደት አላት፡፡**

### የጤና ችግር

በጤና ረገድ ጫት አነሰም በዛም የጨ ጓራ ሕመም፣ የሆድ ድርቀት እና የመሳ ሰሉትን የጤና ችግሮች ሊያስከትል እን ደሚችል ይታመናል፡፡ አእምሮን በመስ ረቅም በአስተዋይነት እንዳናስብ በማድ ረግ ከሚያደርስብን መንፈሳዊ ጉዳት በተጨማሪ የጤና ችግርም ይሆንብናል፡፡

### ለ. በመንፈሳዊ ሕይወት

በመግቢያ ላይ እንዳቀረብነው የሰው ልጅ አፈጣጠር ለቅዳሴ ለውዳሴ የተመ ቻቸ ሆኖ ነው፡፡ እግዚአብሔር ባወቀ ምሥ ጋናውን ከመላእክት፣ ምግበ ሥጋውን ከእንስሳቱ ጋር እንዲካፈል አደረገው፡፡

የጸሎትን ሰዓት ለመጠበቅ፣ የጾምን ጊዜ ለመወሰን፣ በሥርዓተ ቅዳሴ ተሣታፊ፣ የቅዱስ ሥጋው የክቡር ደሙ ታዳሚ ለመሆን፤ ሌሎችንም መንፈሳዊ ተግባራት በወቅቱ፣ በሰዓቱና በቦታው ለመከወን የተረጋጋ አእምሮ፣ የሰከነ መንፈስ፣ የታሸና የተገራ አካለ ሰብእና አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ሥርዓታተ ሕይወት በቤተክርስቲ ያን የተወሰኑና የተለመዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን አንድ በጫት መቃም ልምምድ ውስጥ ያለ ክርስቲያን ሊፈጽማቸው ይችላል ብሎ መገመት ከሚቅመው በላይ መሳሳት ነው፡፡ ምክንያቱም የጫት ቃሚው አካላዊ ስሜት ጫት ሲገኝ በምርቃና፣ ጫት ሲጠፋ በእ ንቅልፍና በማዛጋት የታሠረ ስለሆነ እነ ዚህን ምስጢራተ ቤተክርስቲያን የሚተገ ብርበት ቀርቶ የሚያስብበት ጊዜ የለው ምና ነው፡፡

ከዚህ የበለጠ ምን ስቃይ አለ? ይህስ የሱስ ተገዢነት በመንፈሳዊ ሕይወታችን በቀላሉ እንዳንራመድ ጣዖት አይሆንብን ምን? የሰው ልጅ በክርስቶስ ሰው መሆን ነጻ በወጣበት በአዲስ ኪዳን ዘመን፣ በዓ መተ ምሕረት ማኅፀን እየኖረ ዳግም ወደ ነጻነት አልባ ምድር እየገባ አይደለምን? ሐዋርያው እንዲህ ይላል «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፡፡ አሮጌው ነገር አልፎአል» /፪ቆሮ.፭፥፲፰፤ ገላ.፭፥፩/ መማርም ይሁን ማስተማር፣ ማጥ ናትም ይሁን ማስጠናት፣ መግዛትም ይሁን መሸጥ በጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል በመትጋት በመታመን ይበልጥ አትራፊ ነት ነው፡፡

ጠያቂያችን በጥያቄያቸው መዝጊያ ላይ የማነቃቂያ ነገሮችን ተጠቅሞ በትምህ ርት ስኬታማ መሆን በቤተክርስቲያን የተለመደ አይደለም ወይ? ይላሉ፡፡ በህብ ትም ሆነ በእውቀት በአቋራጭ ለመበል ጠግ የሚደረጉ ጥረቶች እንደቀላል የሚ ታዩ አይደሉም፡፡ በአንዳንድ የአብነት ትምህርት ቤቶች በዕፅ ተጠቅመው በፍ ጥነት ወደ ላቀ ደረጃ ለመድረስ የሚሞ ክሩ በጣት የሚቆጠሩ ደቀ መዛሙርት መኖራቸው የሚካድ አይደለም፡፡ ቤተክር ስቲያን ግን ተግባሩን የምታወግዘው እንጂ የምትደግፈው አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተፈቀደ አይደለም፣ የግል ስሜትና ድረጊት እንጂ፡፡

የመጨረሻ ውጤቱም በአእምሮና በመ ንፈስ አለመረጋጋት መፍጠሩን የተገበሩ ትም ያስተገበሩትም ያውቁታል፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተመለከትነው ጫት ከመቃም ጋር ተመሳሳይነት ያለው አይደለም፡፡ በሱሰኝነት ወጥመድ መያዝ በአካላዊ፣ ሞራላዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ መዝ ፈቅ ከመንፈሳዊነት፣ ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን በአፍአ መቆም የመሳሰሉት ፈተናዎች በጫት መቃም ቁጥጥር ሥር ለዋሉ ወገኖች የተበረከቱ መሆናቸው መካድ የለበትም፡፡

### ማጠቃለያ

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከባሕርየ መላ እክት ጋር ባለው ተዛምዶ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ለይቶ ማየት እንደሚገባው ማመን፤ በሕንጻ እግዚአብሔርነቱ ማኅደረ እግዚአብሔር መሆኑን ማሰብ፤ በሥርዓተ አምልኮው ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ነገ ሮች መሸሽ፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እን ዲሁም አእምሮአዊ ችግሮችን ሊያባብሱ የሚችሉ አደጋዎችን ከጽድቅና ከኃጢአት ጋር እያወዳደሩ መደፋፈር እንዳይኖር መጠንቀቅ፤ ግብረ አሕዛብን የማለማ መድ ተልእኮ ካላቸው ወገኖች መራቅ፤ ከሁሉም በላይ ለሥርዓተ ክርስትና ቅድ ሚያ መስጠት እንጂ አንድን ነገር መጨ ረሻውን ሳያዩ መጀመሪያውን፣ ጉዳቱን ሳያዩ ጥቅሙን ብቻ እየተመለከቱ መጓዝ ካለ አደጋ ነው፡፡ «ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ የለም፤ ነገር ግን አካሉ ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ… ይመግበዋል ይንከባከ በውማል» /ኤፌ.፭፥፳፱/✥

*በቸርነቱ ይጠብቀን*


ከሰሜን አሜሪካ ምን ይደመጣል?
መካነ ድር /website/
http://www.mahiberekidusan.org
www.tewahedomedia.org

ሬድዮ
ለኢትዮጵያና አካባቢዋ
17.690 MHz አጭር ሞገድ
ዘወትር ሰኞ
ከምሽቱ 4:00-5:00
(10pm-11pm)

አትላንታ
860 AM
WAEC
Sundays
7:30 pm - 8:00 pm EST

ዲሲ
1390 AM
Abyssinia Radio
Saturdays
7pm - 7:30pm EST

ዴንቨር
670 AM
KLT Radio
Sundays
8:00 pm - 9:00pm EST




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ቃለ ሊቃውንት

- ቅቤ ካይብና ካንት እንዲለይ፤ በላይም እንዲሆን ጻድቅም ሰው እንደዚያ ነው።
- ሸንኩርትና ድንች ፍሬያቸው በሥራቸው እንደሆነ፤ ጻድቃንም በሥራቸው ለማፍራት የአምላካቸውን ነገር በልባቸው ይተክላሉ።
- የተምር ፍሬ እንዲጣፍጥ የጻድቃንም ሥራ እንደዚያ ነው።
- ቅል በዝናም ይበቅላል፤ ሸክላም በውኃ ይሠራል፤ ኋላ ግን ሁለቱም ለውኃ ማደሪያ ይሆናሉ።
- ከቡላድና ከድኝ ከእንጨትም እሳት ወጥቶ እንዲቃጠል፤ ጻድቃንም ቢቆጡ እሳት ይዘንማል።
- ሙሽራ በጫጉላዋ ውስጥ እንደምታምርና ደስ እንደምትሰኝ ጻድቃንም በመንግሥተ ሰማያት እንደዚያ ናቸው።
- ጣዝማ እጅግ ብልህ ናት፤ መሬት ቀዳ ገብታ እንደዚያ ያለ መድኃኒት የሚሆን ማር ትሠራለች። ምነው እናንተ ሰዎች ወይ ከፈጣሪ ወይም ከሰው ብልሀትን አትፈልጉምን።

*አለቃ ዘነብ*

*መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ መንፈሳዊ*

### ግእዝ ጉባኤ ቃና

ነነዌ አእመርነ በከመ ኮንኪ ሕምምተ፣
ኵሉ ርእስኪ አምጣነ ኮነ እሳተ።

*ትርጉም፦*

ነነዌ! ሕመምተኛ እንደሆንሽ በወቅን
ራስሽ ሁሉ እሳት ሆኗልና።

*ምስጢር፦*

አንዲት ታማ የተኛች ሴት ራሷ ሁሉ እሳት ሲሆን /ሲፋጅ/ ራሷን የዳሰሳት ዘመዷ «በጣም ታመሻል ሁለንተናሽ እሳት ሆኗል» ይላታል። ከሰማይ የወረደው እሳት በነነዌ ከተማ ራስ ላይ አንዣቦ ሳያቃጥላት ወደላይ መመለሱ በቅኔው ተወስቷል።

/የግእዝ ቅኔያት ፪ኛ መጽሐፍ፤
ገጽ. ፩፻፸፮-፩፻፸፯/

### ሰማዕትነት

በቅብጥ ስንክሳር ከተጠቀሱት ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውስጥ ግማሽ የሚሆኑት ከ፪፻፺፮ - ፫፻፲፭ ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መከራን የተቀበሉ ናቸው። ታሪክ ጸሐፊው ላክታንቲየስ /Lactantius/ «ሰማዕትነት ኢ-ክርስቲያኖችን ለማስተማርያና ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲመጡ፤ ለአገልግሎትም እንዲተጉ የሚያበረታታ ታላቅ መሣሪያ ነው። ሰማዕትነት ሰማዕታት ለፈጣሪያቸው ያላቸውን ታላቅ ፍቅርና ክብር እስከ ሞት ድረስ የሚያሳዩበት ብቸኛ መንገድ ነው። እነርሱን በማየት ብዙ ከሐድያን ወደ ክርስትናው ዓለም ይመለሱ ነበር» ብሏል። ሕይወታቸውን ለእውነተኛዋ ወንጌል አሳልፈው የሰጡ ሰዎች የክብር ቦታቸው ከቀዳማውያን ክርስቲያን አባቶቻችን ጋር መሆኑን ተረድተን ለእውነት የቆምን ስንቶች እንሆን?✦

*/አዜብ በርሄ፤ ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ፤ ገጽ. ፲፫/*

### ብሂለ አበው

- «ያለወጣቶች የምትጓዝ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ራእይ የሌላት ናት» */ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ/*
- «ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር የምስጢር ሀገሩ ነች ልጆቼ የኢትዮጵያን ነገር አደራ» */ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ/*
- «የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አንብቧት፣ ተርጉሟት፣ ኑሩባት ያን ጊዜ ሕይወት ታገኙላችሁ» */ብፁዕ አቡነ ናትናኤል /አርሲ/*
- «ቤተ ክርስቲያን የፍግ እሳት ናት ጠፍታለች ስትባል ህያው ትሆናለች» */ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ/*

*ዲ/ን ተመስገን ዘገየ*
*/ደቡብ ጎንደር /ወረታ/*

### በምኔ ልስገደው

በዚህ በፈጠጠው
በዐይኔ የማየውን፣
እሱኑ ስከተል
ነገ የሚያልፈውን፤
ደከመኝ ሆነና
የዛሬ ነገሬ፣
አንዳችም ሳልሠራ
ቢተሳሰር እግሬ፣
ዕድሜዬ ገፋና
ቢንቋቋ ወገቤ፤
አለፈብኝና
የጉብዝና ጊዜው፣
ዛሬ ትዝ ቢለኝ
ጌታን እንዳስከፋሁ፣
ስለዚህ ኃጢአት
በምኔ ልስገደው?

### የሰው ጧፍ

በቀደሙት ጻድቃን ሕይወት
እንደሳብከን፣
ዛሬም የሚያበሩ የሰው
ጧፎች ስጠን።

### መራኝ መሪ ሆኖ

የእውነት ብርሃንህ
ከዐይኔ ተሰውሮ፣
መጠቆሚያው በትር፣
ወድቆብኝ ተሰብሮ
በገዛ ጥፋቴ
እጅና እግሬ ታስሮ፣
ወንጌልህ ታደገኝ
መራኝ መሪ ሆኖ።

*አቤል ሰሎሞን*
*ከአዲስ አበባ*

### ለኔ ነው እንባ የሚያሻው /ቁጥር ፩/

የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ...
በጎቼን አሰማራ
ግልግሎቼን ጠብቅ ብሎኝ፣
የዘለዓለም የኪዳን ቃል
አደራውን በጄ ሰጥቶኝ፤
እምነት ፍቅርን
ከተስፋ ጋር አጣቅሼ፣
የተጠማን አጠጥቼ
የታረዘውን አልብሼ፣
የመንግሥቱን ወራሽ ሁሉ
ለንስሐ ሳልጠራሁኝ፣
የመስቀሉን የፍቅር ቃል
ለተራብ ሳልመግብኩኝ፣
ፈሪሳዊ ሆኖ ግብሬ!!
አባት ሳይሆን አባይ ሆኜ
... ክህነቴን ሳስነቀፍኩኝ፣
የመንጋውን እረኛነት
አደራዬን ለረሳሁኝ፣
ለ'ኔ ነው እንባ 'ሚያሻኝ
ለእንባ ደሀው
እንባ ስጡኝ።
የነቢያት መጠምጠሚያ
የሐዋርያቱ ጥላቸው፣
ፈውስ ሲሰጥ፣ ደዌ ሲነቅል
ሙት ሲያነሣ እምነታቸው፣
የኔ ግብር፣ የኔ ሥራ
ከጥምጥሜ ያላለፈው፣
በብብቴ መስቀል ይገዬ
ልቤ በቂም የጠቆረው፣
እልፍ በጎቼን ከጉሮኖ
አስወጥቼ
በሜዳ ላይ በትኛቸው፣
ጎኔን ደልቶት ለተኛሁኝ
የተኩላ እራት አድርጊያቸው፣
የራስ ምስል፣ የራስ ክብር
የራስ ጣዖት ለማመልከው፣
ለኔ እንጅ – እንባ
'ሚያሻው፤
አገር ሆኖ የማነባው።

*እንዳለም አባተ*
*/የዐደ ልጅ/*




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

«ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ» መኃ.፯፥፰

የመጨረሻው ክፍል

# አዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጠቀሜታው ምንድን ነው?

ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ



*ነገረ ቃልከ ያበርህ ወያጠብብ ሕፃናተ፣ አፉየ ከሠትኩ ወነፋስየ አናሕኩ*

ባለፉት እትሞቻችን የትርጉምን ምንነት፣ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ቦታ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት መቼ ተተረጐሙ? የሚሉትንና በመጨረሻም «አዲሱ የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለምን አስፈለገ?» የሚሉትን ነጥቦች ለመቃኘት ሞክረን ነበር:: የመጨረሻው ክፍላችን በሆነው በዚህ ዕትማችን ደግሞ አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያመጣቸውን ለውጦች፣ ቁጥሩን፣ ስብጥሩንና ሌሎችን ጉዳዮች ለማየት እንሞክራለን::

## ምን አዲስ ነገር አለው?

አዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ገበያ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰዎች በተከፍሎ ልብ ይመለከቱታል:: አንዳንዶች «የራሳችን የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ» ታተመ ብለው ከይዘቱ ምርመራ በፊት ሲደሰቱ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህስ ቢሆን ትክክል ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለው? እያሉ ይጠራጠሩታል:: ሌሎች ደግሞ ከሚያውቋቸው ጥቅሶች ጥቂቶቹን በመመርመር አንዳንዴ «አጉደለ» ሲሉት ሌሎች ደግሞ አተረፈ ይሉታል:: «ጥሩ ነው» የሚሉትም አይጠፉም:: ከሊቃውንትም አንዳንዶቹ ጥያቄ ማንሣት ቢጀምሩም አብዛኛዎቹ ገና እየመረመሩት ያሉ ይመስላል:: በሁሉም አቅጣጫ ግን ልብን ማሳረፍ ላይ ገና የተደረሰ አይመስልም::

## «የእኛ»ነቱ ጉዳይ

የተሐድሶ አራማጁና የክልኤ ባሕርይን ትክክለኛነት የሚለፍፈው የጮራ መጽሔት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን መጽሐፉን «የእኛ ነው» ማለታቸው አሳስደሰተውም:: መጽሔቱ በቁጥር ፴፯ ዕትሙ በርእሰ አንቀጹና በ«ወቅታዊ ውይይት» ዓምዱ እንደ ገለጸው «ቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮዋን ለመደገፍ ያሳተመችው» ሲል ይተቸዋል:: በተለይም በርእሰ አንቀጹ ክልኤ ባሕርይነቱን በስውር በሚገልጽበት የተለመደ ስልቱ «ለትውልደ አውጣኬ እንዲስማማ ለማድረግ የተዘጋጀ» ይለዋል:: /አውጣኬ «መለኮት ሥጋን ዋጠው፣ መጠጠው» የሚል ትምህርት የነበረው መናፍቅ ነው:: ይሁን እንጂ ካቶሊኮቹ /በተለይ ምዕራባውያን/ ኦሬንታሎቹን አውጣኪያውያን በማለት ያለ ስማችን ስም በመስጠት ራሳቸውን ያልተሳሳቱ ለማስመሰል ይጥራሉ::/ በዚህም እነርሱ /ጮራዎች/ ውሉደ ልዮንን የሚያራምዱ ሐዲሳን ሉተራውያን መሆናቸውን ገልጠውልናል:: ለማንኛውም ጥያቄያቸውን እንመልከተው::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቶች

ይህን ርእስ የተጠቀምኩት «የተለያየ መጽሐፍ ቅዱስ አለ» ለማለት አይደለም፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተዘጋጁበት ሁኔታና ዓላማ በአጥኚዎች ዘንድ የተለያዩ አከፋፈሎች አሏቸው ለማለት እንጂ:: በዚሁ መሠረት የተለያየ ስያሜ ስለሚሰጣቸው ይህንኑ ማንነታቸውን እንደ ዓይነት ቆጥረን እንመለከተዋለን::

አጥኚዎች እንደሚሉት ከሆነ እስካሁን በዓለም ላይ ቢያንስ ከዐሥር በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቶች አሉ::

፩. ትውፊታዊ መጽሐፍ ቅዱስ /Traditional Bible/፡- ከጥንት በቅብብል የመጣውና እጅግ ጥቂት የግርጌ ማስታወሻ ታክሎበት የሚታተም፤

፪. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ /Study Bible/፡- ይህ ለጥናት ወይም መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቅ ለመረዳት እጅግ ብዙ





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የግርጌ እና የማብራሪያ ጽሑፎች ታክለውበት የሚዘጋጅ ነው:: በእኛ የአንድም ትርጓሜዎችን በዚህ ክፍል መመደብ ይቻል ይሆናል::

፫. ማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ /Reference Bible/:- ይህ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ምንባብ /ከጥሬ ዘሩ/ በኋላ ማጣቀሻ የሚሆን ዝግጅት ያለው ነው:: ይህም ማለት ጉዳዮችን እንደ መዝገበ ቃላት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል እያስቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የት የት እንዳሉ የሚነግር /Index/ ነው:: በፈረንጆቹ ኮንኮርዳንስ /Concordance - የቃላት ዝርዝር/ ይሉታል::

፬. ሕይወት ተኰር መጽሐፍ ቅዱስ «Place in Life Bible»:- ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ጥቂት ገጾችን ከመካከል መርጦ ትምህርቶችን፣ ስብከቶችን ወይም የተለዩ ጸሎቶችን በማሰባጠር የሚዘጋጅ ነው:: በእኛ ሀገር በየመካከሉ ሥዕል እንደሚደረግበት የብራና መጽሐፍ ማለት ነው:: ዓላማውም አዳዲስ አማኞች፣ ልውጦች የተለየ ሁኔታ ውስጥ ያሉ /በሽተኞች፣ ስፖርተኞች .../ ሰዎች በእነዚያ ማብራሪያዎች እንዲማሩ፤ ጸሎቶቹን በመጸለይ ወደ ታሰበው ሁኔታ ይሸጋገሩ ዘንድ ለመርዳት የሚዘጋጅ ነው::

፭. የዓመት መጽሐፍ ቅዱስ /One Year Bibles/:- እነዚህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን በዓመቱ ቀናት /በ፫፻፷፭ ቀናት/ ከፋፍለው ለየዕለቱ በማዘጋጀት አንድን ሰው ዓመቱን በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነብ ለማገዝ የሚዘጋጁ ናቸው::

፮. የመምህራን መጽሐፍ ቅዱስ /Pastor's Bible/:- እነዚህ ደግሞ በተለይ ለምስራባውያን የተመረጡ ትምህርቶችን አካትተው የሚዘጋጁ ናቸው:: ዓላማው መምህሩ ወደ ሆስፒታል ቢሔድ፣ ቀብር ቢሔድ፣ ሰርግ ቢሔድ፤ ሳይቸገር ለዚህ የተዘጋጀውን አውጥቶ ለማስተማር የሚዘጋጅ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ለጥቂት መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች መልሶችን የያዘም ሊሆን ይችላል::

፯. የሕፃናት መጽሐፍ ቅዱስ /Children's Bible/:- ይህ ደግሞ ሥዕሎችን፣ ካርታዎችን፣ እና ቀለል ብለው የተዘጋጁ ታሪኮችን የያዘ ሲሆን ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሱን ላይዝ ይችላል:: በእኛ ሀገር «የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ» ተብለው እንደ ታተሙት ያሉትን የሚያመላክት ነው::

፰. ትይዩ መጽሐፍ ቅዱስ /Parallel Bible/:- ይህ ደግሞ በተለያዩ ዓምዶች በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ የሚወጣ ነው:: ለምሳሌ በእኛ ሀገር በግራው ዓምድ ግእዙን በቀኙ ዓምድ አማርኛውን ይዘው እንደ ታተሙት ያለ ሲሆን እስካሁን ከወጡት በዓለም ላይ ከፍተኛ የቋንቋ ቁጥር የታየው ስምንት ነው:: ይህም ማለት በስምንት አምዶች ትይዩ አድርጎ በተለያዩ ስምንት ቋንቋዎች የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው::

፱. ቅደም ተከተላዊ መጽሐፍ ቅዱስ /Chronological Bible/:- ይህ ደግሞ የሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ግንዛቤ ለማሳደግ ሲባል ነገሮችን በተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት አድርጎ በትረካ /Naration/ መልክ የሚዘጋጅ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነት ነው::

፲. ልዩ ልዩ መጽሐፍ ቅዱሶች /Special Bibles/:- እነዚህ በተለየ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎችን ፍላጐት ለማሟላት ተብለው የሚዘጋጁ «ልዩ» ሊባሉ የሚችሉ ዝግጅቶች ናቸው:: ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት መሪዎችን ወይም አመራሮችን ለመፍጠር ሲታሰብ የመሪነት /የአመራር/ መጽሐፍ ቅዱስ /Leader ship Bible/ ይዘጋጃል:: የቁልፍ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስም ከእነዚህ መካከል ይጠቀሳል:: ለምሳሌ የዕብራይስጥ ጽርእ ቁልፍ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ /Hebrew – Greek key word Bible/

ከላይ ያየናቸውን ሁሉ መጥቀስ ያስፈለገው መጽሐፍ ቅዱስ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር የኖረና የምናውቀው መሆኑን ለመግለጽ ነው:: በእኔ አመለካከት ከላይ ከጠቀስናቸው ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በእኛም ዘንድ የሚታወቁ ናቸው:: ትውፊታዊ /Tradational/ የሚባለው ከጥንት ጀምሮ ያለን ሲሆን የጥናት የሚባለው ከአቀራረቡና ከቅርጹ በቀር የእኛ የአንድምታ ትርጓሜ ነው:: እነርሱ የዓመት የሚሉትም በእኛ ግጻዌ የምንለውን የሚመስል ነው:: ይህ ቀደም ብሎ የነበረው የእኛ ግጻዌ የተዘጋጀበት ዓላማ ለቅዳሴና ለጸሎት ጊዜያት ቢሆንም በዓመቱ ቀናት ሊነበቡ ይገባቸዋል ብሎ በብቁ ምክንያት የመረጣቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት የያዘ ነው:: የሕፃናት መጽሐፍ ቅዱስ ያልነው በቅርቡ /በንጉሡ ዘመን/ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አማካኝነት የታተሙትን ባለ ሦስት ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያዎችን የሚመለከት ነው። ትይዩው ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ቢያንስ በግእዝና በአማርኛ አለን:: ከልዩ ልዩ ውስጥ ሊመደብ የሚችል ደግሞ ግብረ ሕማማት አለን:: ግብረ ሕማማት ለተወሰነ ወቅት ብቻ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስን ለዚያ ጊዜ በሚሆን መንገድ በማቀናበር የተዘጋጀ ነው:: ሌሎቹም ቢጠኑ የራሳቸው ምልከታ ይኖራቸዋል::

ይህን ከተረዳን በኋላ አሁን የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ከዐሥሩ በየትኛው ይመደባል የሚል ካለ በመጀመሪያው /ትውፊታዊው/ የሚባለው ነው:: ምክንያቱም ከግእዙ ወደ አማርኛ ከመተርጐሙ በቀር ቤተ ክርስቲያኒቱ ከጥንት ከብሉይና በኋላም ቢያንስ ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምራ ይዛቸው የመጣቻቸውን አሥራው መጻሕፍት እጅግ ከጥቂት የግርጌ ማስታወሻዎች ወይም የሕዳግ ማነጻጸሪያዎች ጋር ብቻ ይዞልን የቀረበ ነውና::

ታዲያ በዚህ መንገድ የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ ሰዎቹን ያስከፋቸው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሣል:: የጥያቄያቸውን ሁኔታ ከሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው «ቁጥር» ላይ ለምን ተጨመረ? ... የሚል ነው:: ይህን ጥያቄ «ቁጥር» በሚል ርእስ ስለምንመለከተው ለጊዜው አልፈዋለሁ:: ሌላውና ብዙ ጊዜ እየደጋገሙ ሊያነሡት የሚፈልጉት ግን ትምህርተ ተዋሕዶው ለምን ተዛብቶ አልወጣም የሚል ይመስላል:: «እኛግዲህ ለአዲስ ኪዳን አብነት በሆነው በግሪኩም ያለውን በተጨማሪም በ፲፱፻፷ ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ሓላፊነት ታትሞ ሲሠራበት የቆየውን ቃል ከ፰፻ ዓ.ም

> አንዳንድ ሰዎች የተጨመረና የተቀነሰ መኖሩን የስሕተት ማስረጃ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ:: እውነት ለመናገር እንዲህ ያለ አሳብ አሳፋሪ ብቻ አይደለም፤ አሁን አሁን ነውርም ሊሆን ምንም አልቀረውና:: ግሪኩ ብቻ ከተለያዩ ቅጂዎች አንጻር ቢጠና እንኳ ይኽን የመሰሉ ችግሮች መገኘታቸው አይቀሬ ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ብቻ እንዲተረጐሙ ያስገድድ ነበር:: በዚህም መሠረት በአብዛኛው የፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚቀበላቸው ፴፱ መጻሕፍት /በአይሁድ አከፋፈልና አቆጣጠር ፳፬ቱ/ በተለያየ ጊዜ ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጐሙ ከተመሳሳይ ምንጭ እንኳ ተቀድተው የተለያዩ ትርጉሞችን የሚሰጡበት አጋጣሚ ብዙ ነው::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

መጽሐፍ ቅዱስ ማውጣት <ለትውልደ አውጣኪ መሠረተ እምነት እንዲስማማ ለማድረግ ነው> የሚለውን ሐሜት እውነተኛነት ያረጋግጣል እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል::» /ሎሬ ቁ.፴፮፣ ገጽ.፮/ ከላይ በተገለጸው መንገድ አቋሙን የገለጸው የክልኤ ባሕርይ ባዮችና የዘመኑ «አዳሾች» ንን ባዮች አስተሳሰብ ሥጋት እንዲሆነው የቤተ ክርስቲያኒቱም አካሔድ ለእርሱ እንዳልተመቸው አመላካች ነው::

## የይዘት ለውጥና አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ

ለምን አዲስ ተዘጋጀ የሚለው ጥያቄ የጋራችን ቢሆንም ለዝግጅቱ ምክንያት የሆኑትና በዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ የኅትመት መግቢያ ላይ የተገለጹትን ሁለት ምክንያቶች በቀደመው ዕትማችን ተመልክተናል:: ይሁን እንጂ አሁንም አንባብያን ይጠይቃሉ፤ ምን ለውጥ ታየ? እያሉ::

አንባብያን ሁልጊዜም መዘንጋት የሌለብን አንድ ነገር አለ:: ይኸውም በቀደመው እትማችን ላይ ስለትርጉምና መንፈስ ቅዱስ ስላለው ሚና የተገለጸውን ማብራሪያ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት /ርዳታ/ የተጻፉ እንደመሆናቸው መጠን በዚያው በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ይተረጎማሉ ብለናል:: ይህም የመንፈስ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን የታዛዦቹን የሰዎችንም ድርሻ ይጠቁመናል:: ከጥንት ጸሐፊዎቹ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ያለብማቸዋል /ያሳውቃቸዋል/፤ ይመራቸዋል፤ ይቃኛቸዋል፤ እንጂ ራሱ ብርዕ ይዞ ቀለም በጥብጦ አይጽፍም:: ይህም ማለት ቁሳዊ በሆነው ነገር መከተቡና ሰዋዊ በሆነው ቋንቋ ማስፈሩ የሰዎቹ ድርሻ ነበር:: በትርጉሙም ይኸው ነው:: ስለዚህ ቋንቋውን የመረዳት፣ ሰዋስውን ዐውቆም የመተርጐም ሥራ የሰውየው ድርሻ ነው ማለት ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ማለት ያለ ሰውየው ዕውቀትና እምነት የሚፈጸም አይደለምና:: ይህን በድጋሜ በትንሹም ቢሆን ማስታወስ ያስፈለገው ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ሲተረጐም ቀርቶ ወደ አንድ ቋንቋ /ከአንድ ቅጂ ብቻ/ በተለያየ ጊዜ፣ በተለያዩ ሰዎች ብቻ ቢተረጐም ከላይ ከጠቀስናቸው የሰው ድርሻዎች የተነሣ መጠነኛ ልዩነት /ቋንቋዊ፣ ሰዋስዋዊ፣ .../ የመሳሰሉት ልዩነቶች አይቀሬ መሆናቸውን ለመጠቆም ነው::

በአሁኑ ትርጉምም ከዚህ ዓይነት ልዩነቶች አንሥቶ ሰፋ ያሉ ልዩነቶችን ልንመለከት እንችላለን:: በዚህ መሠረት በዚህ ጽሑፍ ከቋንቋ ችሎታ ልዩነት፣ ከሰዋስው አገባብና ከመሳሰሉት ጋር ያሉትን ልዩነቶች ለዛሬው አንመለከታቸውም:: ይልቁንም መሠረታዊ የሆኑትን የቃላት፣ የሐረጋትና የዓረፍተ ነገሮች መጨመርና መቀነስ መኖሩንና አለመኖሩን እንዲሁም ቀደም ብለን ከጠቆምነው የመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቶች አንጻር ቁልፍ ቃላት እንዴት ተተ ረጉመዋል የሚለውን እንመለከታለን::

*ሀ. ቃላት:- ቃላት የተካሔዱ ለውጦችን ለማየት ያህል ገላትያ ፭÷፲፱ ጀምሮ የተገለጹትን የሥጋ ሥራዎች ዝርዝር እንመልከት::*

| 1<br>የቀድሞው መ/ቅ | 2<br>አዲሱ መ/ቅ | 3<br>ግእዝ |
|---|---|---|
| የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም | የሥጋም ሥራው ይታወቃል፤ እነርሱም | ወይትዐወቅ ምግባሩ ለሥጋ |
| ዝሙት | ዝሙት | ዝሙት |
| ርኩሰት | ርኩሰት | ርኩሰት |
| መዳራት | መዳራት | ወምርዓት |
| ጣዖትን ማምለክ | ጣዖትን ማምለክ | ወአጣዕዎ |
| ምዋርት | ሥራይ ማድረግ | ሥራይ |
| ጥል | መጣላት | ጽልዕ |
| ክርክር | ኩራት | ትዝኅርት |
| ቅንዓት | የምንዝር ጌጥ | ትውዝፍት |
| ቁጣ | ቅናት | ቅንዓት |
| አድመኛነት | ቁጣ | መዓት |
| መለያየት | ጥርጥር | ኑፋቄ |
| መናፍቅነት | ፉክክር | ተቃኅዎ |
| ምቀኝነት | ምቀኝነት | ተሐምሞ |
| መግደል | መጋደል | ተቃትሎ |
| ስካር | ስካር | ስክረት |
| ዘፋኝነት | - | - |
| ይህንም የሚመስል | ይህንም የመሰለው ነው | ወዘአምሳሊሁ ለዝንቱ |

ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ ላይ በተራ ቁጥር ፩ የተቀመጠው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን በእርሳቸው ስም መቅድም ተጽፎለት የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ሁለተኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለው ደግሞ አዲሱ ትርጉም ነው:: የመጨረሻው ለማነጻጸሪያነት የቀረበው የግእዙ ዘርዕ ነው:: በቀረበው ምሳሌ መሠረት አዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥታ ከግእዙ እንደተተረጐመ ከቃላቱና ከቅደም ተከተላቸው መረዳት ይቻላል:: ይሁን እንጂ ከቀደመው ኅትመት ጋር ስናነጻጽረው ደግሞ መጠነኛ ልዩነቶችን እንመለከታለን:: ለአብነት የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል::

*፩. መደመርና መቀነስ:-* ዘፋኝነት በጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሲኖር በዚህኛው ግን የለም:: ግእዙም ላይ እንደሌለ ግን ያስተውሉ::

:- «አድመኛነት፣ መለያየትና መናፍቅነት» የሚሉት የድሮው መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በምስጢር የማይራራቁ ቢሆንም ሦስት ሆነው ቀርበዋል:: በአዲሱ ግን ያው «ጥርጥር» በሚለው ብቻ የተገለጹ ይመስላል:: ስለዚህም ቢያንስ ሁለቱ ቃላት /ጥሬ ቃሉን ብቻ ለሚፈልግ/ በአዲሱ ትርጉም የሉም ሊባሉ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ «ኩራት»ና «የምንዝር ጌጥ» የሚባሉት በቀድሞው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሉም::

*፪. ቅደም ተከተል:-* ቅደም ተከተሉንም ስንመለከተው በጥንቱ «ክርክር» የሚለው ያለበትና በአዲሱ «ፉክክር» አራት ቃላትን መካከል ላይ በማስገባት ተራርቀዋል:: «ቅንዓት» እና «ቁጣ» ደግሞ በአዲሱ ላይ በአንድ ቃል ዘግይተዋል::

*፫. ውክልና:-* ውክልና የምለው ቃላቱ የሚያስተላልፉትን መልእክት የሚመለከተውን ጉዳይ ነው:: በዚህ በኩል የአዲሱ ትርጉም ቢያንስ ሁለቱ ቃላት ብዥታን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: «ፉክክር» የሚለው ቃል አሉታ ትርጉምን አያሳይም:: በግእዙ «ተቃኅዎ» ተብሎ የተገለጸውን ይህን ቃል የጥንቱ «ክርክር» በማለት ቢያንስ አሉታነቱን ያሳያል:: የአንድምታ ትርጓሜው ደግሞ «ሥጋዊ ፉክክር» በማለት ገላጭ ቃል በመጨመር አሉታነቱን አሳይቷል:: ከዚህም በተጨማሪ «ተቃትሎ» የሚለውን የድሮው መጽሐፍ ቅዱስ መግደል በማለት አሁንም አሉታ መሆኑን ይጠቁማል:: አዲሱ ግን «መጋደል» በማለት ለሰማዕትነት ከምንጠቀምበትና ለክብር ተቀባዩ መናኝ ከምንጠቀምበት ቃል ጋር አምታቶታል::

መሠረቱ ግእዙ እንደመሆኑ መጠን «ተቃትሎ» የሚለውን የተደራራጊ ቃልን ሲተረጉሙት «አድራጊ» ብቻ በማድረጋቸው «መጋደል» የሆነባቸው ይመስላል:: አገባቡን ጠንቅቆ ተደራራጊ ቢሆን ግን «መገዳደል» ይሆንና ሰዋስውን ብቻ ሳይሆን ትርጉሙንም ጨምሮ ይዞ ይመጣ ነበር:: ይህ ማለት ግን የጥንቱ ትርጉም እነዚህ ቃላት ላይ ትክክል ነው ማለት አይደለም:: የጥንቱን ስንመለከተው ደግሞ አሉታነቱን ቢያሳይም የግሡን ተደራራጊነትና የባለቤቱን



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ብዙነት ስለማያመለክት እርሱም ቢሆን ግእዙን አልተከተለም፡፡ «መግደል» ነጠላ ባለቤትን እንጂ «መገዳደል» የሚለውን የብዙዎች ሁኔታ አይገልጽም፡፡ ባይሆን ከግእዝ አልተተረጐምኩም ብሎ ካልዳነ በቀር፡፡

*፬. የቃላት ምርጫ፡-* ይህ ደግሞ አንድን ድርጊት ለመወከል የሚጠቀሙበትን የቃላት ምርጫ የሚመለከት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ግእዙን መነሻ አድርገን ከወሰድነው «ወይትዐወቅ ምግባሩ ለሥጋ» የሚለውን የጥንቱ «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው» በማለት «ይትዓወቅ»ን «የተገለጠ» ሲለው አዲሱ ደግሞ በቀጥታ «ይታወቃል» ሲል ተርጉሞታል፡፡ ምንም እንኳን ቃላቱ የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን በራሳቸው ሲታዩ የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ ቢችሉም በዚህ ዓረፍተ ነገር ባላቸው ዓውዳዊ ፍች ግን የሚራራቁ አይደሉም፡፡

ከዚህም በላይ አግባቡን ከተመለከትን «ምግባሩ ለሥጋ» የሚለውን ሲተረጉሙ የግእዙን የ«ለ» ሞያ ወደ አማርኛ ሲያመጡ የተለያዩ ይመስላሉ፡፡ በእኔ መረዳት በጥንቱ ላይ «የሥጋ ሥራም» ብሎ ተጠቅሟል፡፡ አዲሱ ትርጉም ላይ ግን ዘርፍ ደፊነቷን ለሥጋ በማድረግ «የሥጋም» በማለት ተጠቅሞባታል፡፡ ከዚህም በላይ «ተግባሩ» የሚለውን የግእዝ ዘርዛሪ ቃል በአማርኛም «ሥራው» በማለት በወንድ ጾታ ሦስተኛ መደብ ዘርዛሪ አድርጎ አምጥቶታል፡፡ በዚህም አዲሱ ከዚያኛው የተሻለ ነው ሊባል ይችላል፡፡ የ«ለ»ን ሰፊ ብዙ ሞያ ግን ለቅኔ መምህራኑና ለግእዝ ሰዋስው ሊቃውንት መተው ይቀላል፡፡ በሌላ ቋንቋ ትርጉም በቀላሉ መሠረተ ቃላቱን ብቻ በማወቅ/ ሊተገበር የማይችል መሆኑን ይህን ከመሰሉ ሁኔታዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ቃላትን በተመለከተ ከላይ የተመለከቱትን የመሰለ ልዩነት በብዛት ሊኖር የሚችል ቢሆንም የልዩነቱ ምንጭ ግን ከላይ በጠቀስነውና ግእዙን ከመከተል የመጣ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ሰፊው ጉዳይ ወደፊት አጥኚዎችን ይጋብዛል፡፡ በተለይም የትርጉም /Translation/፣ የፊሎሎጂ፣ የሥነ ልሣንና የእኛም የቅኔና የግእዝ ሰዋስው ባለ ሙያዎችና ተመራማሪዎች ብዙ ዲግሪ ሊያሰጣችሁ የሚችል መስክ መከፈቱን እንደማትዘነጉት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

*፭. ሐረጋትና ዓረፍተ ነገሮች*

ለዚህ አንድ ምሳሌ ብቻ ተመልክተን አካሔዱንና አጠቃላይ ሁኔታውን ብቻ በመጠቆም እናልፋለን፡፡ በአሪት ዘዳግም ላይ በተቀመጠው የሙሴ ጸሎት ላይ «ይትፌሥሑ ኲሎን ሰማያት ኅቡረ፡፡ ወይሰግዱ ሎቱ ኲሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር» የሚለው ንባብ ቀደም ባሉት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ የለም፡፡ በአሁኑ ግን ኦሪት ዘዳግም ፴፪÷፵፫ ላይ «ሰማያት ሁሉ በአንድነት ደስ ይላቸዋል፤ የእግዚአብሔርም መላእክት ሁሉ ይሰግዱለታል» ተብሎ ተሟልቶ ተቀምጧል፡፡

ከዚሁ ሳንወጣ በአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚሁ ከዘዳግም ፴፪ ቁ.፵፬ ላይ «ሙሴም በዚያች ቀን ይህችን መዝሙር ጻፋት፤ ለእስራኤልም ልጆች አስተማራት» የሚለው በጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ የለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በጥንቱ የነበሩ በዚህኛው የሌሉም አሉ፡፡ እዚሁ ዘዳ. ፴፪÷፶፪ ላይ በጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ «…ምድሪቱን ፊት ለፊት ታያለህ እንጂ ወደዚያች እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደ ምሰጣቸው ምድር አትገባም» የሚለውን በአዲሱ ስንመለከተው «ምድሪቱን ፊት ለፊት ታያለህ እንጂ ወደዚያች ምድር አትገባም» ተብሎ ተገልጾአል፡፡ ይህ ማለት በቀደመው ላይ «እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደ ምሰጣት ምድር» የሚለው በአዲሱ ላይ የለም ማለት ነው፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን የመሰሉ ብዙ ክስተቶች ወይም ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ ይህ የሆነው በምን ምክንያት ነው? የሚለውን እንመልከት፡፡

ብቸኛው ምክንያት አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከግእዝ ምንጮችን በመተርጎሙ ነው ብሎ መመለስ ይቻላል፡፡ በጥንቱ ላይ የሌሉት ሁሉ በዕብራይስጡ የሌሉ ሲሆን በሐዲሱ የተጐረዱት ደግሞ በዕብራይስጡ ያሉ ናቸው፡፡ በሌላ ቋንቋ የቀደመው መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን የተተረጐመው ከዕብራይስጡ ፴፱ ወይም ፳፬ ብለው አይሁድ ከሚቀበሉት/ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ለእኛ አንባቢ ከጥንቱ የነበረውን ከአሁኑ የሌለውን ለመረዳትም ሆነ በጥንቱ የሌለውን በአሁኑ ያለውን ለመገንዘብ የአዲሱን መጽሐፍ ቅዱስ ሕዳግ መመለከት ይጠቅማል፡፡ በብሉይ ኪዳኑ ሕዳግ ላይ «…የሚለው በዕብራይስጥ የለም» የሚል ካለ ይህ ቃል፣ ሐረግ ወይም ዓረፍተ ነገር በጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም ማለት ሲሆን «ዕብ. ….. የሚል ይጨምራል» ካለ ደግሞ ይህ ቃል በቀድሞው መጽሐፍ ቅዱስ የነበረ በአሁኑ ደግሞ የሌለ ነው ማለት ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ይህንኑ ጉዳይ ለግሪኩ ሰጥቶ መረዳት ይጠቅማል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ነገር አመልክቼ ልለፍ፡፡ በማቴ.፳፬÷፵፩/ ላይ «ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱን ይወስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ» የሚሉ በአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ የተጨመረ በቀድሞው ግን የሌለ ነው፡፡ ይህም ምክንያቱ ዓረፍተ ነገሩ በግሪኩ ባለመኖሩና በግእዙ በመኖሩ ነው፡፡

**የጮራ መጽሔት አዘጋጆችን ካስከፋቸው ነገሮች አንዱ በቀደመው መጽሐፍ ቅዱስ አካሔድ «ዲዮትሮ ፊካኖኒካል» የሚባሉትን ለብቻቸው ከማስቀመጡ ይልቅ ስምን አስባጠሯቸው የሚለው ነው፡፡ ዲዮትሮ ካኖኒካል ማለትም ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት ማለት ነው፡፡ ይህ ጽንሰ አሳብ ደግሞ ከአሥራው መጻሕፍት ጋር ይደመሩ ዘንድ በሌላ ቀኖና የተጨመሩ ማለት ነው፡፡ ተመልከቱ ቀኖናው የኋላ ነው ማለት መጻሕፍቱ የተጻፉት በኋላ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡**

## የለውጦቹ አንድምታ

ከላይ የጠቀስናቸውና ተመሳሳይ ሁኔታዎች የመጽሐፍ ቅዱሳችንን ምንነት በትክክል የሚያስረዱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ጨመረና ቀነሰ ሲባል ሆን ተብሎ የተደረገ አለመሆኑን ይረዱ ዘንድ በሕዳግ መቅረቡ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ ጥርጣሬ ያለው ግን በአዲሱ ተጨመረ ተቀነሰም የተባለውን በሕዳግ ስለሚያገኘው በርግጥ ይህ የራስን አሳብ ለመደገፍ የተደረገ ሊሆን ይችላልን?» ብሎ መመርመር ይችላል፡፡ «እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደ ምሰጣት ምድር» የሚለውን ጭማሪ ብንመለከተው ለኦርቶዶክስ ዶግማ የሚጨምረው ምንድን ነው? ባይኖርስ ምን ሊያጎድል ይችላል? ባይኖር የሚያጎድለው ነገር አንድ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ይህ በግእዙ ለምን እንደተገኘ ለሚያጠኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ተመራማሪዎች መንገድ ይዘጋል፡፡ ግእዝም ጥንታዊ ከሆኑት የትርጉም ቋንቋዎች አንዱ መሆኑንም ለማሳየት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

አንዳንድ ሰዎች የተጨመረና የተቀነሰ መኖሩን የስሕተት ማስረጃ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ፡፡ እውነት ለመናገር እንዲህ ያለ አሳብ አሳፋሪ ብቻ አይደለም፤ አሁን አሁን ነውርም ሊሆን ምንም አልቀረውና፡፡ ግሪኩ ብቻ ከተለያዩ ቅጂዎች አንጻር ቢጠና እንኳ ይኸን የመሰሉ ችግሮች መገኘታቸው አይቀሬ ነው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ብቻ እንዲተረጐሙ ያስገድድ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በአብዛኛው የፕሮቴስታንቱ ዓለም የሚቀበላቸው ፴፱ መጻሕፍት /በአይሁድ አከፋፈልና አቆጣጠር ፳፬ቱ/ በተለያየ ጊዜ ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጐሙ ከተመሳሳይ ምንጭ እንኳ ተቀድተው የተለያዩ ትርጉሞችን የሚሰጡበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ለአብነት አንድ ማቅረብ



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ሁለቱም አንድ ዓይነት ምንጭ /የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን/ ተጠቅመው ወደ እንግሊዝኛ የተተ ረጐሙት «The Jerusalem Bible» እና የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተመው «English Bible» ፪ኛ ሳሙ.፳፬÷፲፫/ ላይ ያለውን የረሀቡን ዓመት በተለያየ ቁጥር አስቀምጠውታል፡፡ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ያሳተ መው ሰባት ዓመት ሲል «የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ» የሚለው የእንግሊዝኛው ግን ሦስት ዓመት ይላል፡፡ ተመልከቱ፣ ይህ በፍጹም ሊሆን የማይገባው ስሕተት ነበር፡፡ በጣም የሚያስገርመው ደግሞ ይኸው በአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የታተመው መጽሐፍ ይህንኑ ጊዜ በ፩ኛ ዜና፳፩÷፲፪/ ላይ ሲተረጉም የረሀብ እንደ ገና ሦስት ዓመት ይለዋል፡፡ በዚህም ስሕተት ያለበት ራሱ እንደሆነ አጋልጧል ማለት ነው፡፡

ይህን ጉዳይ ማንሳት ያስፈለገው አዲሱ ትርጉም ስሕተቶቹ ጥቂቶች ናቸው ብሎ ለመናገር ጊዜው ገና፣ ጥናትንም የሚሻ ጉዳይ ቢሆንም ከላይ የተገለጹት ነገሮች በጥንቱ ግእዛችን ላይ ከመኖርና ካለመኖር ጋር የተገናኙ፤ በርግጥም የራሳችን የሆነ ትርጉም የነበረን መሆኑን ማሳያዎች መሆናቸውን መዘንጋት አይገባም፣ ለማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዱን ሕጻግ ስንመለከተው /በብሉይ ኪዳኑ ትርጉም/ ላይ «በግሪኩ የለም» የሚሉ ሕዳጐችን እናገኛለን፡፡ ይህ ማለት ለግሪኩ እናት በሚባለው በዕብራይስጡ ኖሮ፣ በግእዙም ኖሮ በግሪኩ የለም ማለት ሲሆን ለትርጉማችንም እናት ቋንቋ ሌላ ጥቆማ ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም ዕብራይስጡና ግእዙ ተስማምተው ግሪኩ ከተለየ ከግሪኩ ውጭ ትውውቅ እንዳላቸው አመልካች ነው፡፡ ግእዙ ግሪኩ የጎረደውን በራሱ ሞላው እንዳይባል እንኳ ቢሞላ ሌላ የራሱን ትርጉም ወለድ የሆነ ቃልን መተካት ነበረበት እንጂ ግሪኩ የተወውን ዕብራይስጥ በአጋጣሚ ሊተካው አይችልምና፡፡ አንባቢ ማስተዋል ያለበት ግን ከዚህ በመነሣት ብቻ ግእዙ የተተረጐመው ከግሪክ ሳይሆን ከዕብራይስጡ ነው እያልኩ እንዳልሆነ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን ለተመራማሪዎች ትልቅ ፍንጭ ብቻ ሳይሆን ዕገዛም የሚሰጥ ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡

*ሐ/ የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ*

ቁልፍ ቃላት የሚባሉት ስለ ክርስቶስ፣ ስለ እግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ሥጋዌ፣ አሁን ደግሞ ስለምልጃና ስለመሳሰሉት ወሳኝ ጉዳዮች የሚገልጹትን የቃላት አተረጓጐም የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህን ጽንሰ አሳቦችን በሚመለከት መጠንቀቅም ሆነ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ትርጓሜ ማድረግ በተለይ በምዕ ራባውያን ተርጓሚዎች ዘንድ የተለመደ ክስተት ነው፡፡

አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ በእኛ ሊቃውንት በአግባቡ ሊመረመር የሚገባውም ከዚሁ ሁኔታ አንጻር መሆን አለበት፡፡ ለመፍረድ ሳይቸኩሉ ለመውቀስም ሆነ ለማወደስ ሳይጣደፉ መጻሕፍትን እያመሳከሩ በማገላበጥ የቋንቋችንን ዘር፣ አግባብና አውዳዊ ፍች ያገናዘበና መልእክቱን ሳያዛባ መተርጐሙን መመርመር ተቀዳሚ መሆን አለበት፡፡ በእኛ ሀገር ሁኔታ ይህን ጥያቄ የሚያስነሡ ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን መሠረት ለመጣል የተጋው የኢየሱሳው ያን ልዑክ /Jesuit Missionaries of Catholic/ ከፈጸሙት ተግባር አንዱ አሥራው መጻሕፍት ላይ አሳባቸውን የሚደግፉ ቃላትን ለእነዚህ ቁልፍ ቃላት ተጠቅመዋል /ሞክረዋል/ የሚለው አመለካከት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከእነርሱም በኋላ የተነሡት የእነርሱ ተቀጽላዎች የነበሩት ቅባትና ጸጋ በተለይ በዘመነ መሳፍንት አሁንም በመጻሕፍቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል የሚለው ሲሆን፤ ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የመጣው የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ አሁንም ከራሱ አስተምህሮ ጋር ይቃረናል በሚላቸው ቁልፍ ቃላት ላይ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል የሚለው አሳብ ነው፡፡ የእኛም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመሳሳይ ክርክር ሲነሣባቸው የኖሩ ጥቅሶች አዲሱን «ምን ይል ይሆን?» ተብሎ እንዲጠበቅ አድርገውታል፡፡

እነዚህን ችግሮች ያነሣሁት ትርጉሙን ከዚሁ አንጻር በሰፊው ለመዳሰስ ሳይሆን ሁለት ጉዳዮችን በመጠኑ ለመጠቆም ነው፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ ሊቃውንት ጉባኤ ለአሁኑ ሥራው የተጠቀመው ትርጉም የመቼ ዘመን የግእዝ ትርጉም ነው? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

በርግጥ ቅድመ ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን የተተረጐመ ጥንታዊ ምንጭ ተጠቅሟልን? በመቼ ዘመን የተገለበጠ ነው? ከላይ የተጠቀሱትን ሥጋቶች ግምት ውስጥ አስገብቷል ወይስ የለም? ለምን? ስለዚህ ከእነዚያ አካላት «ጥላ» ማምለጡን በምን እና ረጋግጣለን የሚል ጥያቄዎችን ያስነሣል፡፡ ሁለተኛው ግን እጅግ መጠነኛ ጥቅሶችን በመምረጥ ሁኔታው ሰፊ ጥናት የሚያስፈልገው ባሕር ጉዳይ መሆኑን ጠቁሞ ለማለፍ ነው፡፡

## ጥቂት ቁልፍ ቃላት

ለዚህ ሥራ ብዬ ያነጋገርኳቸው ጥቂት የቅኔና የመጻሕፍት ሊቃውንት ነበሩ፡፡ እነዚህ አባቶች ቀድመው ጥያቄ ያነሡት ቅባትንና ጸጋን የተመለከቱ ቁልፍ ቃላት ላይ ነበረ፡፡

*ሀ. ቅባትን በተመለከተ*

*መዝ.፵፬÷፯ን በቀኝ በኩል ካለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡*

| | |
|---|---|
| በእንተ ዝ<br>ቀብዐከ እግዚ<br>አብሔር<br>አምላክከ፤<br>ቅብዐ<br>ትፍስሕት<br>እምእለ ከማከ | ግእዝ |
| ስለዚህ<br>ከባልንጀሮችህ<br>ይልቅ<br>እግዚአብሔር<br>አምላክህ<br>የደስታ<br>ዘይትን ቀባህ | የቀድሞው<br>መጽሐፍ<br>ቅዱስ |
| ስለዚህ<br>ከባልንጀሮችህ<br>ይልቅ<br>እግዚአብሔር<br>አምላክህ<br>የደስታ<br>ዘይትን ቀባህ | አዲሱ<br>መጽሐፍ<br>ቅዱስ |



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መምህራኑ የአሁኑና የቀድሞው መጽሐፍ ቅዱስ ተስማምተው በዚሁ መንገድ በማቅረባቸው ደስተኞች አይደሉም፡፡ በትርጓሜ ዳዊት ላይ ንባቡን በአማርኛ ዘርሲያስቀምጡ «አዋሐደህ» ስለሚለውና ለዚህም ደግሞ ዮሐንስ አፈወርቅ «ዘይኄይስ» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ዳዊት ጠቀስ ምንባብ በመልእክቱ /የሚበልጥ፣ የሚሻል የሚሉት ቃላት ለጌታ የባሕርይ መሆኑን አመልካች በመሆናቸው «በዘይተ ፍስሐ» ብሎ እንደወሰደው ሁሉ ይህም «እም እለ ከማከ» «ከባልንጀሮችህ» የሚለው በጸጋ ከተቀቡት ከእነ አሮን፣ ከነሙሴ፣ ከነዳዊት ከነሰሎሞን የሚለይ የባሕርይ በመሆኑ «አዋሐደህ» መባል ነበረበት ይላሉ፡፡ ይሔ «ዘይሔይስ» የሚለው ቃል የሚገኘው ይኸንን ጥቅስ በተጠቀመው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ሰዎች በላከው መልእክት ላይ ነው፡፡ ግእዙ «ወበእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ፤ ቅብዐ ትፍስሕት ዘይኄይስ እምእለ ከማከ» በማለት ከላይ ባየነው የዳዊት ጥቅስ ላይ «ዘይኄይስ» የምትለውን ጨምሮ እንመለከተዋለን፡፡ ይህንን የዕብራውያን መልእክት የተረጎመው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ይህችን የቅዱስ ጳውሎስን «ዘይኄይስ» የምትለውን ቃል በማጉላት «ዘአልቦ መስፈርት» በማለትም የእርሱን የባሕርይ አምላክነት አሳይቶበታል፡፡ /ዕብ.፩፥፱ ትርጓሜ/ ይህን የመሰሉትን ሁኔታዎች በጥንቃቄ መተርጐም ግን የተገባ ነው፡፡


ለ. ፍሕረትን በተመለከተ

እመቤታችን ለዮሴፍ ታጨች የተባለበትን ትርጓሜም /ማቴ.፩፥፲፰/ «ፈሐረ - አጨ» በሚለው ከመተርጐም «ፈሐረ - ጠበቀ» በሚለው መተርጐም ነበረባቸው የሚሉ ሊቃውንት አጋጥመውኛል፡፡ እንደ ሊቃውንቱ ገለጻ ከሆነ ዮሴፍ በዚያ ዘመን አረጋዊ ነበር፤ እመቤታችን ደግሞ ገና የ፲፭ ዓመት ልጅ፡፡ በዚህ መሠረት ሊሆን የማይችልና ያልተደረገን ነገር ታጨች ማለት ስሕተት ነው ይላሉ፡፡ እንደ ሊቃውንቱ ለእመቤታችን «ታጨች» ተብሎ መጻፉ ጉዳት ሊያስከትል ባይችልም ከዐውድም ሆነ ከግሱ አንጻር የፈሐረ ትርጉም መስተካከል ነበረበት ይላሉ፡፡

ከላይ የመሰሉትን ያነሣሁት የቁልፍ ቃላትን አተረጓጐም በተመለከተ እንደ ባለሙያ ትኩረትን የሚሻ ከመሆኑም በላይ አብነት ለማሳየት ያህል እንጂ ያለ በቂ ጥናት የሚነካ እንዳልሆነ በእጅጉ እገነዘባለሁ፡፡

ሌሎች፦ ሀ. ሮሜ ፰፥፳፮ እና ፴፬ ላይ «ይማልዳል» የሚሉት ከግእዙ የተነሣ ይፈርዳል በሚሉት ተተክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ግሪኩ ከዚህ የተለየ እና ይማልዳል እንደሚል ደግሞ በሕዳጉ ተገልጿል፡፡

ለአብነት ከላይ ያሉትን ከተመለከትን ሌሎችን በሰፊ ጥናት ማሳየት የሚገባ ይሆናል፡፡ እነዚህን ሁሉ የዳሰስነው «ቤተ ክርስቲያኒቷ በማዘጋጀቷ መጽሐፉ በራሷ ሐሳብ ተሠርቷልን?» የሚለውን በቀና



መንፈስ ለመመልከትም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ጠጣር አሳቦች ከብዙ አንጻር በጥልቅ ጥናት ሊታዩ የሚገባቸው ከመሆናቸውም በላይ በሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ከተደጋጋሚ የትርጉም ሥራ በኋላ እየጠሩና እየታወቁ እንደ ሚሔዱ መገንዘብ ይቻላል፡፡

መቀነስና መጨመርን በዚህ መጠን እንኳ ለማቅረብ ግድ ያለኝ ባለፈው ዕትማችን የተመለከትነው የኅትመቱ አስፈላጊነት ጉዳይ ነው፡፡ በመግቢያው ላይ «የአተረጓጐሙ ስልት ከቤተ ክርስቲያናችን የአተረጓጐም ስልት የራቀ ስለሆነ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ብለው በሙሉ ለመቀበል ሲቸገሩ ኑረዋል» ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚያኛው በተሻለ ሁኔታ እንዲቀበሉት የሚያደርግ አዲስ ትርጉም ብዙም አላየንም፡፡ የቁልፍ ቃላት ትርጉምን መመልከት ያስፈለገው ለዚህ ነበር፡፡ እስካሁን የታየ አዲስ መሠረታዊ የትርጉም ለውጥ /አዲስና ትክክለኛ/ አላየሁም፡፡ ተርጓሚው አካል «አለ የሚለው ካለ ደግሞ» እዚሁ መግቢያው ላይ ማሳያ ማቅረብ ወይም ሕዳጉ ላይ «ቀድሞ ... የተባለው አሁን እንዲህ ብሎ» አሁንም ማሳየት ይጠበቅበት ነበር፡፡ ስለዚህ መግቢያው ላይ የተቀመጠው ምክንያት በሥራ ያልታየ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

## የመጻሕፍቱ ቁጥርና ቅደም ተከተል

አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ በቁጥር ፹፩ መጻሕፍትን ይዞ ታትሟል፡፡ ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን ለ፴፭ቱ ሐዲሳት ተጨማሪ ተደርገው የሚቆጠሩት ፰ቱ የቀኖና መጻሕፍት አልተካተቱም፡፡ ከዚህም በላይ መጻሕፍቱ ሲቆጠሩ ያለው ትውፊት ከዚህኛው ጋር አይገጥምም፡፡ የመጻሕፍቱ ቅደም ተከተላዊ አቀማመጥም እንዲሁ ያልተለመደ ነው፡፡ ለምን ይሆን? አንድ በአንድ እንመልከታቸው፡፡

*ሀ. ፹፩ዱ /ሰማንያ አሐዱ/*

ይህን አሐዝ የቅዱሳት መጻሕፍቶቻችን ቁጥር በተነሣ ጊዜ ሁሉ በተደጋጋሚ እንሰማዋለን፡፡ ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት አንጻር ቁጥሩ ከመቼ ጀምሮ እንደነበረ በትክክል ማረጋገጥ ባይቻልም እጅግ ቀደም ብሎ እንደነበረ ለመረዳት ግን አያዳግትም፡፡ ይህን የምልበት ምክንያትም ከእኛ የቀደሙ ሊቃውንት መካከል ቁጥሩ ላይ ጥያቄ አንሥተው የተከራከሩ እስካሁን አላጋጠመኝም፡፡ እንዲያውም አብዛኛዎቹ የሚደክሙት መጻሕፍቱን በቁጥር ፹፩ ለማምጣት ነው፡፡ ድካሙን ምን አመጣው? የሚል ይኖራል፡፡ አዎን፤ ይገባልም፡፡ በእኔ እምነት የመጻሕፍቱ ቁጥርና መጻሕፍቱ የመጡበት ሁኔታ እና ጊዜ መለያየት አንዱና ዋናው ምክንያት ይመስለኛል፡፡ የሌሎቹን ሀገሮች ስንመለከተው ምንም እንኳ መጠነኛ ልዩነት ቢኖርም በአብዛኛው ግን መጻሕፍቱ አንድ ላይ ደርሰዋቸዋል፡፡ በእኛ ግን እንደዚህ አይደለም፡፡ መጻሕፍቱ የደረሱን በተለያየ ዘመን ለየብቻ ነውና፡፡ ለዚህም ይመስላል አንዱ ሊቅ ሰማንያ አንዱን ሲቆጥር ሲተርፍበት «እገሌን ቢያስገቡ እገሌንና እገሌን አንድ ብለው ይቆጥራሉ» ወይም ደግሞ «እገሌን እንዲህ ስለሚለው ከዚያው ገብቶ ይቆጠራል፤ ስለዚህ እገሌ ይገባል» እያሉ መጻሕፍቱን ሁሉ ደምሮ ፹፩ ለማምጣት ሲደክሙ የኖሩት፡፡ በዚህ ምክንያት ቁጥሩ ያው ሆኖ አቆጣጠሩ ግን ተለያይቶ ይኖሯል፡፡ እስካሁን ድረስም ወጥ የሆነ ነገር የለም፡፡ ይህ በራሱ ችግር አይደለም፡፡ በተለይ የእኛ ቤተ ክርስቲያን የራሷ ሲኖዶስ ከኖራት ገና ፶ ዓመት እንኳን ስላልሞላት የምትቀበላቸውን ቀኖናዎችና በእነርሱ የተገለጹትን ጉዳዮች /ለምሳሌ የመጻሕፍትን ዝርዝር/ በይፋዊ ቅበላ /Official ratification/ ማጽደቅ ይገባታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሥራዎቿ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ናቸው እየተባለች የምትነቀፍና ልጆቿንም መልስ የምታሳጣ እንዳይሆን ያሰጋል፡፡ የመጻሕፍትን ቁጥር በተመለከተ ምንም እንኳን በሲኖዶስ ደረጃ በይፋ አንድም ጊዜ ባታሳውቅም እንኳ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመን ብቻ እንኳ ሁለት ዓይነት አቋም እንደያዘች ሊያስቆጥርባት ይችላል፡፡ ምክንያቱም በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ባሳተመችው «ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት» በሚለው መጽሐፍ የዘረዘረቻቸው ፹፩ መጻሕፍትና አሁን በ፳፻ ዓ.ም ባሳተመችው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተካተቱት መጻሕፍት ዝርዝር ልዩነት አለውና፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

**አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ በእኛ ሊቃውንት በአግባቡ ሊመረመር የሚገባውም ከዚሁ ሁኔታ አንጻር መሆን አለበት:: ለመፍረድ ሳይቸኩሉ ለመውቀስም ሆነ ለማወደስ ሳይጣደፉ መጻሕፍትን እያመሳከሩ በማገባበጥ የቋንቋችንን ዘር፣ አግባብና አውዳዊ ፍች ያገናዘበና መልእክቱን ሳያዛባ መተርጐሙን መመርመር ተቀዳሚ መሆን አለበት::**

## ፰ቱ የቀኖና መጻሕፍት

ብዙ ጊዜ አከራካሪ ከሆኑትና አሁንም በሁለቱ ዝርዝሮቿ ላይ የጎላ ልዩነት የሚያሳዩት የ፰ቱ መጻሕፍተ ቀኖናት ጉዳይ ነው:: እነዚህ መጻሕፍት በ«ውጭ ግንኙነት መጽሐፍ» ላይ ሲዘረዘሩ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን የሉም:: ያ ሊባል ይችላል? እነርሱም ፹፩ መጻሕፍት ተካትተዋል:: ለምን? እንዴት? የሚል ጥያቄ መነሣቱም አይቀሬ ነው::

«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት÷ ሥርዓት አምልኮትና የውጭ ግንኙነት» መጽሐፍ ላይ የተካተቱት ፰ቱ ማለትም «ሥርዓተ ጽዮን፣ ትእዛዝ፣ ግጽው፣ አብጥሊስ፣ ፩ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ ፪ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ ቀሌምንጦስ እና ዲድስቅልያ» ሐዋርያት እንዳዘጋጇቸው ቢታመንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ታትመው ወጥተው አያውቁም:: ለዚህም ቢያንስ ሁለት ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል::

ሀ. መጻሕፍቱ ከአሥራው መቆጠር የለባቸውም:- እነዚህን መጻሕፍት አስፈላጊነታቸውን ከመግለጽ አልፈው ቤተ ክርስቲያን ያለእነዚህ አትመራም የሚሉ አካላት ሳይቀር እንደ አሥራው መጻሕፍት አይቀበሏቸውም:: አንዳንዶቹ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው አልቀዋል ብለው የሚያምኑበትን ጊዜ መሠረት አድርገው ከዚያ ወዲህ የተዘጋጁ ሁሉ ለትምህርት፣ ለተግሣጽና ለሥርዓት አስፈላጊ በመሆናቸው ያለመሸራረፍ አገልግሎት ሊሰጡ ቢችሉም በጊዜያቸው ምክንያት መካተት የለባቸውም ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ከጊዜው ይልቅ ይዞታቸው ላይ በማተኮር በአገልጋዮች እጅ ብቻ ካልሆነ በምእመን እጅ እንዲገቡ ስለማያስፈልግ እና ትምህርተ ሃይማኖትንም በማስተማር ረገድ የእነዚህ ድርሻቸው ዝቅተኛ ነው በማለት ከአሥራው እንዳይቆጠሩ ይስማማሉ:: በርግጥ ሁለቱም ወገኖች ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ መጻሕፍት መገልገል አለባት የሚለውን ያለልዩነት ይስማሙበታል:: ጥያቄው ከአሥራው ይቆጠሩ ወይስ አይቆጠሩ? የሚለው ብቻ ነው::

ከአሥራው መጻሕፍት ሳይቆጠሩ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡትን አገልግሎት ሳያጓድሉ መስጠት ይችላሉ ከሚሉት ውስጥ የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን መጥቀስ ይቻላል:: ግብጾች ፰ቱም የቀኖናት መጻሕፍት ያሏቸውና ለአገልግሎትም የሚጠቀሙባቸው ቢሆንም ከአሥራው መጻሕፍት ጋር ግን አይቆጥሯቸውም::


የእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ደግሞ የእነዚህን መጻሕፍት ከአሥራው መደመር ይስማሙበታል:: አሁን አሁን ወደ ውጭ ሀገር ሔደው የምዕራባውያኑንም ሆነ የምሥራቆቹን ትምህርት ተምረው ከተመለሱት አንዳንዶቹ ምንም እንኳ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚዎች ቢሆኑም ከ፪ ዓ.ም በኋላ የተጻፈ መጽሐፍን ከአሥራው ጋር መቀበል አይገባም ብለው ይከራከራሉ:: እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች እያሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለምን ፹፩ ትላለች የሚለው ጥያቄም የሚነሣው በዚሁ ምክንያት ነው:: የሐዋርያት ቀኖና /Apostolical canons/ ባለ ፹፭ አንቀጹ መጽሐፍ ውስጥ በ ፹፭ኛው ቀኖና የቅዱሳት መጻሕፍትን ዝርዝር ሲገልጽ እነዚህን መጻሕፍት ሳይዘረዝር ይቆጥራቸዋል:: ይህ አቆጣጠር ሁለት የቀሌምንጦስ መልእክታትን ከአስቀደመ በኋላ ስምንቱን ለብቻቸው ይጠራቸዋል:: «The regulations addressed to you bishops through me, Clement, eight books» ትርጉም:- በእኔ በቀሌምንጦስ በኩል ለእናንተ ሊቀጳጳሳት የደረሱት ሕጎች - ፰ቱ መጻሕፍት» ይላቸዋል:: /Apostolic cannons, Article, Lxxxv/ ይኸው ፹፭ኛው ቀኖና በተጠቀሰው አንቀጽ ላይ ስለ እነዚሁ መጻሕፍት ሲናገር «Which it is not right to publish before all, on account of the mysteries in them:- እነዚህም ስለያዙአቸው ምስጢራት በሁሉም ዘንድ ክሡት ሊሆኑ /ሊታተሙ/ የማይገባቸው ናቸው» ይላል:: /Ibid, Encyclopedic dictionary of Christian antiquities, p.113/

እነዚህ መጻሕፍት የሐዋርያት ድንጋጌዎች /Apostolical constitutions/ በመባል ይጠራሉ:: ይዘታቸውም በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ማብራሪያ፣ የግለሰብ /የክርስቲያኖቹን/ ሕይወትንም ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንጻር ያወሳሉ፤ የቅዳሴንና የማኅበር ጸሎትንም በተመለከተ ይናገራሉ:: እንግዲህ ከአሥራው መጻሕፍት ሳይሆን ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መቆጠር አለባቸው፤ ወይም ደግሞ መታተምና ለሕዝብ መድረስ የለባቸውም የሚለው ሐሳብ መነሻዎችም ከዚህ ይዞታቸው በማነሣት እንደሚሆን መገመት ይቻላል:: አዲሱ መጽሐፍ ቅዱሳችን እነዚህን ያላካተተበትን ምክንያት ግን በግልጽ አላቀረበም:: አዘጋጆቹም በየትኛው መድረክ ስለዚህ ሁኔታ ሲገልጹ አልሰማሁም::



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org



## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አቀማመጥ

የሮሜ መጽሔት አዘጋጆችን ካስከፋቸው ነገሮች አንዱ በቀደመው መጽሐፍ ቅዱስ አካሔድ «ዲዮትሮ ካኖኒካል» የሚባሉትን ለብቻቸው ከማስቀመጡ ይልቅ ለምን አሰባጠሩአቸው የሚለው ነው:: ዲዮትሮ ካኖኒካል ማለትም ተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት ማለት ነው:: ይህ ጽንሰ አሳብ ደግሞ ከአሥራው መጻሕፍት ጋር ይደመሩ ዘንድ በሌላ ቀኖና የተጨመሩ ማለት ነው:: ተመልከቱ ቀኖናው የኋላ ነው ማለት መጻሕፍቱ የተጻፉት በኋላ ነው ማለት ግን አይደለም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን መጻሕፍት /በቀኖና የተጨመሩ የተባሉት/ የተቀበለቻቸው ከዚሁ ፈረንጆቹ ከተቀበሉበት ቀኖና በኋላ ሳይሆን በፊት ነው:: በተለይ መጽሐፈ ሔኖክ እንኳን ቤተ ክርስቲያናችን ሀገራችንም እርሱን ጠብቃ በማቆየት የምትታወቅበት መጽሐፍ ነው:: እኛም መጻሕፍቱን ያገኘናቸውና የተቀበልናቸው አሁን ከ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ በተፈጠረው የኅትመት ጥራዝ መልክ ሳይሆን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ በየዘመኑ በተናጠል ነው:: ስለዚህ መጻሕፍቶቹን እንደየዘመናቸው ወይም እንደ የሚመደቡበት ሁናቴ አሰባጥሮ ማስቀመጡ የአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ ጐን ከመሆኑም በላይ ቀደም ብለን እንደገለጽነው ትውፊታዊ /Traditional/ ከሚያሰኙትም ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው::

ይሁን እንጂ አዘጋጆቹም ይሁኑ ቤተ ክርስቲያኒቷ አንደኛ ስለቁጥራቸው ሁለተኛ ስለአቆጣጠሯ፣ ሦስተኛ ስለቅደም ተከተላቸው ሳትገልጽ ማስቀመጧ አግባብነት ያለው አይመስልም:: ይልቁንም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት» ወይም ደግሞ ብዙዎቹ ሊቃውንቶቻችን ከሚጠቀሙበት ከፍትሐ ነገሥታችን አንጻር ያለውን ሁኔታ ያገናዘበ መግለጫ መስጠት ይገባት ነበር:: አሁንም ቢሆን ጊዜው አልመሸምና ሲኖዶሱም ካለበለዚያም ሊቃውንት ጉባኤ አንዳች ነገር ማለት ይገባቸዋል::

ከስብጥሩ ባሻገር ደግሞ ራሱን ችሎ በአቆጣጠር ሲታይም ጥያቄዎችን ያስነሣል:: በቀደመው መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ የቀኖና መጻሕፍት ከተጠቀሱት መካከል መጽሐፈ ሶስና እና ተረፈ ዳንኤል ይባል የነበረው ደግሞ «ዳንኤልና የቤል ካህናት» ተብሎ የትንቢተ ዳንኤል አሥራ ሦስተኛና አሥራ አራተኛ ምዕራፎች ሆነው ሲጠቃለሉ መዝሙር ዘሠለስቱ ደቂቅ ደግሞ በዚሁ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ ሦስት ላይ ከቁጥር ፳፫ በኋላ ገብቶ ነገር ግን በአዲስ ቁጥር /ከአንድ ጀምሮ/ ተገልጿል:: በዚህ ምክንያት በቀደመው መጽሐፍ ሦስት ተብለው የተቆጠሩት አሁን ከትንቢተ ዳንኤል ጋር ተካትተዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ተረፈ ባሮክን እንደ አንድ መጽሐፍ አምጥቶ አስገብቶታል:: ይህም በራሱ ከአቆጣጠራችን አንጻር ማብራሪያ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነበር፤ ይሁን እንጂ ምንም አልተባለበትም::

### የገጽ መልክና ቅንብር

ይዘቱን በተመለከተ ይህን ያህል ካልን እንደመጨረሻ የሚነሣው የመጽሐፉ ይገጽ መልክና ቅንብር ጉዳይ ነው:: በአጭሩ ለማጠቃለል ሲባል ከገጽ መልክና ቅንብሩ ጥቂቶችን ነጥቦችን ብቻ እንመለከታለን::

*ሀ/ ጠንካራ ጐኖች፡-* መጽሐፉ ንዑስ ርእሶችን እየሰጠ መገናዘቢያ ጥቅሶችንም መካከል ላይ እያስገባ ማቅረቡ ታሪኩን በውል ለመረዳትና ለማነጻጸር ከመጥቀሙም በላይ ለአንባቢ ቅርብ ቅርብ ማረፊያዎችን /eye breaks/ መፍጠሩም ከጠንካራ ጐኖች ይጠቀሱለታል:: ከዚህም በላይ መጽሐፉ ውበት አለው:: መካከል ላይ ያለው መስመር ግን ጉዳትም ጥቅምም ውበትም የሌለው ነገር ነው:: በርግጥ በአምዶቹ መካከል ያለው ቦታ በመጥበቡ ምክንያት ሁለቱን አምዶች ለመለየት ታስቦ ይሆናል:: ነገር ግን መስመሮቹ ስለማይገናኙ /ስለሚዛነፉ/ የመስመሩ ጥቅም አይታይም::

*ለ. ደካማ ጎን፡-* የዚህ መጽሐፍ ዋናውና መሠረታዊው ደካማ ጐን የቁጥሮች አቀማመጥና መጠን ነው:: ቁጥሮቹ በመጠናቸው እንደ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥሮች /footers/ ከመሆኑም በላይ በየመካከሉ ዝርዋን በመሆናቸው ፈልጐ ማግኘቱን በእጅጉ አስቸጋሪ አድርጎታል:: ዓይናቸው ለደከመ ቀርቶ ለወጣቶቹም ቢሆን ፈታኝ ነው።

ከዚህ በተረፈ ትውፊታዊ መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን የግርጌ ማስታወሻ ይጠበቅበታል:: በመሆኑም ከግሪኩና ከዕብራይስጡ እያነጻጸረ «የለምና አለ» ወይም «እንዲህ ይላል» በማለት የገለጻቸው ለተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለአንባብያንም የግእዝ ትርጉማችን ከተጠቀሱት ግሪክና ዕብራይስጥ ቅጂዎች ያለውን ልዩነትና አንድነት ወይም መቀራረብ ብቻ ሳይሆን የታመነ ምንጭ መሆኑንም አስመስክሮለታል:: ከእነዚያ እጅግ ኢምንት ልዩነቶች በስተቀር አንድነቱንና ታማኝነቱን አረጋግጧልና:: በዚህም በህብታችን ብቻ ሳይሆን የህብቱና የታሪክ ባለቤት ባደረጉን አባቶቻችን መንፈሳዊ ኩራት /አድናቆት/ እንዲሰማን «ተዘከሩ መኳንንቲከሙ፡- ዋኖቻችሁን አስቡ» በተባለው መሠረትም ዝክራቸውን እንድናስብ የሚያደርግ ነው:: በርግጥም አባቶቻችን በዚያ በቀደመው ዘመን ምን ያህል የሁለገብ ዕውቀት ባለቤቶችና ለፈጣሪያቸው አደራ የታመኑ መሆናቸውን አሳይቶናል::

*ማጠቃለያ፡-* አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ሞያዊ በሆነ መንገድ ገና ሊጠና፣ ሊተነትን የሚገባው ቢሆንም ሥራው የሚያስመሰግን ነው:: ነገር ግን ሌሎች መጻሕፍትን በማጥናት በማዘጋጀትና ለኅትመትና ለንባብ በማቅረብ እየተደገፈና እየታጀበ መሔድ ይገባዋል:: የተገኙበትን መጠነኛ ችግሮች አስተካክሎና አርሞ የሚጠበቅበትንም ማብራሪያና ጉዳያዊ ዕውቀት አስጨብጦ ተደጋግሞ መታተምም የሚገባው ነው:: ከዚህም አልፎ ከላይ በጠቀስናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቶች ውስጥ ለእኛ በሚሆነው መንገድ ሊከተሉት ይገባል:: ይህም ሆኖ መጽሐፉ በተዘዋዋሪም ቢሆን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ታሪካችን፣ የግእዝ ምንጫችንን ታማኝነት፣ የትርጉም ባህላችንን፣ እንዲሁም የመጻሕፍት ትውፊታችን በማስረዳት ሰፊ ጠቀሜታን ያጐናጽፋል:: ይህ እንግዲህ እንደ ማንኛውም ቅዱስ መጽሐፍ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የሚሰጠው ጥቅም ነው:: የትርጉም ሒደታችን ከራሳችን ወደ ራሳችን በማሻገርና ለሌሎች ቋንቋዎችም እናት ወይም ማነ ጻጸሪያ በመሆን የሚሰጠው ጠቀሜታም ከፍተኛ ነው:: የቅዱስ መጽሐፍን ጠቀሜታ የምናጠቃልለው በቀዳሽነቱ መሆን ይገባዋል:: ስለዚህም እግዚአብሔር የተቀበልነውን ሁሉ ይቀድስልንና ያከብረን ዘንድ ፈቃዱ ይሁን፣ አሜን::ቀ

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*




©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ተአምረ ማርያም በግብጽ

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን




በግብጽ ካይሮ የሚገኘው የቅድስት ዴሚያና ቤተ ክርስቲያን

የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን ያመኑ ውሉደ አትናቴዎስ፣ የድንግል ማርያምን እመ አምላክነት የሚመሰክሩ ውሉደ ቄርሎስ ያሉባት የግብጽ ምድር የእመቤታችን ተአምራት ተዘውትሮ የሚታይበትና ክብሯም እጅግ የገነነበት ነው፡፡

በሀገራችን የእመቤታችን ተአምር ዛሬም በአስደናቂ ሁኔታ በመፈጸም ላይ ያለ ይሁን እንጂ ይህንን የማይቀበሉ በውስጥና በውጪ በበዙበት በዚህ ዘመን ግብጻውያን ግን የድንግል ማርያምን ተአምር መዝግበው ለትውልድ ማስተላለፋቸውን፣ መመስከሩን ቀጥለዋል፡፡ ከግብጻውያን ለእመቤታችን ተአምራት ክብርን መስጠትን ብቻ ሳይሆን የተአምራት አቀባበልና ምዝገባ ሂደታቸው ለእኛ ታላቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡ የዛሬ ፳፪ ዓመት ገደማ በግብጽ ምድር እመቤታችን ስለሠራችው ተአምርና ከዚያ ጋር ተያይዞ ስለነበሩት ሁኔታዎች እስቲ እናስተዋውቃችሁ፡፡

ቀኑ እ.ኤ.አ መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም ነው፡፡ በግብጽ ካይሮ በቅድስት ደሚያና ቤተክርስቲያን ግብጻውያን አንድ ታላቅ ተአምር ተገለጠላቸው፡፡ በዚህች ቤተክርስቲያን ሁለት ማማዎች መካከል ቅድስት ድንግል ማርያም በዚያ ለሚኖሩ ሁሉ ታየች፡፡ ታላቁን አንጸባራቂ ብርሃን ከድንግል ሙሉ አካል ጋር አዩት፡፡ በተለይም በጉልላቱ በስተምዕራብ ያለው በብርሃን ጐርፍ የተፈጠረው አክሊል እጅግ አስደናቂ ነበር፡፡ አስተርእዮው /መገለጡ/ በተከታታይ ስለነበር ዜናው በተለያየ የእምነት ሐሳብ ውስጥ ለነበሩ ወገኖች ሁሉ ደረሰ፡፡ በደረሰው ዜና ምክንያት ቤተ ክርስቲያኑን የከበበው ጠባቡ መንገድ በሰዎች ተጨናነቀ፡፡ ብዙዎች በደስታ ዘመሩ፤ ጸለዩ፡፡ ለእውነተኛው ብርሃን እናት ሌሊቱን ሁሉ ሰገዱ፡፡

በዚያም ብዙዎች ለረጅም ዘመን ከአብረባቸው ማየት ካለመቻል፣ ከኩላሊት፣ ከጸና የልብ ሕመም፣ ከሌሎች በብልቶቻቸው ከነበሩ ደዌያት ሁሉ ተፈወሱ፡፡ ሁሉም ከዚያ ቀደም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው መፍትሔ ያጡ ነበሩ፡፡

## የግብጽ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተአምሩን ያረጋገጠበት አሠራር

እ.ኤ.አ ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፱፻፹፮ ዕለት ስለተገለጠው ተአምር አባ /Father Heg/ አብደል መሲህ ኤል ሼርቤኒ እና አባ ሳሙኤል ዮሃን /የቅድስት ዴሚያና ቤተክርስቲያን ካህናት/ ለፖፕ ሺኖዳ ዘገባ አቀረቡ፡፡

ቅዱስነታቸውም የታንታ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የሆኑትን አንባ ጳውሊንና የአል ሙሃረክ ገዳም ጳጳስ የሆኑትን አንባ ሳዊሮስን ወደ ቤተክርስቲያኑ በመላክ ነገሩ እንዲጣራ አዘዙ፡፡ እነዚህም አባቶች ወደዚያው በመጓዝ ተአምሩን አረጋግጠው ለቅዱስነታቸው ዘገባ አቀረቡ፡፡

ነገሩ ግን በዚህ አላበቃም፡፡ ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ክስተት በግብጽ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ዘንድ በተሰማ ጊዜ ነገሩን የሚመረምር /የሚያረጋግጥ/ ልዑክ ወደ ቦታው እንዲሔድ ሚያዚያ ፱ ቀን ፲፱፻፹፮ ተወሰነ፡፡

*ለዚህ ልዑክ የኮሚቴ አበላት ሆነው የተመረጡትም*

፩ኛ. አባ ቢሾይ የዳሚታ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ
፪ኛ. አባ ሙሳ የወጣቶች ጉዳይ ጳጳስ
፫ኛ. አባ ጳውሊ የታንታ ሀገረ ስብከት ጳጳስ
፬ኛ. አባ ሲራፒዮን የማኅበራዊ አገልግሎት ጉዳዮች ጳጳስ
፭ኛ. አባ /ሄግ/ ማርቆስ ጋሀሊ /በመንበረ ፓትርያርክ ዋና ረዳት/
፮ኛ. ሚስተር ሞሳድ ሳዴቅ ጋዜጠኛ ሲሆኑ ቅዱስ ሲኖዶሱም ልዑካኑን እግዚአብሔር በሥራቸው እንዲያግዛቸውና ምስጢሩን እንዲገልጽላቸው በጸሎት በማሰብ ወደ ቦታው ልኳቸዋል፡፡

እ.ኤ.አ ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፹፮ በእኩለ ሌሊት ልዑኩ ወደ ቦታው በመሔድ በቅርበት ተአምሩን በመመርመር ለመዝገብ ተጓዙ፡፡ በዚያም ከእኩለ ሌሊት እስከ ማለዳ ቆዩ፡፡ ለዐሥር ሰዐት ሃያ ጉዳይ ሲሆን ቅድስት ድንግል ማርያምን በብርሃን ኀርፍ ታጅባ አዩአት፡፡ ይህም መገለጽ እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት ድረስ ቀጠለ፡፡ አባ /Father Heg/ ጊዮርጊስ አሚንም የልዑኩን ሥራ ለመከታተል በዚያ ነበር፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ልዑኩም በራሱ ካየው የእመቤታችን ተአምር በተጨማሪ በዚያ ተሰብስበው ከዚህ እውነተኛ ተአምር በረከት ተካፋይ ከነበሩ ወገኖች ማለትም ከጳጳሳት፣ ከአባ ቶች መነኮሳት፣ በዚያ አጥቢያ ካሉ ምእ መናን፣ ከተለያዩ የእምነት ድርጅቶች መጥተው የሆነውን ካዩ ሌሎች ወገኖች መርምሮ ዘገባ በማደራጀት ለቅዱስ ሲኖ ዶስ አቅርቧል።

በቅድስት ደሚያና ቤተክርስቲያን የነበረው የእመቤታችን አስተርእዮ ልዩ ነበር።

፩ኛ. አስተርእዮው በሌሊት ሳይወሰን በቀንም የተከሰተ መሆኑ፤

፪ኛ. አስተርእዮው በሁለቱ የቤተክርስ ቲያን ማማዎች መካከል በውጪ ብቻ የተ ወሰነ ሳይሆን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በመ ሠዊያው /መንበሩ/ በስተምሥራቅ በውስ ጠኛው የቤተክርስቲያኑ ጉልላት በቅዱሳት ሥዕላት ማስቀመጫ /Iconostasis/ ላይም ነበር።

፫ኛ. አስተርእዮው የእመቤታችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ቅዱሳን ታይተዋል። ቤተክርስቲያኒቱ መታሰቢያ እንዲሆናት የተሰጣት ቅድስት ደሚያናም ታይታለች። ድንግል ማርያም ልጇን ወዳጇን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በክንዶቿ ታቅፋ ታይ ታለች። በተለይም እ.ኤ.አ ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፹፮ የነበራት መገለጥ ይህንን አጉ ልቶ ያሳየ ነበር። ይህም አባ /Father Heg/ ዳውድ ታድሮስ የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ካህን /ገባሬ ካህን/ በሆነ በት ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ በግልጽ ታይቷል።

፬ኛ. ተአምሩም ላንዴ ወይም ለአንድ ቀን ብቻ ሳይሆን የተደጋገመና ለቀናት ቆይቷል።

፭ኛ. የእመቤታችን አስተርእዮ በአን ጸባራቂ ብርሃን ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ጊዜያት ደግሞ በእሳት ነበልባል መልካም ነበር። እነዚህም የእሳት ላንቃዎች ወዲያውኑ ወደ አንጸባራቂ ብርሃን ይለወጣሉ።

በጊዜው በግብጽ ታዋቂ የነበረው ዋታኒ የተባለው ሳምንታዊ ጋዜጣ ሲዘግብ ድንግል




የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተአምሩን እንዲያረጋግጥ የተቋቋመው ልዑክ አባላት

ከእግር እስከ ራሷ በብርሃን ጎርፍ ተከባ ታይታለች ብሏል። በተለይም የብርሃን ጎርፍ የድንግልን ራስ እንደ አክሊል ከቦ ነበር። ድንግል ማርያም ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ እጇን ዘርግታ ትባርካለች፤ አንዳንዴም ያዘኑች መስላ አጎንብሳ ትታይ ነበር።

ከቤተክርስቲያኑ የውስጥ ጉልላት የሚነሣው /የሚፈልቀው/ ብርሃን ወደ ውጪም ያበራል። ከዚያም አልፎ አካባቢውን አል ብሷል። በርቀትም ታይቷል። ጋዜጣው እንዳለው ሚያዝያ ፲ ቀን ፲፱፻፹፮ በነበረው የእመቤታችን መገለጥ የነበረው የብርሃን ነበልባል ከቤተክርስቲያኑ በስተምዕራብ ካለው ማማ እየተረጨ፤ ወደ እርሱም ዳግም እየተመለሰ ለጨለማው ታላቅ ብርሃንን ያጎናጽፈው ነበር። የብርሃን ነበልባሉ /መንታ ላንቃዎች ይመስላሉ። እሳትና የብርሃን ማዕበልም ይፈጥር ነበር። የብርሃኑም መልክ ብርቱካናማ መልክ /ቀለም/ በመሆን ጀምሮ ፍፁም ነጭ ብርሃን ይሆናል።

ቅድስት ደሚያናም የድንግልን መገለጥ በሚያበሥር ዓይነት በስተቀኝ ሆና አረንጓዴ የአበባ ዕቅፍ ይዛ አብራ ተገልጣለች። ከቤተ ክርስቲያኑ ማማ በስተምዕራብ የሚፈልቀው ብርሃን የእንቁላል ቅርጽ /oval shape/ ያለው



የቅድስት ዴሚያና ቤተ ክርስቲያን የመቅደሱ መግቢያ በር

ሲሆን ነጭ ርግብም በብርሃኑ መካከል ታይ ቷል። በቤተክርስቲያኑ አናት ይበር ነበር። ከማማው በስተምዕራብ በሚያንጸባርቀው ብርሃን ላይ ድንግል በግልጽ ትታይ ነበር።

ያ ከምዕራብ የሚወጣው ሰፊ ብርሃን ወደ ምሥራቅ እየፈለቀ በዚያው ላይ ድንግልና ሰማዕቷ ቅድስት ደሚያና ተገልጸዋል። ብርሃኑ ወደ ምዕራብ ሲመለስ ድንግል በምሥራቁ አቅጣጫ በግልጽ እየታየች ትቀር ነበር። እጆቿንም ወደ ሕዝቡ ዘርግታ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ስትንቀሳቀስ /ስትሔድ/ አይተዋታል። ከዚያም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ እያለች እስክት ሰወር ትወጣለች።

ከቤተክርስቲያኑ ማማ በስተምዕራብ የሚወጣው ብርሃን ከእንጨት የተሠራ ለሚ መስለው መስቀል ያበራል። መስቀሉም በነበልባል መልክ ይታይ ነበር።

ቅድስት ድንግል ማርያም በተገለጸችበት በዚያ ተአምር በኮፕቲክ ፊደሎች ጽሑፍም ታይቷል። በቤተክርስቲያኑ መቅደስ ውስ ጥም ካለው መጋረጃና ከእርሱ በላይ ብርሃኑ ይገለጥ ነበር። በዚያም ድንግል ማርያም በውስጥ ትመላለሳለች።

ድንግል ማርያም ሙሉ ነጭ ለብሳ ስትገለጽ በስተምዕራብ ካለው ጉልላት ፊት ለፊት ደግሞ ሰማያዊና ቀይ ቀለም ይታይ ነበር። የአራት ማዕዘን /ሬክታንግል/ ቅርጽ ያለው አንጸባራቂ ብርሃንም በመቅደሱ መጋረጃ ላይ አብርቶ ሦስት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ተመላልሶ በተሰበሰበው ሕዝብ አናት ላይም ታይቷል። በቤተ ክር ስቲያኑ በስተምሥራቅ ባለው ማማ ላይ ደግሞ ብርቱካናማ ደመና ይታይ ነበር። በቤተ ክርስቲያኑም አካባቢ የዕጣን ጢስ ይሸት እንደነበርና በኤሌክትሪክ ኃይል ይሰጥ የነበረው ብርሃን እንዲጠፋ ተደርጐም ከተገለጸው ተአምር የሚወጣው ብርሃን ጸንቶ እንደነበረም ተዘግቧል።

እ.ኤ.አ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፮ የተሰ በሰበው የግብጽ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ዘገባውን ከተቀበለ በኋላ አጠቃላይ የተ አምሩን እውነትነት በመግለጽ፣ እውነተኛ ተአምረ ማርያም መሆኑንም በመመስከር በዚያም ደረጃ እንደሚመዘገብ ወስኗል።ቀ




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በጆሮአችን የሰማነውን በዓይናችን አየነው

## ኢሉባቦር ሀገረ ስብከት

ጌታቸው በቀለ እና መ/ር ሳሙኤል ተስፋዬ



በመቱ የምትገኘው ደብረ ሰላም ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን

በጅማ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ዘገባ እንዳጠናቀቅን ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ አላሰብንም:: በጠቅላይ ቤተ ክህነት ከተሰጠን የድጋፍ ደብዳቤ በተጨማሪ የጅማ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ስልክ በመደወል ምቹ ሁኔታ ከፈጠሩልን በኋላ ጉዟችንን ወደ ኢሉባቦር አቀናን:: በተጓዝንበት ወቅት በዚያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ተዘዋውረን እንድንዘግብ ሁኔታዎችን ላመቻቹልን ኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ ለሊቀ ጉባኤ መሐሪ ጥበቡ ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

ኢሉባቦር በምዕራብ የሀገራችን ክፍል የሚገኝ ክፍለ ሀገር ሲሆን መጠሪያውም ከሁለት ቃላት የተገኘ ነው:: እነርሱም «ኢሉ» እና «አባ ቦራ» ናቸው:: በቀድሞ ስያሜውም 'ኢሉ አባቦራ' በመባል ይታወቃል:: ነገሩ እንዲህ ነው:- በዚህ ሀገር የሚኖሩ 'ኢሉ' የሚባሉ ታዋቂ ባላባት ነበሩ:: የፈረሳቸው ስም ደግሞ 'አባቦራ' ይባላል:: ቦታን በሰው ስም ... ወዘተ መጥራት የተለመደ በመሆኑ ክፍለ ሀገሩም በታዋቂው ባላባት ስም 'ኢሉ አባቦራ' ተብሎ ተሰየመ:: እስከዛሬም ድረስ በዚሁ ስም እንደሚጠራ የአነጋገርናቸው የሀገር ሽማግሌዎች አስረድተውናል::

በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ፪፻፳፪ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: እንደ ዋና ጸሐፊው ማብራሪያ ከሆነ በሀገረ ስብከቱ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በአብዛኛው አገልግሎት እያገኙ ናቸው:: በሳምንት ባይሆን ቢያንስ በወር እንኳ አንዴ ይቀደስባቸዋል:: በካህናት እጦት የተነሣ አገልግሎት የሚታጐልባቸው፣ ለተወሰነ ጊዜ የሚዘጉ አብያተ ክርስቲያናትም አሉ:: ለምሳሌ ሲጠቅሱም ሰሌኖኖ በሚባል የጠረፍ ወረዳ የሚመደቡ ካህናት በቦታው ብዙም አይቆዩም:: በመቱ የማኅበረ ቅዱሳን ማዕከል በደረሰን መረጃ መሠረት በተለያዩ ምክንያቶች የተዘጉ እና የካህናት እጥረት ያለባቸው በርካታ አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: የመቱ ማዕከል ዋና ጸሐፊ ዲ/ን ዳዊት ስማቸው የተዘጉትን ሲዘረ ዝሯቸው ወልተጂ ሚካኤል፣ ቡሩሙ ወረዳ ቀረሲ ልደታ ለማርያም፣ ሱምጣ ጊዮርጊስ፣ መቱ ወረዳ መርዳፍ ኪዳነ ምሕረት፣ ገቺ ወረዳ ሰከቻ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ጐሌ ተክለ ሃይማኖት ኩላዬ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው::

አብያተ ክርስቲያናቱ አፋጣኝ ርዳታ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ምእመናን የተቻላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ዋና ጸሐፊው አሳስበዋል::

ልክ እንደዚሁ ዓይነት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትም ተዘዋውረን ባናያቸውም የአገልጋይ ችግር ያለባቸው፣ የተሟላ አገልግሎት የማይሰጥባቸው እንዳሉ ያነጋገርናቸው ምእመናን ገልጸውልናል::

ሀገረ ስብከቱ እንደዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸውን ቦታዎች በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ቀጣይ አገልግሎት እንዳይቋረጥ የሀገረ ስብከቱን ሠራተኞች በማሰማራት በሰባት ወረዳዎች ላይ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እየሰጠ ነው::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሀገረ ስብከቱ የሥራ ውጤት ከሆነው አንዱ የመቱ ካህናት ማሠልጠኛ ነው:: ማሠልጠኛውን የመሠረቱት ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካልዕ ናቸው:: ማሠልጠኛው የተመሠረተው በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ሲሆን ፳፰ ዓመቱን ይዟል:: በእነዚህ ዘመናት በርካታ ካህናትን አሠልጥኖ አስመርቋል:: ከዚሁ ተቋም የወጡ እስከ ጵጵስና መዓርግ የደረሱ ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስና ብፁዕ አቡነ ሙሴ ይገኙበታል::

ማሠልጠኛው የተቋቋመው በኢሉባቦር አዋሳኝ ለሆኑት አህጉረ ስብከቶች ታቅዶ ነው:: እነዚህም ኢሉባቦር፣ ከፋ፣ አሶሳና ጅማ ናቸው:: በአሁኑ ወቅት ግን እነዚህ አህጉረ ስብከቶች ወደ ማሠልጠኛው ተማሪዎችን አይልኩም:: ምክንያቱም የራሳቸውን ማሠልጠኛ በማቋቋማቸው ነው:: በአሁኑ ወቅት በማሠልጠኛው የሚሠለጥኑት ከኢሉባቦርና ከጋምቤላ የሚመጡ ካህናት ናቸው::

ተማሪዎቹ ከቀለም ትምህርት በተጓዳኝ የሙያ ትምህርት ይማራሉ:: የሙያ ትምህርቶችም የልብስ ስፌት፣ ሽመና፣ ቅርጻ ቅርጽ፣ ንብ ማንባት፣ ዶሮ ርባታ፣ ከብት ማድለብ፣ የወተት ከብቶችን ማርባት እና የጤና ትምህርት ናቸው:: ተማሪዎቹ ያመረቷቸውን የሥራቸውን ውጤት /የተለያዩ አልባሳቶች፣ ቆብ፣ የተለያዩ መስቀሎች በተለያዩ ቅርጻ ቅርጾች የተሠሩ መስቀሎች/ ተመልክተናል:: ከ፳፻ ዓ.ም ጀምሮ ግን የሙያ ትምህርቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች መስጠታቸው ተቋርጦ በቀለም ትምህርት ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኗል:: የዚህም ምክንያት መምህራኑ የሚጠይቁት ገንዘብ ከሀገረ ስብከቱ አቅም በላይ በመሆኑ ነው::

በማሠልጠኛው የተመለከትነው ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ነው:: ተቋሙም የመማር ማስተማሩን ሂደት በበለጠ ለማጠናከር የተለያዩ መርጃ መጻሕፍት የሉትም:: የመብራት የንጹሕ ውኃ አቅርቦት ከፍተኛ ችግር አለባቸው:: ማሠልጠኛው እንደ ቀዳሚነቱ ትኩረት ተሰጥቶት በጀት ተበጅቶለት ሰፊ ክትትል ቢደረግለት ኖሮ ኮሌጅ መሆን የሚችል ነበር:: ማሠልጠኛውን ከተመለከትን በኋላ በቀጥታ ያመራነው ሀገረ ስብከቱ ወደ ሚያካሂደው ልማት ነበር::

ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊትና ታሪካዊት መሆኗን የታሪክ መዛግብት ቢያስረዱና ምስክርነታቸውንም በጉልሕ ጽፈው ቢገኙም ከዚህ የታሪክ ጉዞ ጋር የተለያዩ የልማት ሥራዎች አብረው ተያይዘው የመጡ መሆናቸውንም የታሪክ መዛግብት ያስገነዝባሉ:: በተለይ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙት አጸዶች ቤተ ክርስቲያን ለአካባቢ ጥበቃና ለደን ሀብት ጥበቃ የምትሰጠው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያሉ:: በኢሉባቦርም የምንመለከተው ይኸንኑ ነው::

ደኑም በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ነው:: ቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ዓይነት ደኖችን በመትከሏ የምታገኘው ጥቅም፣ ለሀገሪቱም የምታበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: ሀገረ ስብከቱም እነዚህን ደኖች በመሸጥ እንዲሁም ላቋቋመው የጎጆ ኢንዱስትሪ በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ለሀገረ ስብከቱ ጥሩ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ማድረግ ይችላል::



ሊቀ ጉባኤ መሐሪ ጥበቡ
የመቱ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ

በማሠልጠኛው ፴ ሄክታር የሚጠጋ የልማት ቦታ አለ:: ዋና ጸሐፊው እንዳስጎበኙን ባሕር ዛፍ፣ ሸንኮራ አገዳ፣ ቡና፣ የተለያዩ አትክልቶች ተተክለዋል:: በተለይ የቡና እርሻው የኢሉባቦር ሀገረ ስብከትን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በጉ ሥራ መታሰቢያ ሆኖ በስማቸው ተሰይሟል:: አሁንም ድረስ የአቡነ ኤልሳዕ ቡና፣ የአቡነ ማትያስ ቡና እየተባለ ይጠራል:: ስያሜው ለአካባቢውም መጠሪያ ሆኗል:: በየዓመቱም ከሚለቀመው ቡና ሀገረ ስብከቱ ጥሩ የገቢ ምንጭ ያገኛል::

ሌላው በሀገረ ስብከቱ ከታዘብናቸው ነገሮች ውስጥ የመናፍቃን እንቅስቃሴ እየጨመረ መምጣቱን ነው:: በተለይ የፕሮቴስታንቱ እንቅስቃሴ ዘርፈ ብዙ ነው:: የኑፋቄን ትምህርት በማስተማር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የሚዘምቱት ተጓዳኝ ሥራዎችን ይዘው ነው:: የሕክምና ቡድን በመላክ ችግር ያለበትን ቦታ አይቶ ርዳታ በማድረግ፣ በመኪና፣ በሞተር ብስክሌት፣ በጋማ ከብት ታግዘው ገጠር ድረስ በመጓዝ ምእመናንን እየነጠቁ ይገኛሉ:: የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ ስለሁኔታው ሲገልጹ «በመንግሥት የአስተዳደር ቦታዎች ሳይቀር በአብዛኛው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ካልሆንክ ሓላፊ አትሆንም የተባለ ይመስል ሥልጣን የሚፈልግ ሁሉ ያንን እምነት መቀበል እንደ ቅድሚያ መመዘኛ ተደርጎ ነው የሚታሰበው::» ብለውን ነበር:: ይህም ወደፊትም ሀገረ ስብከቱ በስብከተ ወንጌል ዘርፍ የተጠና፣ የተቀናጀ ሥራ ካልሠራ ትልቅ የቤት ሥራ እንዳለብን ያሳያል::

ሀገረ ስብከቱ እንደ ትልቅነቱና ጥንታዊነቱ ብዙም የጐላ ሥራ የማይታይበት በተለያየ ምክንያት ቢሆንም ዋናው ግን በተደጋጋሚ የሀገረ ስብከቱ ማዕከል መፈናቀል መሆኑ ይጠቀሳል:: ሊቀ ጉባኤ ሲያስረዱ:- በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም የኢሉባቦር ርእሰ ከተማ ከጎሬ ወደ መቱ ሲዛወር ሀገረ ስብከቱም ኅጅ ወጪ የሆነበት ጊዜ ነበር:: በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም በወታደራዊው መንግሥት እንደገና ሀገረ ስብከቱ ታጥፎ ወደ ጅማ ሄደ:: የነበሩትን ንብረቶች ሁሉ አንድም ነገር ሳያስቀር ወደ ሚዛን ተጓዘ:: በዚህም ምክንያት አስተዳደሩ ባዶ ሆኖ ቀረ:: ሀገረ ስብከቱም ለስድስት ዓመታት በጅማ ሀገረ ስብከት ሥር ሆኖ ቆየ:: በኋላም በ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ርእሰ ከተማው ወደ መቱ እንዲመለስ ሲባል ሀገረ ስብከቱ አሁንም አዲስ ጐጆ ወጪ ሆነ:: በእነዚህ ምክንያቶች የሀገረ ስብከቱ እንቅስቃሴ ተዳክሞ ቆይቷል::

## የመቱ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

በመቱ ከተማ ካሉት ስድስት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ የመቱ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነው:: ቤተ ክርስቲያኑ ከከተማው በስተምሥራቅ አቅጣጫ ይገኛል:: በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: የቅዱስ ሚካኤልና የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው:: አስቀድሞ የታነጸው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ደጃዝማች ገነሜ በሚባሉ የኢሉባቦር ጠቅላይ ግዛት አስተዳደር እንደ ተተከለ ይነገራል:: ዓመተ ምሕረቱ ግን በግልጽ አይታወቅም:: ሁለተኛው በ፲፱፻ ፹፯ ዓ.ም የታነጸ ሲሆን በዚሁ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሚካኤል ጽላት እንዲገባ ተደረገ:: በቀድሞው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጽላት ገባ:: ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዘልቀን ስንገባ ዙሪያውን እንደ አጥር የሚያገለግሉ የመካነ መቃብር ቤቶችና ሐውልቶች ተገጥግጠው ይታያሉ:: አንዳንዶቹ የመቃብር ቤቶች ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች፣ ለአባቶች ማረፊያ ወዘተ ጥቅም እየሰጡ የሚገኙ ቢሆንም ቤቶቹ ያረጁና አሠራራቸውም አንድ ወጥ ባለመሆኑ የቤተ ክርስቲያኑን ውበት አደብዝዞታል:: «ቀድሞ የነበሩት አስተዳደርና ሰበካ ጉባኤ በቤተ ክርስቲያን ግቢ ዙሪያ መጠለያ የሚሆነውን ቦታ ለመቃብር መፈቀድ አልነበረበትም:: የመቃብር ቦታ ከአጸዱ ወጪ መሆን ነበረበት» የሚሉት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መልአከ ሰላም ኪሮስ ደጉ ናቸው:: የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊም ቦታው እንደ መዘጋጃ ቤት





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ተሸንሽኖ ለቀብር ቦታ መስጠቱ ተገቢ አለመሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ወደፊትም የመቃብሩ ሁኔታ ዘዴ ሊበጅለትና ወደ ዐውደ ምሕረቱ እንዳይቀርብ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል፡፡

ሰበካ ጉባኤውም ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንቅፋት የማይሆኑ፤ ይልቁንም ቤተ ክርስቲያንን ሊደግፉ የሚችሉ የልማት ተግባራትን ማከናወን ይገባዋል፡፡ እነዚህ ተግባራት መንፈሳዊውን አገልግሎት ከመደገፋቸው በተጨማሪ ገቢ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያንን ወጪ ይሸፍናሉ፡፡ ከልመና ተላቅቀው ሌሎችን ሊረዱ ይችላሉ፡፡

**ቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ዓይነት ደኖችን በመትከሏ የምታገኘው ጥቅም፣ ለሀገሪቱም የምታበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ሀገረ ስብከቱም እነዚህን ደኖች በመሸጥ እንዲሁም ላቋቋመው የጐጆ ኢንዱስትሪ በጥሬ ዕቃነት በመጠቀም ለሀገረ ስብከቱ ጥሩ የገቢ ምንጭ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡**

### የመቱ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም

ከመቱ ከተማ በስተምዕራብ የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም የተመሠረተች ናት፡፡ ታቦተ ሕጉ የገባው በብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ካልዕ ተባርኮ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ እንደ ዛሬው በዘመናዊ ሕንጻ ከመሠረቷ በፊት በትንሽ መቃኞ ውስጥ ነበረች፡፡

በአጥቢያው የሚኖሩ ምእመናን ጠዋት ለቅዳሴ፣ ለኪዳን፤ ማታ ለሠርክ ጸሎት የሚሔዱበት አልነበራቸውም፡፡ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም ስለራቃቸው በቅርብ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች፡፡ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ቦታ ላይ መኖሯ ምልክቱ ጥቅጥቅ ያሉ ዛፎች መኖራቸው በመሆኑ የማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያምም ዙሪያዋን ጥቅጥቅ ባለ ደን የተከበበች ናት፡፡ ኀሊናን የሚያድስ፣ መንፈስን የሚያረካ ከአዕዋፋት ዝማሬ በቀር ምንም የማይሰማባት ምድራዊ ገነት ናት፡፡ ብፁዕ አቡነ ታዴዎስም ይኽን ተመልክተው ጌቴሴማኒ ብለው እንደሰየሟት ከደብሩ ያገኘነው መረጃ የስረዳል፡፡

የመቱ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲነሣ የአባ ጸጋዘአብ ስም አብሮ ይወሳል፡፡ ለቤተ ክርስቲያኗ እዚህ መድረስ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ መልአከ ፀሐይ አባ ጸጋዘአብ ክፍሌ ናቸው፡፡ በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ታመው ተኝተው እንኳ ሊጠይቋቸው የሚሔዱትን ሰዎች በማስተባበር ከሰማንያ ሺሕ ብር በላይ ለሕንጻ አሠሪ ኮሚቴው ገቢ አድርገዋል፡፡ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ድረስ ቀንም ሌሊትም ሐሳባቸው ቤተ ክርስቲያኒቷን ማሳደግ፣ ልማቱን ማስፋፋት ነበር፡፡

ቤተ ክርስቲያኗ ከተመሠረተች ምንም እንኳ አጭር ጊዜ ቢሆንም፤ በልማቱ ረገድ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የገቢ ምንጭ በመፍጠር ላይ ናቸው፡፡ የሰበካ ጉባኤውና የልማት ኮሚቴው በመተባበር ፲፮ ቤቶችን ሠርተው አከራይተዋል፡፡ በተጨማሪም ለሱቅ አገልግሎት የሚሆኑ ቤቶችም ሠርተዋል፡፡



በካህናት ማሠልጠኛው ሥልጠና የወሰዱ ካህናት

በቤተ ክርስቲያኗ ይዞታ ዙሪያ ፳፫ አባወራዎች ለ፷፭ ዓመታት ሠፍረውባት ቆይተዋል፡፡ ቦታውን ለልማት ለማዋል ከሀገረ ስብከቱ ጋር በመሆን ለማዘጋጃ ቤት ካርታና መረጃ በማቅረብ ለቤተ ክርስቲያኗ እንዲመለስ በማድረግ ላይ ሲሆኑ ወደፊትም በዚሁ ቦታ መዋዕለ ሕፃናትና ፩ኛ ደረጃ ት/ቤት ለመክፈት ፕሮጀክት አስቀርጸው በዝግጅት ላይ መሆናቸውን የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ መልአከ ስብሐት ቆሞስ አባ ወ/ጊዮርጊስ ኃይለሚካኤል አስረድተውናል፡፡

በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የሚገኙ ቅርሶች፣ ንዋየ ቅድሳት በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ አስተዳደሩ ቅርሶቹን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስረከብ ዘመናዊ ዕቃ ቤት /ሙዚየም/ ማቋቋም እንዳለበት ሳንጠቁም አናልፍም፡፡ በአሁኑ ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ የሚያገለግሉ አምስት ካህናትና ፲፫ ዲያቆናት አሉ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ያለውን ችግር አስተዳዳሪው ሲገልጹ፡- «ችግሩ የመቱ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በኢሉባቦር ያለ ችግር ነው፡፡ ይኸውም የመናፍቃን መብዛት፣ የቤተ ክርስቲያንን ይዞታዎች መቀማት፣ ምእመናንን በተለያየ መደለያዎች እየተወሰዱ መሆኑ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ ስለዚህ በኢሉባቦር ትኩረት የሚያሻው ነገር የስብከተ ወንጌል መጠናከር ጉዳይ መሆኑንም አስምረውበታል፡፡

አባ ጸጋዘአብ ደከሙ፤ ሰለቹኝ ሳይሉ ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ እንደነበረ ሁሉ አሁንም የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር የእርሳቸውን መልካም አርአያነት ይቀጥሉበት እንላለን፡፡

ከመቱ ከተማ ዘገባ በኋላ ጉዞ ያደረግነው በታሪካዊነቷና በአርአያነቷ ለአንድ ቀን ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ጐሬ ከተማ ነው፡፡ ዝርዝር ዘገባውን በሚቀጥለው እትም ይዘን እንቀርባለን፡፡ ✤

ይቆየን፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዘጠኝ ቁንጮ በአንዲት ጎጆ

ጌታቸው በቀለና መ/ር ሳሙኤል ተስፋዬ



ቅድስት ቤተክርስቲያን ከጌታዋና ከአምላኳ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማረችው እንድታደርግም ከታዘዘቻቸው ተግባራት አንዱና ዋነኛው ችግረኞችን መቀበልና ችግሮቻቸው እንዲቀረፉ ድጋፍ ማድረግ ነው። ይህን ምግባረ ሠናይ በማድረግ የኖረችው፣ እያደረገች ያለችውና ወደፊትም የምትቀጥለው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በየአህጉረ ስብከቶቿም እንዲህ ያሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ትገኛለች።

እጓለ ማውታን መቀበልን፣ በኤች አይቪ የተጠቁ ወገኖችን መንከባከብን፣ በእርዛትና በረኀብ ላሉት መድረስን በየደረጃው ባሉ መዋቅሮቿ ታከናውናለች። ይኸን መሰል ተግባር ከሚያከናውኑት አህጉረ ስብከቶች አንዱ በጅማ ሀገረ ስብከት ሥር ያለው የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ነው። ጽ/ቤቱ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሥርጭትን በመቀነስና ከዚያ ጋር ተያይዞ ጉዳት ለደረሰባቸው አካላት ድጋፍ ከማድረግ አንጻር እርምጃዎቹ አበረታች ናቸው።

የፕሮጀክቱ አስተባባሪ የሆነው አቶ አብርሃም ሞገስ እንደገለጸው ጽ/ቤቱ የሚያከውናቸው ተግባራት ማስተማር፣ ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣ ካህናትና የአቻ ለአቻ ምክር አገልግሎት ለሚሰጡ ወጣቶች ሥልጠና መስጠት እና በሊቀ ጳጳሱ የሚመራ ሐዋርያዊ ጉዞ ማካሔድ ነው።

ያቤት ለቤት የምክር አገልግሎት ሰጪዎች በየሕሙማኑ ቤትና በየሆስፒታሉ እየሄዱ ይመክራሉ፤ ይንከባከባሉ። ወላጆቻቸውን ያጡትን ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ እና የመሳሰሉትን ዐበይት ተግባራት ያከናውናሉ።

በፕሮጀክቱ ሥር ከታቀፉት ፻፷፫ ተረጂዎች መካከል ፻ዎቹ ወላጆቻቸውን ያጡ ሲሆኑ ፷፫ ደግሞ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ናቸው።

በጅማ ሀገረ ስብከት የተከናወኑ ተግባራትን ለመዘገብ ከየካቲት ፳፩ ቀን ፳፻ ዓ.ም በተገኘንበት ወቅት በፕሮጀክቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ውስጥ በግድግዳ ላይ የተሰቀሉ በርካታ ፎቶግራፎች ከነመግለጫቸው ተለጥፈዋል። ከእነዚያ ውስጥ አንድ ፎቶ ግራፍ ትኩረታችንን ሳበው።

ፎቶውም በሊስትሮ /በጫማ ጠረጋ/ ሙያ የተሰማራችውን ወጣት ያሳያል። ወጣቷ እንዴት በዚህ ሙያ ተሰማራች? ብለን ፕሮጀክት አስተባባሪውን አቶ አብርሃም ሞገስ ጠየቅነው። እርሱም የልጅቷንና የቤተሰቧን ታሪክ በጽሑፍ ያዘጋጀውን ሰጠን፤ እኛም እንዲህ አቀናብረነዋል፡-

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ጽ/ቤት ሥር ከሚገኙት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አንዱ የአጋሮ ፈለገ ሰላም ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተስፋ ማዕከል ነው። በዚህ ማዕከል ውስጥ ፳ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትና ፮ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ በፕሮጀክቱ ታቅፈው የራሳቸውን ኑሮ ለማሸነፍ ገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ አብርሃም በፕሮጀክቱ የታቀፉትን መጎብኘት፣ ማስተማርና ማበረታታት የዕለት ተዕለት ተግባሩ ነው። ታዲያ በአንድ ወቅት በፕሮጀክቱ ከታቀፉት ውስጥ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት አሳዳጊዎችን እያነጋገረ ፎርም ይሞላል። ተረኛዋ ወጣት ቀረበች፤ እንደ ተለመደው ጥያቄውን አቀረበላት «ቤተሰቡ ውስጥ ያለው ወላጅ አልባ ብዛት ምን ያህል ነው?» ሲላት አንገቷን እንደማቀርቀር ብላ «ዘጠኝ አለች» አብርሃም ጥያቄው ያልገባት መስሎት «የቤተሰቡን ብዛት ሳይሆን ወላጅ የሌላቸው ሕፃናትን ማለቴ ነው» አላት። የልጅቷን ሕይወት በደንብ የሚያወቀው በአጠገቡ የነበረው




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የጎማ ወረዳ ሊቀ ካህናት ቀሲስ ታጋይ ታደለ «እውነት ነው ዘጠኝ ናቸው፤ እናትና አባታቸው ዐርፍዋል:: ቅድም ስንመጣ ጫማ የጠረገችልህ ልጅ እኅት ናት ይለዋል::» አብርሃም ጉዳዩ አእምሮውን ዕረፍት ነሳው::

አስቀድሞ ወደ አጋሮ ፈለገ ሰላም ቅድስት ማርያም «የተስፋ ማዕከል» ሲመጣ የቀጠሮው ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ጽጌረዳ ሆቴል አጠገብ ጫማውን ለማስጠረግ ሲቀመጥ ወጣቷ ፀጉሯን በማሳጠሯ ወንድ የመሰለችው ለካስ የዘጠኙ የቤተሰብ መሪ መብራት ለገሰ ነበረች:: የመብራትን ቆራጥነትና ሥራ ወዳድነት እያደነቀ፤ በሥራዋ ቅልጥፍና እየተገረመ፣ ጫማውን አስጠርጎ ወደ ቀጠሮው ቦታ ተጓዘ::

አብርሃም ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትን ከሚያሳድጉ ጋር የነበረው ውይይት እንደ ተጠናቀቀ የእነመሠረትን ጉዳይ ለማወቅ ፈለገ:: አጠገቡ የነበሩትን ወላጅ አልባ ሕፃናት፣ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩትን ሰዎች፣ የሚከታተሉትን ረዳት የምክር ሰጭዎችን ስለመሠረትና ቤተሰቧ እንዲያስረዱት



በሊስትሮነት ቤተሰቧን እያስተዳደረች ያለችው መብራት ለገሰ

ጠየቀ፤ ሙሉ መረጃም አገኘ:: በአንዲት ደሳሳ ጎጆ ሥር የሚኖሩ ዘጠኝ ሕፃናት ችግርና ሰቆቃ መስማት ለአእምሮ የሚከብድ፤ ለማመንም የሚያዳግት ቢሆንም ለጊዜው ለችግራቸው ለመድረስ በማዕከሉ እንዲታቀፉና ርዳታ እንዲያገኙ አደረገ::

አባታቸው ለብዙ ጊዜ በሕመም ሲሰቃዩ የኖሩ ናቸው:: ኑሯቸውም ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ ሆስፒታል ሄዶ ለመታከም አቅሙ አልነበራቸውም:: እየታመሙ ልጆቻቸውን ለማሳደግ ደፋ ቀና ይሉ ነበር:: ሕመሙ ጸናባቸውና ለወራት የአልጋ ቁራኛ ሆኑ:: ኋላም ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ:: የቤተሰቡ ኑሮ እየከበደ መጣ:: እናታቸውም በሽተኛ ሆኑ አልጋ ያዙ:: ቤተሰቡም የመከራ ኑሮ ለመግፋት ተገደደ:: ልጆቹም እናታቸውን እያዩ ከማንባት በስተቀር ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም::

ጤና ጣቢያ ሄደው ቢታከሙም መፍትሔ ሊያገኙ አልቻሉም:: ከአንዱ ሐኪም ቤት ወደ ሌላው ቢሄዱም ያው ነው:: መፍትሔ የሌለው ነገር ሆነባቸው:: በዚያ ላይ የልጆቻቸው ነገር ቀን ዕረፍት ሌሊት እንቅልፍ እየነሳቸው ለሁለት ዓመታት ተሰቃዩ:: የአካባቢያቸው ነዋሪዎች በቀበሌ አስተባባሪነት ገንዘብ አዋጥተውላቸው ነበር:: ጅማ ሆስፒታል ሄደው የኤች አይ ቪ /ኤድስ ምርመራ እንዲያደርጉ ቢታሰብም ገንዘቡን ስታሰባስብ የነበረችው ሴት ገንዘቡን ይዛ በመጥፋቷ ወደ ሆስፒታል ሄደው ሳይመረመሩ ለስድስት ወራት አልጋ ላይ ዋሉ:: የነበራቸውንም ጥሪት ሁሉ ሸጡ:: ቤቱ ባዶ ሆነ:: እናታቸውም ዛሬ ነገ ድኜ እያሉ ተስፋ ቢያደርጉም በሽታው ጸንቶባቸው ከሚወዷቸው ልጆቻቸው ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::

እናታቸው ሲሞቱ መብራት የ፲፯ ዓመት ልጅ ነበረች:: ለቤተሰቡም ሁለተኛ ልጅ ናት:: ለቤተሰቡ አራተኛ ልጅ የሆነችው እኅቷ መሠረት ለገሠ ደግሞ የ፲፫ ዓመት ልጅ ነበረች:: እንዴት ይኖሩ እንደነበረ መብራት ስትናገር «እናትና አባቴ ሲሞቱ የ፰ኛ ክፍል ተማሪና የ፲፯ ዓመት ልጅ ነበርኩ:: አባትና እናቴ በሕይወት ሳሉ ከቤታችን ሰው ጠፍቶ አያውቅም፤ እነርሱም ይሄዳሉ:: ይጠይቃሉ:: ጥሩ ማኅበራዊ ግንኙነት አላቸው:: ከሞቱ በኋላ ግን ቤታችን ዝር የሚል ሰው ጠፋ:: የቤተሰቦቻችን ወዳጆች የነበሩት ጎረቤቶቻችንም ሳይቀሩ ሸሹን:: የወላጆቻችን ሐዘን ልባችንን ክፉኛ ማቁሰሉ ሳያንስ የጎረቤቶቻችን ሽሽት ደግሞ ቅስማችንን ሰብሮት በኅሊናችን የማይሻር ጠባሳ አኖረብን»::

መሠረትም ስለ ወላጆቿና ያሳለፉትን ሁኔታ ከዕንባዋ ጋር እየተናነቀች ስትገልጽ «እናታችን በሕይወት እያለች ምታውቀው ሰው ቀርቶ የማታውቀውን ችግረኛና ዘመድ የሌለው ሰው ሞተ ሲባል እንኳ ቀድማ የምትደርስ፣ የምትገንዝና ከለቅሶው ሳትለይ የምትቀብር ሰው ነበረች:: እሷ ስትሞት ግን የሚገንዛት አጣች:: ያን ሁሉ ሰው የምታውቅና የከተማው ነዋሪም አልመሰለችም:: እንደ መጤ ነው የታየችው:: ብቻ እንደምንም ተቀበረች:: ቤታችንም ከዚያች ቀን ጀምሮ ጭር አለ:: ሰማይ ምድሩ ተከደነብን:: የቀን ጨለማ ዋጠን:: ምን እንብላ? ምን እንጠጣ? ወትሮም ከእጅ ወደ አፍ የነበረው ኑሮአችን አሁን ባሰ:: በእንቅርት ላይ እንደሚሉት ሆነብን:: እናታችን አልጋ ላይ በመዋሏ ያሉንን ጥሪቶች ሁሉ አውጥተን ሸጠን ጨርሰናል:: አሁን ባዶ ቤት ውስጥ ተዘግተን ጾም ውሎ ጾም ማደር ዕጣ ፈንታችን ሆነ::» ነበር ያለችው::

መብራት የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኗ መጠን እናትና አባታቸው ሲሞቱ የቤተሰቡ ሸክም ሁሉ የወደቀው በእርሷ ላይ ነው:: በዚህም የተነሣ ቀድሞም እናቷን በማስታመም ያዝ ለቀቅ ስታደርገው የነበረውን ትምህርቷን ጭራሹኑ አቋረጠች::

ጠያቂ ዘመድ ወዳጅ በታጣበት ሰዓት ስምንት ታናናሽ እኅቶችን በባዶ ቤት ይዞ መማር እንዴት ይቻላል? ማስተዳደሩስ እንዴት አይፈትናት? መብራት ዕንባዋ እየተናነቃት ያሳለፈቻቸውንም ጊዜያት መናገር ቀጠለች:: የሚበላና የሚቀመስ በሌለበት ቤት ውስጥ እነዚህ ሕፃናት ሲያለቅሱ፣ ሲተራመሱ ስመለከት ራስሽን አጥፊ ነበረ የሚለኝ:: ነገር ግን የእኔ ሞት ለታናናሾቼ የሚፈይድላቸው ነገር ስለማይኖር አንድ ነገር ወሰንኩ፤ የቀን ሥራ ለመሥራት:: በአካባቢያችን ቤት ወደሚሠሩ ግንበኞች ሄጄ እንዲቀጥሩኝ ችግሬን ነግሬ ለመንኳቸው:: እነርሱም ቀጠሩኝ:: በቀን ፯ ብር እየተከፈለኝ ድንጋይ መሸከም ጀመርኩ:: እንደ ሌላው ሠራተኛ በየሳምንቱ ሳይሆን ያችን ፯ ብር በየዕለቱ እየተቀበልኩ ለእራትና ምሳ የሚሆነንን ጥራጥሬና ዳቦ እየገዛሁ ረኀባችንን ለማስታገስ ሞከርኩ»

ይሁን እንጂ የቀን ሥራው መብራትን ከበዳት:: ባልበላ አንጀቷ ድንጋይ መሸከም እንዴት ትቻለው? በዚህም የልጆቹን ረኀብ ልታስታግስ ባለመቻሏ፣ እሷም በመጎዳቷ ሌላ ሥራ ፈለገች::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## «ጠያቂ ዘመድ ወዳጅ ቤታጣበት ሰዓት ስምንት ታናናሽ እኅቶችን በባዶ ቤት ይዞ መማር እንዴት ይቻላል? ማስተዳደሩስ እንዴት አይፈትናት? መብራት ዕንባዋ እየተናነቃት ያሳለፈቻቸውንም ጊዜያት መናገር ቀጠለች።

በአጋሮ ከተማ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ የቡና መፈልፈያ ሥራ እንዲያሠሯት ሃዳ ጠየቀች። እርሱም ያለው ሥራ ኩንታል መሸከም መሆኑን ነገሯት። መብራት ግን ችግሯን ስለምታውቅ አላንገራገረችም፤ ጊዜ የማይሰጠውን የታናናሾቿን ረኀብ አስታውሳ ለመሸከም ተስማማች። በቀን ፲ ብር እየተከፈላት መሥራትም ጀመረች። እርሷም ስትናገር «በማገኛት ገንዘብ ይህንን ሁሉ ቤተሰብ ማስተዳደር ባለመቻሌ ሎሚና ብርቱካን እየገዛሁ እኅቶቼ ከትምህርታቸው መልስ እያዞሩ እንዲሸጡ አደረግሁ። ምንም እንኳ ትምህርታቸው ላይ ተፅዕኖ ቢኖረውም። በዚህም ምንም ትርፍ ማግኘት ስላልቻልን ከእኅቶቼ ጋር ተነጋግረን አንድ ውሳኔ ላይ ደረስን። አንድ ቦታ ፈልገን እኔ ሊስትሮ መሥራት እንዳለብኝ ተስማማን። ከዚያም ጽጌረዳ ሆቴል አጠገብ አንድ ወንበርና የሊስትሮ ዕቃ አስቀምጬ መሥራት ጀመርኩ።»

መብራት የሊስትሮ ዕቃ ይዛ ለሥራ ስትዘጋጅ ከማኅበረሰቡ የቀረበላትን ምላሽ ስትገልጽ «ሥራ ስጀምር ብዙዎቹ የአጋሮ ነዋሪዎች የቤተሰቦቻችንን ሁኔታ ስለሚያውቁ ቀለም በመግዛት አበረታተውኛል። ብዙዎቹ ‹ከሊስትሮ ደረጃ ተነሥተው ከፍተኛ ቦታ የደረሱ አሉ አንቺም በርቺ› እያሉ የመከሩኝ አሉ። በአንፃሩ ደግሞ ሴትነቴን ለክፉ ሐሳባቸው መጠቀሚያ ሊያደርጉ የሚፈልጉ ሰዎችም አጋጥመውኛል። በአጠቃላይ የጎዳና ዳር ሕይወቴ በጎውንም ክፉውንም እንዳስተውል አድርጎኛል።» ብላ ነበር።

መብራት ከድንጋይ እና ኩንታል ተሸካሚነት፣ ከሊስትሮነት በተጨማሪም በየመሐሉ ሰው ቤት በተመላላሽነት ከመሥራቷም በላይ ለሴት ልጅ ከባድ ናቸው የሚባሉትን ሥራዎች ሁሉ ያለ መሰልቸት ሠርታለች። ዛሬ በሀገራችን ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ብዛት ያላቸው ሕፃናትንና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችን እየረዱ ቢሆንም መብራትና እኅቶቿ ግን በመገናኛ ብዙሃንና በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሰዎች ከሚሰሙት፣ ጎረቤቶቻቸው ከሚነግሯቸው በስተቀር ምንም ያገኙት ነገር የለም።

ከዕለት ሥራቸው ጋር የሰማዩን አምላክ እግዚአብሔርን መማጸን አላቆሙም። ዛሬም ከችግራቸው ጋር በፍቅር ተስማምተው ይኖራሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የጅማ ሀገረ ስብከት ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣሪያ ጽ/ቤት በአጋሮ ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተስፋ ማዕከልን በማቋቋም ወላጅ አልባ ሕፃናትን እና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችን ለመርዳት ዕቅድ እንዳለውና የሚመለከታቸው መጥተው እንዲመዘገቡ መጥራቱን ሰማች። በዚያም ታናሽ እኅቷን አስመዝግባ መጣች። ከማዕከሉም የተለያዩ ድጋፎችና ገንቢ የሆኑ ምክሮችን አገኙ። ለጊዜው የገቢ ማስገኛ የሚሆን ሥራ እንዲሠሩበት ፲፱ ብርና ለአራት ወራት ያህል በየወሩ ፮ ብር ርዳታ አገኙ። ገንዘቡ በቂ ባይሆንም ለጊዜው ተስፋ በማግኘታቸው እየበረቱ፤ እግዚአብሔርን እየለመኑ፤ የወላጆቻችን ነፍስ እንዲምር እግዚአብሔርን እየተማጸኑ ሥራቸውን ጀመሩ።

«ቤተክርስቲያን የደረሰችልን ቤተሰባችን በከፍተኛ ችግር ውስጥ ባለበት፣ ቤታችንም ፈርሶ ላያችን ላይ ሊወድቅ በተቃረበበት ወቅት ነው። በተሰጠን ድጋፍ ብርድን ለመከላከል ቤታችንን አሳደስኩበት። ሊስትሮዬን እየሠራሁ፤ በተጓዳኝም የተለያዩ አትክልቶችን እየገዛሁ በመሸጥ፣ እኅቶቼም በትርፍ ጊዜያቸው እየዞሩ እንዲሸጡ በማድረግ ኑሮአችንን ለማሻሻል እየጣርን ነው።» ትላለች መብራት።

መሠረትም «እኅታችን በተስፋ ማዕከሉ ከታቀፈች በኋላ ረዳት የምክር ሰጭዎችና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች እየመጡ ይጠይቁናል። በተለይ አሁን እኔ በአጋሮ ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በማገልገል ላይ በሚገኘው የመድኀን ፀረ ኤድስ ክበብ አባል በመሆኔ ብዙ ትምህርት አግኝቻለሁ። ብቻችንን እንደሆንን እና ወላጆች የሌላቸው ሕፃናት ስሜት እንዳይሰማን አድርገውናል።» ብላለች። እኅቷን ተከትላ መብራት ደግሞ እንዲህ ብላ ነበር። «እግዚአብሔር ይመስገን በፊት በፊት ከግንበኞች ጋር ድንጋይና ቡና መፈልፈያ ውስጥ ስሠራ በየቀኑ የማገኘውን ገንዘብ ለዕለት ቀለባችን ነበረ የማውለው። ሥራ በሌለ ቀን ምንም ሳንቲም ስለማላገኝ ባዶ እጄን ስገባ እነርሱም እንደ እናት አንድ ነገር ይዛልን ትመጣለች እያሉ ውጭ ውጪውን አንጋጠው ይጠብቁኛል። በዚህ ጊዜ ልጆቹን ሳያቸው ሆድ ብሶኝ ወደ ጓሮ ሄጄ ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ። ጥራጥሬም ሆነ ሌላ ነገር በዱቤ አምጥቼ ቀምሰን እናድራለን።

በአሁኑ ወቅት ለዕለት ጉርሳችን ሊስትሮ እየሠራሁ ነው። ሁለት የሊስትሮ ሳጥኖች አሉኝ። በአንዱ ላይ በቋሚነት እሠራለሁ። በሁለተኛው ላይ ደግሞ እኅቶቼ በፈረቃ ይሠራሉ። በዚህም እግዚአብሔር ጤና ሰጥቶን የዕለት ምግባችንን ቀምሰን እናድራለን። ብዙ ጊዜ እህል ገዝተን አስፈጭተን፣ አቡክተንና ጋግረን ባንበላም የበሰለ ነገር እየገዛን እንበላለን፤ እግዚአብሔር ይመስገን። አንዳንዴ ከአቅማችን ባላይ ተደራራቢ ችግር ያጋጥመናል። ከእጅ ወደ አፍ በሆነው ኑሮአችን የት/ቤት ክፍያ፣ የደብተር፣ የዩኒፎርም ማሰፊያ በተለይ ደግሞ ከቤት ውስጥ አንድ ልጅ ከታመመ ለማስታመም ያለብንን ጭንቀት ምን ብዬ ልናገር?»

«ልጆቹ ነፍስ እያወቁ ሲሄዱ የእኛን ኑሮ ከጓደኞቻቸው ጋር እያነፃፀሩ ሆድ እየባሳቸው መጣ። ታዲያ ይህን ሁሉ ወጪ እንዴት እንቻለው? ቤተሰቤን ለማስተዳደር ሥራ ሳልንቅ እሠራለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን ወደፊት ፈቃዱ ከሆነ ሁሉን ነገር ሊያሟላልን ይችላል።» ነበር መልሷ። ዐይኗ ዕንባ አቀረረ፤ በልጅነት ዕድሜዋ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆንን እንዴት ትቻለው? አቤት ጽናት!!!

ወላጆቻቸውን ያጡት ሕፃናት ለነገ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገዋል እግዚአብሔር ደግሞ ሕፃናቱን እናለብስ፤ እንመግብ፤ እናጽናና፤ እንመክር ዘንድ ሓላፊነት ሰጥቶናል። ሕዝበ ክርስቲያን እንዲህ ያለ የውጥረት ኑሮ ለሚገፉ ሕፃናት

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን *«አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት»* የተሰኘ ዓምድ ከ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል። በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በተቋቋመው *«የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር»* የሚዘጋጅ ነው። ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው።

*መ/ር ደሴ ቀለብ*

## ጥቂት ስለ ግእዝ ቋንቋ ተመራማሪዎች

ግእዝ ቋንቋን በተመለከተ ብዙ የውጭ ሀገር ምሁራን፣ የቋንቋ ሊቃውንት ሌሎችም ከተሰማሩበትና ከዋና የሥራ መስካቸው በመለየት ዘመናቸውን አሳልፈውበታል። ኢትዮጵያውያን በግእዝ ቋንቋቸው መግባቢያነት ወደ ሌሎች የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ከተሸጋገሩበት ጊዜ ጀምሮ በቋንቋው የተጻፉትን፣ የተደረሱትን ድርሰቶች ሁሉ በመማር፤ በማስተማር፤ በማጥናት፤ በማስተላለፍ የደከሙበት አበው ሁሉ ቋንቋውን ለማስተዋወቅ ታግለዋል። የውጮቹን ምሁራን ተሳትፎ ለመጥቀስ ያህል ከከሣቴ ብርሃን ሰላማ ጀምሮ ተስዓቱ ቅዱሳን በመጻፍ በመማር በማስተማር መጻሕፍትን በመተርጎም በማስተርጎም ተሳትፈውበታል። ይሁን እንጂ የቋንቋውን ሥርዐተ ሰዋስው ለማጥናት እና የቋንቋውን የትመጣ ለመመርመር የደከሙት ግን ከ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ይረዳል። «የመጀመሪያውን» የግእዝ ሰዋስው ያሳተመው ጀርመናዊው ኢዮብ ሉዶልፍ በአባ ጎርጎርዮስ እርዳታ በ፲፮፻፷፩ ዓ.ም /እ.አ.አ/ ሲሆን በተመሳሳይ በ፲፮፻፺፰ ዓ.ም የአማርኛን ሰዋስው አሳትሟል። በአንዳንዶች ዘንድ የመጀመሪያው የግእዝ ሰዋስው በሮም /አውሮፖ/ ተብሎ የሚታመን በ፲፯፻፴፰ የተሠራው የጀወመር ሥራ ሲሆን ግእዝን በተመለከተ መጻሕፍትን ለማሳተም ግን በ፲፭፻፲፫ ዓ.ም የታተመው የፔትኪን መጽሐፍ ቀዳማዊ መሆኑ ይታወሳል። እንዲሁም በ፲፭፻፶፪ ዓ.ም የታተመው የግእዝ ሰዋስው መልክዕ ገላጭ የማሪያነስ ቪክቶሪየስ ነው። ከፔትኪን እና ከማሪያነስ ቪክቶሪየስ ግን የዐረብኛ እና የዕብራይስጥ ቋንቋ ዕውቀቱን የተጠቀመበት የኢዮብ ሉዶልፍ ሥራ የተሻለ ነበረ። ጀርመናዊው አውገስት ዲልማንም/ ሰዋስው በ፲፰፻፶፯ ዓ.ም፤ መዝገበ ቃላት ፲፰፻፷፭ ዓ.ም በላቲን/ ያለፉትን መዛግብት በመጠቀም ያዘጋጀው ሥራ በግእዝ የተሰማሩ ሊቃውንትን፣ ደቀ መዛሙርትን በመርዳት የሚያህለው የለም። ብዙዎችን ይጥቀም እንጂ ዲልማን የግእዝን አነባበብ ሥርዐት ለማስቀመጥ ያደረገው ጥረት ስኬታማ ነበር ለማለት እንደማይቻል ሁሉ የግእዝን ቀዳማይ አንቀጽ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስረዳት የተጠቀመበት የንዑስ አንቀጽ ትርጉም ግን እንደ ድክመት ሊታይ የሚችል ነው። ለጀማሪ የግእዝ ተማሪዎች ሊረዱ የሚችሉ መጻሕፍትን ከሠሩት ከፕሪቶሪየስ እና ቼል ጀምሮ ኮንቲሮሲን፣ ሊትማን ሚትወች /ስለ ሥርዐተ ንባብ/ እና የተሻለ የግእዝ መዝገበ ቃላት እስካዘጋጀው ወልፍ ሌስሎው እና ሌሎችም ድረስ በግእዝ ቋንቋ ላይ የተደረጉት ምርምሮች አበረታች ነበሩ። ከሀገር ውስጥም ሊቃውንት ለግእዝ ሰዋስው መጠበቅ፣ ለሥነ ጽሑፍ እድገቱ መዳበር በመጽሐፍ ዝግጅቱ ከቀደምቱ አባ ተክለ ማርያም ወልደ ሰማሃራይ፣ አባ ያዕቆብ ገብረ ኢየሱስ፣ አለቃ ታየ፣ ክፍለ ጊዮርጊስ እና አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከቅርቦቹ ደግሞ አስረስ የኔሰው፣ ዓለማየሁ ሞገስ፣ ዜና ማርቆስ፣ አፈ ወርቅ፣ ይትባረክ፣ ያሬድ ፈንታ፣ ዘርዐ ዳዊት፣ በላይ መኮንን... ሲጠቀሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መጽሐፈ ሰዋስው ከሚለው በተጨማሪ በየዘመናቱ በምታሳትማቸው መጻሕፍት እና በሀገር መዐዛዎቹ ጉባኤ ቤቶቿ ያበረከተችው አስተዋፅኦ ታላቅ እና ሕያው ነው።

## «ከጸሎትና ከጾም ... »

ከገጽ ፯ የዞረ

በማኅበርና በሀገር ደረጃም ለሚያስቃየን አብሮ አደግ ፈተና /ችግር/ ሁሉ ጾም ጸሎት በእውነት ኃይልን ያደርጋል። ከእኛ ብቻ ሰይጣንን ለማሳደድ ሳይሆን ከባልንጀሮቻችንም ጭምር በመሆኑ ከእነርሱም ወጥቶ እንዲሰደድ በጾም በጸሎት ስላልተመላለሱ ምእመናንም መቆም ይገባናል። የእኛ ድካም ለእነርሱ አይሠራም በማለት በጥርጥር እንዳንያዝ ያስፈልጋል። ለእነርሱ ረድኤተ እግዚአብሔርን ለማቅረብ የእኛም እውነተኛ እምነትና ጾም ጸሎት ካለ ይሳካል። አስከሬን ይዘው በኤልሳዕ መቃብር ላይ የጣሉትና ያም ሙት እንዲነሣ ምክንያት ስለሆኑት ሰዎች እናስብ። በእምነት በጾምና በጸሎቱ ጌታችን ወደ ሊቀ ሐዋርያት ያቀረበው ቆርነሌዎስ አብረውት ለነበሩት ዘመዶቹና የቅርብ ወዳጆቹ ጸጋው እንዴት እንደተረፈ እናስተውል። /፪ነገ.፲፫÷፳፩፤ የሐዋ.፲÷፳፬፣ ፵፫/

በመሆኑም ለእኛም ለባልንጀሮቻችንም መንፈሳዊ ኃይልን አግኝተን በጠላታችን ላይ እንድናይል ከፊታችን የሚገጥመንን የጾመ ነቢያት ጊዜ ሁላችንም እንድንጠቀምበት የፈጣሪ እርዳታ፣ የቅዱሳንም አማላጅነት አይለየን፤ አሜን።፨

## ወላጆቻቸውን ...

ከገጽ ፴፰ የዞረ

ድጋፍ እንድናደርግላቸው፤ ከጐናቸው በመሆን ልናበረታታቸው ይገባል። በየአጥቢያችን ዙሪያ ያሉ አማኞችንም ሆነ የማያምኑ ችግረኞችን በመደገፍ የክርስቶስን ፈቃድ መፈጸም ይገባናል። በየአጥቢያችን ቤተክርስቲያን በመዋቅሯ ለምትሰጠው አገልግሎት ፈጥኖ ከመድረስ ተግባር በተጓዳኝ ምእመናን ተሰባስበን ያቅማችንን ያህል አስተዋጽኦ በማድረግ ችግረኞችን እንድንደግፍ ቤተክርስቲያን ዘውትር ታሳስባለች። ይህን በጐ ተግባር ፈጽመን ከተገኘን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማሳለፍ ዳግመኛ ሲመጣ «እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና...» ማቴ ፳፭÷፴፬-፴፯። የሚለውን የሕይወት ቃል እንድንሰማ ያበቃናል።፨

### «ጩኸ ጩኸ የሚል ድምፅ!
### ምን ብዬ ልጩኸ?»

ባለፉት እትሞቻችን ስለመዝሙር ባቀረብንበት ወቅት አንዳንዶቻችሁ «የስብከቱን ነገር ለምን ተዋችሁት?» የሚሉ አስተያየቶችን ስትሰጡን ነበር። በዚህ መሠረት ከሚቀጥለው ዕትም ጀምሮ **ስብከትንና ሰባክያንን** አስመልክቶ የውይይት ዓምድ እንከፍታለንና እንደተለመደው ትሳተፉ ዘንድ ተጋብዛችኋል። ስለዚህ

- ግለሰባዊ ያልሆነ
- ተጨባጭ ችግሮችን የሚያሳይ
- ገጠመኞችን ያካተተ
- ችግሮቻችን አሳይቶ መፍትሔ የሚጠቁም በማድረግ ጻፉልን።

*«ጩኸ ጩኸ የሚል ድምፅ !*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# የዐቢይ አንቀጽ እርባታ

## በቀዳማይ አንቀጽ /Past tense/

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩. ውእቱ - ቀተለ -ገደለ | - | He killed - እሱ ገደለ | |
| አነ - | I ቀተለኒ | - | He killed me - ገደለኝ |
| አንተ - | You ቀተለከ | - | He killed you - ገደለህ |
| አንቲ - | You ቀተለኪ | - | He killed you -ገደለሽ |
| አንትሙ - | You ቀተለክሙ | - | He killed you -ገደላችሁ |
| አንትን - | You ቀተለክን | - | He killed you - ገደላችሁ |
| ንሕነ - | We ቀተለነ | - | He killed us - ገደለን |
| ውእቱ - | He ቀተሎ | - | He killed him - ገደለው |
| ይእቲ - | She ቀተላ | - | He killed her - ገደላት |
| ውእቶሙ - | They ቀተሎሙ | - | He killed them - ገደላቸው |
| ውእቶን - | They ቀተሎን | - | He killed them - ገደላቸው |

*ማስታወሻ፦* በአማርኛ «ህ» ከ፣ ኽ እየሆነ ያገለግላል:: ይህ ደግሞ የድምዕ ለውጥን ሲያሳይ መሠረታዊው የግእዝ ከ ወደ ኽ /Spiratized/ እና ሀ መለወጡ ነው:: ኽ የሚባል ድምጽ በግእዝ የለም:: በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር «ንሕነ» /we/ «እኛ» ደግሞ አማርኛው የግእዙን «ነ» ሲፈ ልግ እንዳለ አንዳንዴም ወደ «ን» ለውጦት እናገኛለን: እንደተናጋሪው:: ምሳሌ: ቀተለነ ገደለን/ ገደለነ:: «ን» እንደ አዲስ አበባ አማርኛ፣ «ነ» ደግሞ እንደ ጎንደር ... አማርኛ:: ትግርኛም የግእዙን «ነ» ወደ «ና» «ለውጦ» ይጠቀምበታል:: ምሳሌ ሀገርነ ሀገራችን ሀገርና /በትግርኛ/::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፪. ይእቲ - ቀተለት | | She killed | - | እሷ ገደለች |
| ቀተለተኒ | - | She killed me | - | ገደለችኝ |
| ቀተለተከ | - | She killed you | - | ገደለችህ |
| ቀተለተኪ | - | She killed you | - | ገደለችሺ |
| ቀተለተክሙ | - | She killed you | - | ገደለቻችሁ |
| ቀተለተክን | - | She killed you | - | ገደለቻችሁ /ለሴቶች/ |
| ቀተለተነ | - | She killed us | - | ገደለችን |
| ቀተለቶ | - | She killed him | - | ገደለችው |
| ቀተለታ | | She killed her | - | ገደለቻት |
| ቀተለቶሙ | - | She killed them | - | ገደለቻቸው |
| ቀተለቶን | - | She killed them | - | ገደለቻቸው |
| ፫. አንተ - ቀተልከ - | | You killed | - | ገደልህ |
| ቀተልከኒ | - | You killed me | - | ገደልኸኝ |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| ቀተልከነ | - | You killed us | - | ገደልከን |
| ቀተልኮ | - | You killed him | - | ገደልከው |
| ቀተልካ | - | You killed her | - | ገደልካት |
| ቀተልኮሙ | - | You killed them | - | ገደልካቸው |
| ቀተልኮን | - | You killed them | - | ገደልካቸው |
| ፬ አንቲ - ቀተልኪ | | - You killed | - | ገደልሺ |
| ቀተልኪኒ | | - You killed me | - | ገደልሺኝ |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| - | - | - | | - |
| ቀተልኪነ | - | You killed us | - | ገደልሺን |
| ቀተልኪዮሙ | - | You killed them | - | ገደልሻቸው |
| ቀተልኪዮን | - | You killed them | - | ገደልሻቸው |

ፌ በልማድ /በድምጽ ለውጥ ቀተልኪኒ ቀተልክኒ ኪ ክ/ ሺ ሽ/:: ኒ/ግእዝ/ ኚ/ኝ/ አማርኛ/

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፭. አነ - ቀተልኩ - | I killed | - | ገደልሁ |
| - | - | - | - |
| ቀተለኩከ - | I killed You - | | ገደለሁህ |
| ቀተለኩኪ - | I killed you - | | ገደልሁሺ |
| ቀተለኩክሙ- | I killed you - | | ገደልካችሁ |
| ቀተልኩክን - | I killed you - | | ገደልኳችሁ |
| ቀተልክዎ - | I killed him - | | ገደልኩት |
| ቀተልክዋ- | I killed her - | | ገደልኳት |
| ቀተልክዎሙ- | I killed them - | | ገደልኳቸው |
| ቀተልክዎን - | I killed them- | | ገደልኳቸው |

/*ማስታወሻ፣* «---» የሚያመለክተው በቋንቋ ሥርዐት ውስጥ ቃሉ ቢባል ወይም ሊጻፍ ቢችል እንኳን ትርጉም የማይሰጥ መሆኑን ነው:: ምሳሌ፦ ቀተልኩ /ገደልኩ/ እንጂ ራሴን ገደልኩ ለማለት ቀተለኩኒ /ቀተልኩ ኪያየ ራሴን ገደልኩ እንጂ/ አለመባሉን ያሳታውሰናል:: ቀ

*ይቆየን::*

## ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ...

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ሌሊትና ቀን በዕንባ እያንዳንዳችሁን ከመ ገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ::» /የሐዋ.፳፥፴፩/:: የእርሱ ሕይወት የተቀ ደሰ ሆኖ ሳለ ዕንባው ወይም የተግሣጽ ቃሉ ሕግጋትን እንዲጠብቁ ሊያነሣሣ ቸው ሊያስተምራቸውና ደኅና አድርጎ ሊረዳቸው ይችላል:: ሆኖም ግን ይህ ብቻ ሁሉንም ነገር ይፈጽማል፤ ይበቃል ማለት ግን አይቻልም::

የሃይማኖትን /ዶክትሪን፥ዶግማን/ የተ መለከተ ጸብ፣ ክርክር በተነሣ ጊዜ፥ ሁሉም መሣሪያውን ከአንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጠቀሰ ጊዜ፤ የሕይወት ምግባር ብቻውን ምን ይረባል? ከካህኑ የዕውቀት ጉድለትና የጥበብ ማነስ የተነሣ አንዱ ወደ ኑፋቄ ቢሄድና ከቤተክርስቲያን አካልነት ቢለይ የትህርምቱና የሕይወቱ መልካምነት ጠቀሜታ ምን ላይ ነው? ብዙዎች የተጎዱበትና የጠፋበት አሳዘኝ ሁኔታ ነው:: ትዕግሥቱ፣ ጾሙ . . ለእርሱ ምን ይጠቅመዋል? ሕይወቱ የተበላሸ ከሆነ ትምህርቱን የሚሰማው እንደማ ይኖረው ሁሉ ዕውቀትና ትምህርት ካነሰው ደግሞ ሕይወቱን ብቻ የሚያይ የለም:: ስለዚህ ከሌሎች በበለጠ ሌሎችን አስተምራለሁ የሚል ሰው ጥልቅ ዕው ቀት ሊኖረውና እንዲህ ባለ የክርክር ጉዳዮች ልምድ ሊያከብት ይገባል::

ምንም እንኳ እርሱ ለራሱ የጸናና በተ ቃዋሚዎች ጉዳት የማይደርስበት ቢሆን በእርሱ ስር ያሉ ብዙኃኑ መሪያቸውና መም ህራቸው መልስ አጥቶ ሲረታ፤ ተቃዋ ሚዎችን የማያሳፍርና የነገራቸውን ምንነት ገልጦ ማስረዳትና ማሳየት የሚያቅተው ሆኖ ሲመለከቱ፤ ይህንን መልስ ማጣቱንና ሁኔታውን የእርሱ የሰውየው ድካም ነው ከሚሉ ይልቅ ዶክትሪኑ ራሱ ስሕተት እንደሆነና እምነታቸው ከንቱ እንደሆነ አድርጎ ወደ ማሰብ ይሔዳሉ:: ካህኑ በራሱ የግል የዕውቀት ማነስ የተረታ ሳይሆን እምነቱ ራሱ መልስ የሌለው ቢሆን ነው ብለው ወደ ማጠቃለል ይሮጣሉ:: እንዲህ ያሉት ወደ ጠላት ጎራ ጠቅልለው ባይ ሔዱም ቀድሞ በሚገባ ያመኑባቸውና የተቀበሏቸውን ነገሮች መጠየቅና መጠ ራጠር ይጀምራሉ:: በሃይማኖት መጽናት ይቸግራቸዋል:: ከካህኑ ድል መነሣት የተነሣ በእነርሱ ኅሊና ብዙ መታወክ ይደርስባቸዋል::

በእንዲህ ያለ ሁኔታ ስለሚጠፋው ስለ እያንዳንዱ ነፍስ ይህ ሰው የሚከፈለው ቅጣት፥ የሚጠብቀው መከራ ምን ያህል ከባድና አስፈሪ ነው! ለማሰብ የሚከብድ ነው! ቀ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ለአንባብያን

## የተዘነጋው ታላቁ መሣሪያ

በቤተ ክርስቲያን ጥንተ ታሪክ ጸሎተ ምሕላ ጉልህ ቦታ ይሰጠው እንደነበር ማንኛችንም የምንዘነጋው ጉዳይ አይደለም:: ዛሬ ዛሬ ግን ይህንን ታላቅ መሣሪያ ስንጠቀምበት አንታይም:: የቤተ ክርስቲያንን ጥንተ ታሪክ ብቻም ሳይሆን የትላንቱን እንኳን ብናስታውስ በሃገራችን በኢትዮጵያ ድርቅና አባር ቸነፈር በሆነ ጊዜ ያለዛም ሀገር በጦርነት ሰላሟ ሲናጋ ሲቃረብ በተለይ በገጠሪቷ ኢትዮጵያችን ታቦት ወጥቶ ካህናቱና ሊቃውንቱ እየመሩ ሕዝቡም እየተከተሉ ጸሎተ ምህላው ሲደርስ የታሰበውና የታዘዘው መቅሰፍትና ችግር ሲበተን በምትኩም በረከትና ሰላም ሲሰፍን ሰምተናል፤ ዓይተናል፤ አንብበናልም:: ታዲያ ዛሬ በሃገራችን በኢትዮጵያ በተለይም የጉዳዩ ባለቤት በሆነችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የአሕዛብ ቤቶ ክርስቲያንን ማቃጠል፣ ብሎም የካህናቱ በቤተ መቅደስ መታረድና የምእመናን መገደል ሳያንስ ፕሮቴስታንቶችም ተመሳሳይ ተግባር መፈጸማቸውን በስምዐ ጽድቅ ፲፮ ዓመት ቁ፪ እትም ላይ አንብበናል:: በአጠቃላይ የእስልምና አክራሪው የአሸባሪነት ዘመቻ የኢትዮጵያ ክብር በሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ መሆኑን ስንረዳ እጅና እግራችንን አጣጥፈን መቀመጣችን ለምን ይሆን? በተፈጥሮ አደጋና በድርቅ እየተጠቃን መሆኑንስ እንዴት ዘነጋን? በምህላ ወደ እግዚአብሔር መጮኺያው ጊዜስ ይሔ አልነበረምን? ነው ወይስ ጅቡ እግሩን እየቆረጠመው አጠገቡ የነበረ ጓደኛው ምንድነው የሚሰማው ባለው ጊዜ ዝምበልና ተኛ ጅቡ የእኔን እግር እየቆረጠመ ነው እንዳለው ፈሪ መሆናችን ነው? ከተኛንበት የፍርሃት መኝታ እንንቃና የዘነጋነውን ታላቁን መሣሪያችንን /የምህላ ጸሎት/ እናውጣው:: ይህ ጉዳይ በመሪነታቸው በቀጥታ አባቶቻችንን የሚመለከት ቢሆንም እንኳን ከታች ያለነው ምእመናንም ወደ አባቶቻችን በማመልከት ዕለት ዕለት ማሳሰብ ይጠበቅብናል:: ብቻ ፈጣሪያችን ከሁላችንም ዝንጋኤ ልቡናን ያስወግ ድልን::✣

*ጸዳለ ማርያም ለገሠ*
*/አ.አ/*

## ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

እግዚአብሔር አምላክ ክብር ምስጋና ይግባውና የአሕዛቡ እና የመናፍቃኑ ተስፋ የመቁረጥ ዘመቻ እንዳለ ሆኖ የቤተ ክርስቲያናችንን እንቅስቃሴ ሳስተውለው እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው በየክፍለ ሃገሩ የሚደረገዉን የስብከተወንጌል እንቅስቃሴ፣ ለአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ምላሽ፣ ለምእመናን ማጽኛ የሚጻፉ ወቅታዊ ጽሑፎችን በተለይ ማኅበረ ቅዱሳን በጥልቀት ገብቶበት የሚለቃቸው የመረጃ ጽሑፎች በቀላሉ የምናያቸው ጉዳዮች አይደሉም:: ይህ ሁሉ ሆኖ ግን እጅግ በጣም የሚቆጨኝ አንድ ነገር አለ መዋሐድ የሚገባቸው አካላት ሳይዋሐዱ በተናጠል ሲሮጡ አያለሁ:: የሰ/ት/ቤት ተማሪዎች፣ የስብከተወንጌል ኮሚቴ፣ የሰበካ ጉባዔ አባላት፣ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት፣ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀ መዛሙርት ወዘተ... በብዙ ቦታዎች በንብረት እንደሚሠሩት ሁሉ በጣም በጥቂት ቦታዎች ተባብረው ሲሠሩ አላይም:: አንዳንድ ጊዜ ክፍተቱ ለጠላት ሲመቸው ሁሉ አስተውያለሁ ድሮስ ቢሆን «ውሻ በቀደደው»... አይደል ተረቱ፤ አባቶቻችን አንድ የሚሉት ታላቅ ቁም ነገር አለ «አንድ ጎጆ የሚሠሩ ሰዎች በሳር አይጣሉም» ይላሉ እውነት ነው ለአንዲቷና ስለ አንዲቷ ቤተ ክርስቲያናችን የቆምን ሁላችን ስለምን በሳሩ እንሻማለን? ተመካክረንና ተባብረን ስንሠራ ጠላቶቻችን ይደነግጣሉ፤ ሥራችንም ይከናወናል:: እኔም ይህንኑ እናድርግ እላለሁ::✣

*ሠይፈ ሚካኤል*
*/ድሬዳዋ/*

## ምስጢር ተብየው

ከጥቂት ወራቶች በፊት ሮንዳ ባየርን በተባለች አሜሪካዊት ጸሐፊ የተሠራጨው «The Secret» የተባለው መጽሐፍ በእኛ ሀገር በሲዲ ጭምር ተባዝቶና ወደአማርኛ ቋንቋ ተመልሶ በየቤቱ ገብቷል::

ሰዎች በዚች ምድር ሲኖሩ በሕይወታቸው ሊያዩትና ሊያገኙት የሚመኙትን ማናቸውንም ነገሮች ማግኘት የሚያስችላቸውን «ምስጢር በጥናት አግኝቻለሁ የምትለው ጸሐፊዋ «ምስጢሩም» የስበት ሕግ /Law of Attraction/ እንደሆነ ታስረዳለች::

ለዚህ አጭር ደብዳቤ ምክንያት የሆነኝ ታዲያ የጸሐፊዋ አካሔድ ክርስትናንና ህልዎተ እግዚአብሔርን የሚጻረርና ወንድምና እኅቶቻችንን ወደ ክህደት ዓለም የሚመራ፣ በሥጋዊ እድገትና ብልጽግና /ስኬት/ ካባ ተጀቡኖ ሰይጣናዊ መልእክት ያዘለ መሆኑ ነው:: ይህንንም ልል የቻልኩበትን አንዱን ነጥብ ባነሣ ጸሐፊዋ አንድ ሰው የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ሲፈልግ ጥያቄውን ለነባራዊው ዓለም /Universe/ ያቀርባል ትላለች:: እንግዲህ ልብ በሉ የሰው ልጅ ጥያቄውን የሚያቀርበው በአምሳሉ ለፈጠረው ለእግዚአብሔር አምላክ ሳይሆን ለአካባቢው /Universe/ ሆነ ማለት ነው:: ከዚያም ዩኒቨርስ በጽሑፍ ወይም በቃል በተደጋጋሚ የተላለፈለትን መልእክት በስበት /Law of Attraction/ አማካኝነት ለጠያቂው የሚፈለገውን ነገር በመስጠት መልስ ይመልሳል ማለት ነው:: ይህ በእውነት ለአንድ ክርስቲያን የሚያሳዝንና የጠላታችን የዲያብሎስ ውጊያ በየጊዜው እንዴት እየሰፋና እየጠለቀ መምጣቱን የሚያሳይ ነው::

ስለዚህ ሁላችንም ዘመኑን በመዋጀት ከፊት ይልቅ እዝነ ልቡናችንን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ማስረከብ ይጠበቅብናል እላለሁ:: ✣

*ብንያም አሰፋ*
*/ጎንደር/*




# አዲስ መጽሐፍ

በእርግጥ እግዚአብሔር ለኔ ሕይወት ፍቃድ አለው?

- ሳያነቡት ሊያመልጥዎ የማይገባና ለልብ ወዳጅዎ በገፀ በረከትነት ሊሰጡት የሚችሉት ምርጥ መጽሐፍ
- የእግዚአብሔር ፍቃድ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ምን እንደሚመስል በሰፊው ያትታል
- በመከራ ውስጥ ስንሆን እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ መከራችንን እንደሚመለከተው ይናገራል
- እግዚአብሔር የሚፈቅደው እውነተኛው የአምልኮ ስርዓት የትኛው እንደሆነ ሌሎችንም ጉዳዮችን ይዳስሳል

መጽሐፉን ማከፋፈል ለምትፈልጉ
0912 141044 ደውሉልን


©ማኅበረ ቅዱሳን 


ውዳሴ ማርያም ዜማ
የቅዱስ ኤፍሬምን ድርሰት በቅዱስ ያሬድ ዜማ
"ቅድስት ሆይ ለምኝልን"
የጣና ገዳማት
ክፍል ፩ እና ፪ ዘጋቢ ፊልም
አዲስ የቪሲዲ ገጸ በረከት
በጣና ሐይቅ፡- ስንት ደሴቶች አሉ?
ምን ያህል ገዳማት ይገኛሉ?
ገዳማቱ መቼ ተመሰረቱ?
ታሪካቸው ምን ይመስላል?
የነገሥታት አጽም፣ የኦሪት መሥዋዕት፣
የቅዱስ ሉቃስ ሥዕለ ማርያም፣ አስደናቂ ገቢረ
ተአምራትን እና ሌሎችንም
ድንቃ ድንቅ ታሪኮች
የሚጉበኙበት
ምርጥ ፊልም!
አድራሻ
ቅ/ማርያም ሱቅ፡- ከ5 ኪሎ ወረድ ብሎ ሸዋ ዳቦ ቤት አጠገብ
ቅ/ጊዮርጊስ ሱቅ፡- እሳት አደጋ ፊት ለፊት ከ3 ቁ. አውቶቡስ መነሻ አጠገብ
ቅ/ልደታ ሱቅ፡- ከቅ/ልደታ ቤተክርስቲያን ከፍ ብሎ ከአፍሪካ ከፍተኛ ክሊኒክ ፊት ለፊት
በተጨማሪም ክ/ሀገር በሚገኙት በሁሉም የማኅበሩ ማዕከላት ሱቆች ያገኙዋቸዋል።
011-124 61 82/24 61 84/0111-56 67 88 E-mail- MK_distribution@yahoo.com ፖ.ሳ.ቁ 80078 አ.አ
የኦዲዮ ቪዥዋልና ሥነ ጥበባት ሥራዎች ማዕከል
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
አዲስ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ፡-
ማስታወቂያ
ዘጋቢ ፊልም
መዝሙር
የትርጉም ሥራ
ልብ ወለዳዊ ፊልም
ትረካ
በቅርብ ቀናት ከአዳዲስ የትረካ ሥራዎች ጋር እንገናኝ።
CUT
አድራሻ፡- ከአራዳ ጊዮርጊስ ቤ/ክ ወደ ስድስት ኪሎ በሚወስደው መንገድ ከመቅደላ ሆቴል አጠገብ
ስልክ - 0111-56 67 88
ዋጋ 4.00

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡